# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 81ኛ ዓመት ቁጥር 220 ሚያዝያ 10 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





# ምክር ቤቱ አገራዊ ምክክሩ አካታችና ግልጽ እንዲሆን በትኩረት መሥራት እንደሚገባ ገለጸ


ዶክተር ራሔል ባፌ

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- አገራዊ ምክክሩ አካታችና ግልጽ ሆኖ በሁሉም ኢትዮጵያውያን ዘንድ ቅቡልነት እንዲኖረው በትኩረት መሥራት እንደሚገባ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ገለጸ።

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢ ዶክተር ራሔል ባፌ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አገራዊ ምክክሩ ለዘመናት ሲንከባለል የመጣውን ችግር በመፍታት የሁሉም ነገር መፍትሔ ይሆናል የሚል ተስፋ ተጥሎበታል። በመሆኑም ሂደቱ ግልጽና አካታች ሆኖ በሁሉም ባለድርሻ አካላት ዘንድ ቅቡልነት እንዲያገኝ መሥራት ይገባል ።

አገራዊ ምክክሩ ገና ጅምር ዝግጅት ላይ ይገኛል ያሉት ዶክተር ራሔል፤ የተጠበቀውን ውጤት እንዲያመጣ ከአሁን ጀምሮ ለሁሉም ግልጽ ሆኖ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በንቃት የሚሳተፉበት እንዲሆን መሥራት እንዳለበት ገልጸዋል።


ምክር ቤቱ አገራዊ ምክክሩ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





# በኢትዮጵያና በጎረቤት አገራት መካከል ያለው የነዳጅ ዋጋ ልዩነት ሕገወጥ ንግዱን እያባበሰው መሆኑ ተገለጸ

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- በአሁኑ ወቅት ነዳጅ በኢትዮጵያ የሚሸጥበት እና በጎረቤት አገራት የሚሸጥበት ዋጋ ልዩነት የተጋነነ መሆኑ ሕገወጥ ንግዱን እንዳባባሰው የኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት ገለፀ።

የኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ታደሰ ኃይለማርያም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ መንግሥት የነዳጅ ዋጋን ከጎረቤት አገራት የነዳጅ መሸጫ ዋጋ ያለው የተጋነነ ልዩነት ባለማጥበቡ ምክንያት አገር ውስጥ በተሰገሰጉ ሕገወጥ ነጋዴዎች አማካኝነት ከአገር በሚወጡና ሕገወጥ ንግዱ ተባብሷል።

በአዲስ አበባም ሆነ በክልል ከተሞች ነዳጅ በየሥርቻው ሊሸጥ የበቃው ነዳጅ በተገቢው የዋጋ ተመን እንዲሸጥ ባለመደረጉ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ነዳጅ አምራች አገራት እንኳን በማይሸጡበት ዋጋ ነዳጅ እየሸጠች ነው፤ የሚሉት ሥራ አስፈፃሚው፤ ዋጋው እስከ እጥፍና ከዚያ በላይ የሚለያይ መሆኑ ሕገወጥ ንግዱን እንዲስፋፋ አድርጓል ብለዋል ።

ነዳጅ አምራች አገራት ካልሆኑ በስተቀር ሸማች አገራት ሙሉ በሙሉ ድጎማ ሳያደርጉ በገዙበት ዋጋ እየሸጡ እንደሆነም አመልክተው፤ወደ ጎረቤት አገራት የሚሄድ የነዳጅ የኮንትሮባንድ ንግድ ስላስቸገረ ዋጋውን ከጎረቤት አገራት ጋር እኩል በማድረግ መከላከል እንደሚቻል ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ታደሰ ገለፃ፤ መንግሥት በሌለው የውጭ


በኢትዮጵያና በጎረቤት አገራት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ታደሰ ኃይለማርያም




# የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት በክልሉ የተለያዩ እርምጃዎች እየተወሰዱ ናቸው


ዶክተር ኢንጂነር ነጋሽ ዋጌሾ

መዓዛ ማሞ

አዲስ አበባ፡- የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት በክልሉ የተለያዩ እርምጃዎች እየተወሰዱ እንደሆነ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል መንግስት አስታወቀ።

የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ኢንጂነር ነጋሽ ዋጌሾ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት; ከክልሉ ነዋሪዎች ጋር በቅርቡ በተደረገው ውይይት ከተነሱ የሕዝብ ጥቄዎች አንዱ የኑሮ ውድነት ነው። ይህንን ችግር ለመቅረፍ ኅብረተሰቡን በማደራጀት ሸቀጦችንና ምርቶች የፍጆታ እቃዎች በክልሉ ዋና ዋና ከተሞች በኅብረት ሥራ ማኅበራት በኩል እንዲቀርቡ የማድረግ ሥራ መጀመሩን የጠቆሙት ርዕሰ መስተዳድሩ፤በሚቀጥለው የምርት ዘመን ምግብ ነክ ምርቶች ላይ እጥረት እንዳይገጥም ከወዲሁ የግብርና ሥራዎች በተለየ ትኩረት


የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ዶክተር መለስ መኮንን

## በምርት ዘመኑ ከ405 ሺ በላይ ሄክታር መሬት በስንዴ እየለማ ነው


ገጽ 4








# አፓርታማዎችን በሳምንት የሚያጠናቅቅ የፈጠራ ውጤት ይዞ በፋይናንስ የሚፈተነው ወጣት

**ውብሸት ሰንደቁ**

ኢትዮጵያ በኮንስትራክሽን ዘርፍ 60 በመቶ ያህሉን ዋና ዋና የግንባታ ዕቃዎቿን ከውጭ አገራት ነው የምታስገባው። ለዚህም ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወጪ ታደርጋለች። ይህን የውጭ ምንዛሪ ለማደን በአገር ልጆች የሚሠሩ የፈጠራ ውጤቶችን ከመጠቀም ይልቅ ከውጭ የሚመጡ ግብዓቶችን መጠቀም የተለመደ ተግባር ሁኗል።

በዚህ ምክንያትም የአገር ውስጥ የፈጠራ ባለቤቶችን ደግፎ ለቁም ነገርና ለውጤት ማብቃት አልተለመደም። ወንድማገኝ ገለታ ከእነዚያ የፈጠራ ባለቤቶች መካከል አንዱ ነው። የዜጎችን ሕይወት ይቀይራሉ፤ የኑሯቸውንም ሁኔታ ያሻሽላሉ ያላቸውን የተለያዩ ፈጠራዎችን ወልዶ ስሟል።

ወጣት ወንድማገኝ የመጀመሪያ ዲግሪውን ከአዳማ ዩኒቨርሲቲ ሁለተኛ ዲግሪውን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በአርክቴክቸራል ኢንጅነሪንግ ተመርቋል። ወጣቱ በአሁኑ ጊዜ በባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ አርቴክቸር ትምህርት ክፍል በመምህርነት እያገለገለ ይገኛል።

ይህ ወጣት በእጁ በርካታ የፈጠራ ሥራዎች ቢኖሩትም በኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት የተወደደና ኢኒስቲትዩቱ የተለያዩ አጋር ተቋማትን ሰብስቦ ይህን ድንቅ ሥራ ተመልከቱልኝ ብሎ መርጦ ካሳያቸው ሥራዎች አንዱ የሆነውን ነው።


የወጣቱ የፈጠራ ሥራ በሌሎች አገራት እንዲህ ይደረጋል እየተባለ ጭምጭምታቸውን የምንሰማላቸውን ተገጣጣሚ የመኖሪያ ቤቶች በኢንዱስትሪ ውስጥ ተመርተው የትም ሄደው እንዲገጣጠሙ የሚያስችል ነው።

እንደ ወጣቱ ፈጠራ መኖሪያ ቤቶቹ ከኮንክሪትና ከብረት ግብዓትነት ይመረታሉ፤ አስፈላጊው ቦታ ላይ ሄደው በብሎን ይገጣጠማሉ። እያንዳንዱ ቤት ሲገጣጠም ምን ያህል እንደሚሸከም ታሳቢ ተደርጎ የተሠራ ስለሚሆን ጥንካሬው በሳይንሳዊ መንገድ የተረጋገጠ ነው። በተገጣጣሚ ክፍሎቹ እስከ ጂ ፕላስ 7 ድረስ መሥራት እንደሚቻል በተለያዩ አካላት መፈተሹን ወጣት ወንድማገኝ ይናገራል።

የፈጠራ ሥራ አንድ ጊዜ ተፈጥሮ የሚያቆም እንዳልሆነ የተረዳው ወጣቱ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሥራውን እንደከለሰለት ይገልጻል። ወደ ትግበራ የሚገባበትን መንገድም በመነጋገር ላይ እንገኛለን ብሏል። የኮምፒውተር ሲሙሌሽን ሥራውንም አጠናቋል። በፈጠራ ሥራው ባለቤትነት ጉዳይ ላይ ከአዕምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት ለዚሁ ፈጠራ ማረጋገጫ ለማግኘት ወደ ማጠናቀቁ ላይ ይገኛል።

ይህ ፕሮጀክት ተግባራዊ ቢደረግ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የበርካታ ዜጎችን የመኖሪያ ቤት ጥያቄ ሊመልስ የሚችል ስለመሆኑ ወጣት ወንድማገኝ በልበ ሙሉነት ይገልፃል። ከዋጋ አንፃርም በጣም የተሻለ ነው ይላል። የመኖሪያ ቤቶች ሽያጭ በጊዜ ልክ የሚለዋወጥ ቢሆንም ለዚህ ፕሮጀክት ተብሎ ታኅሳስ 2014 ዓ.ም ላይ በተጠናው መሠረት በካሬ ሜትር 17 ሺህ ብር ቅናሽ አለው። ይህም በሕንፃ ደረጃ ሲሰላ ከፍተኛ የዋጋ ልዩነት ያለው መሆኑን ወጣቱ ያስረዳል።

እንደ ወጣት ወንድማገኝ ገለፃ፤ ፕሮጀክቱን ወደሥራ ለማስገባት እንደመነሻ ለማሽንና ለኢንዱስትሪው ሼድ ግንባታ 28 ሚሊዮን ብር ያስፈልጋል። 28 ሚሊዮን ብር ፋይናንስ አድርጎ ፈጠራዬን የሚደግፍልኝ ስላጣሁ በቀላሉ ሊፈታ የሚችለው የከተሞች የቤት ችግር አሁንም አንገብጋቢ እንደሆነ ቀጥሏል ይላል ወጣት ወንድማገኝ።





ወጣት ወንድማገኝ ገለታ

እንዲያውም ስለተገጣጣሚ ቤቶች ሲታሰብም የአገር ውስጥ የፈጠራ ውጤቶችን መጠቀም ሳይሆን የውጭ ቴክኖሎጂዎችን የማምጣት አዝማሚያ ነው የሚታየው በማለት ትዝብቱን ያክላል። በርካታ የመንግሥት ተቋማትን በር ቢያንኳኳም ፊት የሚሰጠው አለማግኘቱ እንዳሳዘነውም ይናገራል።

የተገጣጣሚ መኖሪያ ቤት ፋብሪካው ሙሉው ግንባታ ላይ ሲደርስ በሳምንት እስከ 7ኛ ወለል ያላቸውን አራት አፓርታማዎችን መገንባት የሚችልበት ደረጃ ላይ ይደርሳል። የመኖሪያ ቤት አንዷን ክፍል ለመሥራት የሚወስደው ስድስት ሰዓታትን ብቻ ነው። በየ24 ሰዓቱ ሦስት ክፍሎችን መሥራት እንደሚቻል ነው የነገረን።

ሆኖም እዚህ ፈጠራ ላይ ደፈር ብሎ ኢንቨስት ማድረግ የሚችል አካል በመጥፋቱ በየቀኑ ብዙ የመኖሪያ ቤት ጥያቄዎች እንዲፈጠሩ ከማድረጉም ባሻገር ገቢ ሊሆኑ የሚችሉ ገንዘቦችም በከንቱ እየቀሩ ነው ሲል ስሜቱን በቁጭት ይገልፃል።

ይህ የቤት ግንባታ ፈጠራ ከአገር ውስጥ ምርቶች ወደ 70 በመቶ የሚሆነውን ግንባታ መጠቀሙም ሌላው መልካም ጎኑ መሆኑን ገልጾዋል። አገሪቱ እስካሁን ባለው መረጃ ከውጭ እያስገባቻቸው የምትገኘው ዋና ዋና የግንባታ ግብዓቶች በመቀነስ ረገድ ተስፋ ሰጭ ነው።

ፋይናንሱ ከተገኘ በማግስቱ ለመጀመር ሁሉም ነገር ዝግጁ አድርጌ እየጠበቅሁ ነው የሚለው ወጣት ወንድማገኝ ከመከላከያ ኢንጅነሪንግ ኮሌጅ የመሞከሪያ ቦታ ፈቃድ ማግኘቱንም ይናገራል።

# በቡኖ በደሌ በንብ ማነብ በተደራጁ ወጣቶች በዓመት 16ሺ ቶን ማር ለገበያ ይቀርባል

**ስምስም መንግስቱ**

በደሌ፦በኦሮሚያ ክልል በቡኖ በደሌ ዞን በንብ ማነብ በተደራጁ ወጣቶች አማካኝነት በዓመት እስከ 16 ሺህ ቶን ማር ለገበያ እንደሚቀርብ ተገለጸ።

በኦሮሚያ ክልል ትኩረት ከተሰጣቸው የግብርና ሥራዎች አንዱ በሆነው በንብ ማነብ የማር ልማት ለወጣቶች በተፈጠረ የሥራ ዕድል እየተከናወነ ያለው ሥራ ውጤታማ እየሆነ መጥቷል ብለዋል።

የዞኑ ምክትል አስተዳዳሪ አቶ ግርማ ፍቃዱ ትናንት በበደሌ ከተማ በተካሄደ የማር ፌስቲቫል ላይ እንደተናገሩት፤ በዞኑ በባህላዊና በዘመናዊ የማር ልማት በዓመት እስከ 16ሺ ቶን ማር ለገበያ እንደሚቀርብና በዘርፍ ሞዴል አርሶ አደሮች መፍጠር ተችሏል። እስከ 600 የንብ ቀፎ ያለው አርሶ አደር መፈጠሩ የሥራ ተነሳሽነትን እየጎለበተ መምጣቱን ያሳያል።

በኦሮሚያ ክልል ቡኖበደሌ፣ኢሉአባቦራ፣ጅማና ምሥራቅ ወለጋ ዞኖች ለማር ልማት ምቹ መሆናቸውን አመልክተው፤ ይህንኑ ዘርፍ ለሥራ ዕድል በመጠቀም ላለፉት አራት ዓመታት በተከናወነው ሥራ በዘመናዊ የአመራረት ዘዴ በገበያ ላይ ተወዳዳሪ የሆነና ጥራት ያለው ማር ማምረት መቻሉን ገልጸዋል።

የክልሉ መንግሥትም ሀብቱ የሚገኝበት የክልሉ ምዕራብ ክፍል በአግባቡ እንዳልተጠቀመበት ከዚህ ቀደም መልዕክት ማስተላለፉን በማስታወስ፣ ይህንኑ መነሻ በማድረግ በተከናወነ እንቅስቃሴ በቡኖ በደሌ ዞን እየተገኘ ያለውን ውጤት እንደሚያስቀጥል ገልጸዋል።

በክልሉ አራት ዞኖች ውስጥ ከሁለት ዓመት በፊት በስልጠና፣በቁሳቁስ ድጋፍ በንብ ማነብ የማር ልማት የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸውን ወጣቶች በማገዝ እየሠራ ያለው በማስተር ካርድ ፋውንዴሽን የሚታገዘው ዓለም አቀፍ የሥነ ነፍሳት የምርምር ማዕከል ሞይሽ ፕሮጀክት ለውጤቱ ትልቅ አስተዋፅኦ ማበርከቱን ገልጸዋል።



ፕሮጀክቱ በሚኖረው ቀሪ ሶስት ዓመታት በሚሰጠው ድጋፍ የበለጠ ውጤት ይመዘገባል ብለዋል። የማር ልማቱ በቤተሰብ ደረጃ ይበልጥ ተስፋፍቶ የልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ይሠራል ብለዋል።

የስነ ነፍሳት ምርምር ማዕከል የሞይሽ ፕሮግራም የኦሮሚያ ተጠሪ ሥራ አስኪያጅ አቶ ተሾመ ኩመላ እንደገለፁት፣ በክልሉ አራት ዞኖች ስምንት ወረዳዎች ውስጥ ያለውን ሀብት ማዕከል በማድረግ ፕሮግራሙ ከሁለት ዓመት በፊት የተጀመረ መሆኑን አውስተው፣እስካሁን በተከናወነው ሥራ 14ሺ 200 ወጣቶች በንብ ማነብና ማር ልማት ስልጠና አግኝተው ወደ ልማት ገብተዋል። ከእነዚህ ውስጥም 60 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

በተደረገላቸው የቁሳቁስ ድጋፍና ባገኙት ስልጠና በሁለት ዓመት 188ሺ ኪሎ ግራም ማር አምርተው ተጠቃሚ ሆነዋል። ንብ በማባዛትም ክህሎት አግኝተዋል። በአጠቃላይ የተጣራና የታሸገ ማር በጥራት በማምረት በአካባቢው ላይ ማሳየት መቻላቸውን ገልጸዋል።

# መኢአድ በኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት እንዲከበርና አንድነት እንዲጠናከር እንደሚታገል ገለጸ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) በኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት እንዲከበርና አንድነት እንዲጠናከር የጀመረውን ትግል አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታወቀ።

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) 9ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔውን በትናንትናው ዕለት በአዲስ አበባ አካሂዷል። በጉባኤው ላይ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የፓርቲው ፕሬዚዳንት አቶ ማሙሸት አማረ እንደገለጹት፣ በአንድ አገር ውስጥ ዜጎች ሠርተው ሊለውጡ የሚችሉት ሰላም ሲኖርና የሕግ የበላይነት ሲከበር ነው። በኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት እንዲከበርና አንድነት እንዲጠናከር መኢአድ ላለፉት በርካታ ዓመታት ሲታገል ቆይቷል፤አሁንም ትግሉን አጠናክሮ ይቀጥላል።



የአምባገነኑን የኢሕአዴግ መንግሥት ኢትዮጵያ በጎጥና በማንነት ከፋፍሎ ሲገዛና ኢትዮጵያን ሲያፈርስና ሕዝቦቿን ሲያሰቃይ ነበር ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ወደፊትም ኢትዮጵያን ማዳን የሁላችንም ኃላፊነት ነው። በአሁኑ ወቅት አገራችን ከመጠን በላይ ሕመሟ በዝቷል። ከሕመሟ እንድትፈወስና ወደ ፊት ጠንካራ አገር አድርጎ ለማስቀጠል ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለነጻነቱ፣ ለክብሩ፣ ለአኩልነት፣ ለፍትሕና ለሕግ የበላይነት የመታገል ግዴታ አለበት ብለዋል።

አገር ከሌለ ሰርቶ ማደግ አይቻልም ያሉት አቶ ማሙሸት፤ አገራችን አሁን ያለችበት የሰላም ሁኔታ ከየትኛውም ጊዜ በላይ አሳሳቢና አስቸጋሪ ነው። ከዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ለመውጣትና እየተስተዋሉ ያሉ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት የሁሉም ኢትዮጵያያን ኃላፊነት መሆኑን አመልክተዋል።

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅትም በኢትዮጵያ እየተከሰቱ ያሉ ችግሮችን ለማስቆምና ዘላቂ መፍትሄ እንዲያገኙ ይሠራል ሲሉ ገልጸዋል።

የሚስተዋሉ ችግሮችን በራሳችን ትግልና ጽናት መፍታት ካልቻልን በስተቀር ችግራችንን ሌላ አካል መጥቶ አይፈታልንም ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ለሰላም የሚከፈለው ዋጋ ከፍተኛ መሆን አለበት ሲሉ አሳስበዋል።

እንደ አቶ ማሙሸት ገለጻ፤ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለሕዝባችንና ለአገራችን በገባነው ቃል ኪዳን መሠረት በጋራ ተባብረን መሥራት ይኖርብናል። አንድ ትልቅ ኃይል በመፍጠር ለኢትዮጵያ ሕዝብ አስተማማኝ ሰላምን ለማረጋጋጥ በጋራ መሥራት አለብን ሲሉ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።

# ከኢድ እስከ ኢድ መርሐ ግብር ላይ በአማራና አፋር በጦርነቱ የተጎዱ መስጅዶችን የማስገንብኘት ዕቅድ ተይዟል

**ዳግማዊት ግርማ**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> ከኢድ እስከ ኢድ በተሰኘው መርሐ ግብር በአማራና  አፋር ክልሎች በጦርነቱ የተጎዱ መስጅዶችንና አካባቢዎችን የማስጎብኘት ዕቅድ መያዙን የከኢድ እስከ ኢድ አገራዊ ጥሪ አስተባባሪ ኮሚቴ አስታወቀ።

በጦርነቱ ምክንያት ውድመት የደረሰባቸውን መስጂዶች የማስጎብኘትና ከዲያስፖራው ማኅበረሰብ ጋር የመልሶ ማቋቋም ዕቅድ እንዳለም አስተባባሪ ኮሚቴው ገልጿል።

የአስተባባሪ ኮሚቴው አባል ኡስታዝ ካሚል ሸምሱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በኢድ እስከ ኢድ የተሰኘውን አገራዊ ጥሪ ተከትለው ወደ አገር ቤት የሚመጡ ዳያስፖራዎች በአማራና  አፋር አካባቢዎች በጦርነቱ የተጎዱ የተመረጡ ስፍራዎችንና መስጂዶችን እንዲጎበኙ ይደረጋል።

የጉብኝት መርሐ ግብሮቹ ከሚካሄድባቸው አካባቢዎች መካከል በአማራ ክልል ሰሜን ጎንደር፤ ሰሜንና ደቡብ ወሎ ዞኖች እንዲሁም በአፋር ክልል የተለያዩ ዞኖች ይገኙበታል ብለዋል።

በመርሐ ግብሩ መሠረት በጦርነቱ ምክንያት ውድመት የደረሰባቸውንና በአሸባሪው የሕወሓት ቡድን ሆን ተብሎ ጉዳት የደረሰባቸውን ሃይማኖታዊ ተቋማት፣ ሃይማኖታዊ መጽሐፍትና ታሪካዊ ቅርሶች በቪዲዮና በድምፅ በታገዙ ማስረጃዎችን ጭምር ለጎብኚዎች እንዲቀርቡ እንደሚደረግ ገልጸዋል።

ለዚህም በአግባቡ የተደራጀ ሰነድ ተዘጋጅቷል፤ በጦርነቱ የተጎዱና ችግሩ የደረሰባቸው አካባቢዎችን በማስጎብኘት ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያኑ በጦርነቱ ምክንያት ስለደረሰው ውድመት በቂ መረጃ እንዲኖራቸው ጥረት ይደረጋል ሲሉ ኡስታዝ ካሚል ተናግረዋል።

በአገራዊ ጥሪው መሠረት ለሚመጡ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያኑ ሃይማኖታዊና አገራዊ ግዴታዎቻቸውን የሚወጡባቸው መርሐ ግብሮች እንደተዘጋጀላቸው የተናገሩት ኡስታዝ ካሚል፤ ከዝግጅቶቹ መካከልም ዋነኞቹ ለተጎዱ ወገኖች ድጋፍ የሚደረግባቸው መርሐ ግብሮች መኖራቸውን ገልጸዋል።

በተለይም የመልሶ የማቋቋም ሥራና ለተጎዱ ሃይማኖታዊ ተቋማት ድጋፍ የማድረግ ክንውን እንደሚኖርም ጠቁመዋል።

የቱሪዝምና የኢንቨስትመንት ፍሰትን ሊጨምሩ የሚችሉ የጉብኝት መርሐ ግብሮች፣ ሲምፖዚየምና ታላቅ የአፍጥርና የሰላት ዝግጅቶች ዲያስፖራዎቹ በተገኙበት እንደሚከናወኑ አስታውቀዋል።

ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያኑን አገራዊ ጥሪውን ተከትሎ የተለያዩ ቅርሶችንና የተጎዱ አካባቢዎችን ለማየት ያላቸውን ፍላጎት እየገለጹ ይገኛል። በተለያዩ ዓለማት የሚገኙ በርካታ ዜጎች በመርሐ ግብሩ ለመሳተፍ ወደ አገር ቤት መግባት ጀምረዋል ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በታላቁ የረመዳን ወር በኢትዮጵያ ታላቁ የኢድ ሶላት እንዲደረግ ያስተላለፉትን ጥሪ ተከትሎ "ከኢድ እስከ ኢድ" በሚል ስያሜ ለተሰናዳው መርሐ ግብር የተለያዩ ዝግጅቶች እየተደረጉ ይገኛል።


ኡስታዝ ካሚል ሸምሱ

በኡስታዝ አቡበከር አሕመድ የሚመራው የመርሐግብሩ አስተባባሪ ኮሚቴም ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በዝግጅቶቹ ላይ እንዲታደሙ ለማስቻል ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርንና ከተለያዩ የፌዴራል ተቋማት ጋር በጣምራ እየሠራ ይገኛል።

መርሐ ግብሮቹ በሁለት ምዕራፍ ተከፍለው የቀረቡ ሲሆን፥ የመጀመሪያው ዙር መርሐ ግብሮች ከሚያዝያ 3 እስከ ግንቦት 3 ቀን 2014 ዓ.ም፤ የሁለተኛው ዙር መርሐ ግብሮች ደግሞ ከሰኔ 24 እስከ ሐምሌ 4 ቀን 2014 ዓ.ም እንደሚካሄዱ ከኢትዮጵያ ዲያስፖራ ኤጀንሲ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

# የሸቀጦች ዋጋ ላይ እየታየ ያለው የዋጋ ጭማሪ የሸማቾችን የመግዛት አቅም ፈትኗል

**በኃይሉ አበራ**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> በየጊዜው እየጨመረ በመጣው የመሠረታዊ የሸቀጦች ዋጋ ጭማሪ የመግዛት አቅማቸውን እየተፈታተነ መሆኑን ሸማቾች ተናገሩ። መንግሥት ኢኮኖሚውን ለማረጋጋት መሠረታዊ በሆኑ ሸቀጦች ላይ የአጭር ጊዜ የዋጋ ተመን እንዲያወጣ ተጠየቀ።


የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በአዲስ አበባ በተለያዩ አካባቢዎች በመዘዋወር ሸማቾችንና ነጋዴዎችን በጉዳዩ ላይ አነጋግሯል፤ አስተያየታቸውን የሰጡት የአዲስ አበባ ነዋሪ ወይዘሮ ደስታ ደበሌ እንደሚሉት በመሠረታዊ የሸቀጦች ዋጋ ላይ በየጊዜው ከፍተኛ ጭማሪ እየታየ ነው። ይህ መሆኑም ምርቶችን የመግዛት አቅማቸው ላይ ጫና ፈጥሯል።

ከአንድ ወር በፊት 105 ብር የነበረው የአገር ውስጥ ምስር በአሁኑ ጊዜ 130 ብር ገብቷል፤ 95 ብር የነበረው ከውጭ የገባው ምስር ደግሞ ከ100 ብር በላይ እየተሸጠ ስለመሆኑ መታዘባቸውን ተናግረዋል። ቡና በኪሎ እስከ 400 ብር፣ ዘይት አምስት ሊትር ደግሞ 900 ብር መሸመታቸውን ተናግረዋል።

ለመሠረታዊ የሸቀጦች ዋጋ ጭማሪ ከነጋዴዎች በኩል የሚሰጠው ምላሽ ከአከፋፋዮች ጭማሪ በማሳየቱና እቃ ስለማይገባ የሚል ቢሆንም በአገር ውስጥ የሚመረቱትም ከፍተኛ የዋጋ ጨማሪ እየታየባቸው ነው ብለዋል።

ነጋዴውም ሆነ ሸማቹ መካከል የተሻለ የግብይት አማራጭ ማስፋት ይገባል የሚሉት ወይዘሮ ደስታ፤ መንግሥትም ለሸማቾች አማራጮችን መፍጠር እንዳለበት ይመክራሉ።

ሌላኛው አስተያየት የሰጡት አቶ ይበልጣል ሽሽጉ በበኩላቸው፤ ከጸጥታ ስጋት ጋር በተያያዘ ነጋዴዎች እንደልብ አለመንቀሳቀሳቸው ጠቅሰው፤ መንግሥት ነጋዴው በደረሰኝ እንዲሸጥ እንደሚቆጣጠረው ሁሉ ነጋዴ አርሶ አደሮችም ላይ ቁጥጥር ማድረግ ባለመቻሉ የመሠረታዊ ሸቀጦች ዋጋ በየጊዜው እየጨመረ ነው ብለዋል።


አቶ ይበልጣል ሽሽጉ


ወይዘሮ ደስታ ደበሌ


አቶ ደረጀ ደስታ

የአገር ውስጥ ምስር በኪሎ 123 ብር፣ የውጭ ምስር 100 ብር እንደሚሸጡም ተናግረዋል። ነጋዴውም ሆነ በላተኛው በመተሳሰብ የገበሬ ነጋዴዎችም ለወገኑ እንደሚሸጥ በማሰብ አገር ውስጥ የሚያመርተውን ምርት ከመጠን በላይ ጭማሪ ማድረግ እንደሌለበት መክረዋል።

በሾላ ገበያ በቅቤ ንግድ የተሠማሩት አቶ ደረጀ ደስታ በበኩላቸው ሸኖ ለጋ ቅቤ 800 ብር በመካከለኛ እና በሳል ቅቤ 650 ብር እየተሸጠ መሆኑን ጠቁመዋል። በተለይ ከ15 ቀናት ወዲህ ከተለመደው ዋጋ በላይ ጭማሪ በምርቶች ላይ እየታየ መሆኑን በመጠቆም።

ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞም ገበሬው ጋር እጥረት በመኖሩ አከፋፋዮች ጋርም የምርት እጥረት አለ ያሉት አቶ ደረጀ፤ ነጋዴው አላስፈላጊ ጥቅም ለማግኘት ማሰብን ቢያቆምና ሸማቹም ከመጠን ያለፈ ምርትን ባለመሸመት የምርት ተደራሽነት እንዲሰፋ ቢደረግ በተወሰነ ሁኔታ የዋጋ ንረቱን ማስተካከል ይቻላል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ሸማቾች መብት ተቆርቋሪ ድርጅት መሥራችና ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ቁምላቸው አበበ እንደሚሉት፤ ለገበያ ዋጋ መናር ዋነኛው ምክንያት ስነ ምግባርን ተላብሰው የሚንቀሳቀሱ ነጋዴዎች  እንዳሉ ሁሉ ምርትን በመደበቅ ሰው ሠራሽ እጥረት እንዲፈጠር ካደረጉ በኋላ ምርት የሚያወጡ ነጋዴዎች መኖራቸው ነው ይላሉ።

የተወሰኑ ቡድኖች የገበያውን ሁኔታ ተነጋግረው በአድማ መወሰንና ዋጋ በመቁረጥ ሕገ ወጥ ግብይት እየተፈጠረ በመሆኑ መንግሥት ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ እንደሚገባው አመልክተዋል።

ገበያው የሚወሰነው ነጻ ገበያ ፖሊሲ እንደምትከተል አገር በአቅርቦት እና ፍላጎት ሳይሆን ደላሎች በተመኑት ዋጋ ወደ ገበያው ሲገባ እየታየ በመሆኑ የግብይት ሂደቱ ሥርዓት አለባ መሆኑ አንዱ ምክንያት መሆኑንም ጠቅሰዋል።

ሙዝ አርባ ምንጭ ከሰባት ብር እስከ 12 ብር በደረጃ ይሸጣል፤ አዲስ አበባ ሲገባ 40 ብር ነው። ይሄንን ትርፍ የሚያገኘው አርሶአደሩ ሳይሆን በመሐል ያለው ደላላው ነው።

እንደ አቶ አቶ ቁምላቸው ገለጻ፤ የኑሮ ውድነቱ በየመሥሪያ ቤቱ የሚታየው ሙስና እና የአገልጋይነት ስሜት መጓደል ተዳምሮ አጠቃላይ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ መዋቅራችንን እያዛባ ነው።

አምስት ሊትር የዘይት ዋጋ 900 ብር ገብቷል። ከፊት የበዓላት መደራረብ ጋር ተያይዞም የቅቤ እጥረት ባይኖርም አብዛኛው ሰው ሳይወድ ቅቤ ላይ ያለው ፍላጎት ይጨምራል።

ባለፉት 30 ዓመታት ፖሊሲያችን መንግሥት ወደ ኢኮኖሚው በሚረጨው ከፍተኛ ገንዘብ የተወሰነ የኅብረተሰብ ክፍልን ተጠቃሚ በማድረግ የመጣ ነው ያሉት አቶ ቁምላቸው፤ ገንዘብ ገበያ ላይ ሲበዛ የምርቶች ዋጋ እንዲወደድ ያደርጋል ስለሆነም የኢኮኖሚ ፖሊሲው መፈተሽ እንዳለበት ጠቁመዋል።

መንግሥት ኢኮኖሚውን ለማረጋጋት መሠረታዊ በሆኑ ሸቀጦች ላይ የአጭር ጊዜ የዋጋ ተመን ማውጣት፤ የትርፍ ህዳግ (ፕሮፊት ማሪጅን) መወሰን፣ ስለሸማቾች መብት ከሚቆረቆሩ ድርጅቶች ጋር በቅንጅት መሥራት እንዳለበትም አመልክተዋል።



ዶክተር መለሰ መኮንን

# በምርት ዘመኑ ከ405 ሺ በላይ ሄክታር መሬት በስንዴ እየለማ ነው

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ በዘንድሮው የበልግና የበጋ መስኖ ምርት ዘመን ከ405 ሺህ በላይ ሄክታር መሬት በስንዴ እየለማ መሆኑን ግብርና ሚኒስቴር ገለጸ። በበጋ መስኖ ከ44 ሺህ በላይ ሄክታር መሬት በስንዴ እየለማ መሆኑን አመልክቷል።

በግብርና ሚኒስቴር የእርሻና ሆርቲካልቸር ሚኒስቴር ዴኤታ ዶክተር መለሰ መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በዘንድሮው የበልግና የበጋ መስኖ ምርት ዘመን በአገር አቀፍ ደረጃ ከ405 ሺህ በላይ ሄክታር መሬት ስንዴ እየለማ ነው። በበጋ መስኖ ደግሞ ከ44 ሺህ በላይ ሄክታር መሬት በስንዴ እየለማ ነው።

እንደ ዶክተር መለሰ ገለጻ፣ በኢትዮጵያ በተያዘው የምርት ዘመን እየለማ ካለው ከ450 ሺህ በላይ ሄክታር መሬትም 16 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል። እስካሁን ባሉት እንቅስቃሴዎች በአገር ደረጃ አበረታች ውጤቶች እየታዩ መሆኑን ተናግረዋል።

የመስኖ ስንዴ ልማት በተሠራባቸው አካባቢዎች ላይ የደረሱ ሰብሎችን ከብክነት ለመከላከል እንዲቻል በዘመናዊ የምርት መሰብሰቢያ መሳሪያ በመታገዝ ምርት እየተሰበሰበ መሆኑንም ዶክተር መለሰ ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ እስካሁን ባለው ወቅታዊ መረጃ ከ140 ሺህ በላይ ሄክታር ምርት መሰበሰቡን ዶክተር መለሰ ጠቁመው፤ ከተሰበሰበው አዝመራ ከአራት ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ተገኝቷል ብለዋል።

የምርት አሰባሰብ ሥራውም በተጠናከረ መልኩ በሁሉም የመስኖ ስንዴ አምራች አካባቢዎች ላይ ተጠናክሮ መቀጠሉን ገልጸዋል።

እንደ ዶክተር መለሰ ገለጻ፤ በቀጣይ የመኸር ወቅትም በሰፋፊ የኩታ-ገጠም እርሻዎች ላይ የመስኖ ስንዴ ልማትን በተጠናከረ ሁኔታ በመሥራት ከውጭ የሚገባውን ስንዴ ለማስቀረት እየተሠራ ነው። በኢትዮጵያ በቀጣይ የምርት ዘመን የመስኖ ስንዴ ልማት ባልተስፋፋባቸው አካባቢዎች በስፋት ለማስጀመር እቅድ መያዙንም ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያ ከአራት ዓመት በፊት የተጀመረው የመስኖ ስንዴ ልማት በመጀመሪያው ዓመት በሶስት ሺህ ሄክታር መሬት፣ በሁለተኛው ዙር ደግሞ ወደ 10 ሺህ ሄክታር መሬትና በሶስተኛው ዙር ደግሞ ከ187 ሺህ በላይ ሄክታር መሬት በመስኖ ስንዴ መሸፈን ተችሎ እንደነበር ዶክተር መለሰ አስታውሰዋል።

ተቋሙ ባለፉት ሶስት ተከታታይ ዓመታት ውስጥ የገጠሙትን ተግዳሮቶች በመቅረፍ በቀጣይ የምርጥ ዘር፣ የማዳበሪያ፣ የውሃ ማውጫ ፓምፕ አቅርቦትን በማሻሻል ላይ ይሠራል ያሉት ዶክተር መለሰ፤ ያሉትን የውሃ አማራጮችን በመጠቀምና የአቅም ግንባታ ሥራ በመሥራት ከውጭ የሚገባውን ስንዴ በአገር ውስጥ ምርት ለመተካት እንደሚሠራ ተናግረዋል።



ለአርሶ አደሮች የተሰጡ ዘመናዊ ትራክተሮችን

# የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በጦርነት ከፍተኛ ጉዳት ለደረሰባቸው የወረኢሉ ወረዳ አርሶ አደሮች ድጋፍ አደረገ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በወረኢሉ ወረዳ በጦርነቱ ለተጎዱ በሶስት ቀበሌዎች ለሚገኙ አርሶ አደሮች 100 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ፣ 10 የውኃ መሳቢያ ጀነሬተሮችና አራት መለስተኛ ዘመናዊ ትራክተሮችን ድጋፍ አድርጓል።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንት ዶክተር ዮሐንስ አያሌው እንደገለጹት ወረኢሉ በታሪክ የምናውቀው፣ በአገሩ ክብር የማይደራደር ጀግና ሕዝብ ነው።በቅርቡ በተደረገው የሕልውና ጦርነት ተጋድሎ በማድረግ ተዋግቷል፣ ጀብድም ፈጽሟል ብለዋል።

በወረዳው የደረሰውን ሰብዓዊና ቁሳዊ ጥፋት የከፋ ቢሆንም ማኅበረሰቡ ለሥራ ካለው ጥንካሬና የአካባቢው ሰብል አምራችነትን ታሳቢ በማድረግ ባንኩ ተገቢውን የግብዓትና ቴክኖሎጂ ድጋፍ እያደረገ ወረኢሉን ሞዴል አድርጎ ለማስቀጠል እንደሚሠራ ጠቁመዋል።

የወረኢሉ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ አቶ ሰለሞን አይቸው፣ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ላደረገው ድጋፍ ከፍ ያለ ምስጋና አቅርበዋል። ለመስኖም ሆነ ለመኸር እርሻ ምቹ መሬትና ውኃ ባለው ወረኢሉ ግብርናውን ለማዘመን ልማት ባንክ በጀመረው ሁኔታ የአርሶ አደሩን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ተግተው እንደሚሠሩ ተናግረዋል።

የደቡብ ወሎ ዞን ምክትል አስተዳዳሪ አቶ ተስፋ ዳኛው በበኩላቸው የአካባቢው ሕዝብና አመራር ያገኘውን ዕድል በሚገባ ተጠቅሞ በዘርፉ ስኬታማ ውጤት በማምጣት የባንኩን ጥረትና ድጋፍ በተግባር በማሳየት ለበለጠ ዕድገት እንዲነሳሳ ጥሪ አቅርበዋል።

# በኢትዮጵያና በጎረቤት አገራት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ምንዛሪ የሚገዛውን ነዳጅ በአግባቡ እየሸጠ አይደለም፤ እንዲያውም ለሌሎች መጠቀሚያ እየሆነ ነው።

ኬኒያና ጂቡቲን ከመሳሰሉት ጎረቤት አገራት ጋር እኩል የሆነ የነዳጅ ዋጋ ተመን ቢወጣ የሕገ ወጥ ንግዱ ይቀንሳል ያሉት አቶ ታደሰ፤ በአሁኑ ጊዜ የሚስተዋለው የነዳጅ አቅርቦት እጥረትም ይሻሻላል ሲሉ መክረዋል።

የነዳጅ ዋጋ ላይ ሁልጊዜ ድጎማ በማድረግ ብቻ ጫናውን መቀነስ ስለማይቻል ሌሎች አማራጭ መንገዶችን ሊፈለጉ ይገባል ብለዋል።

መንግሥት ይህን ተግባራዊ ለማድረግ እንደ አቀደና የንግድ ሚኒስቴር የነዳጅ ዋጋ መጨመርን እንደ አንድ አማራጭ ይዞ ስትራቴጂ ቀይሶ እየተንቀሳቀሰ መሆኑ በመልካም እንደሚያዩት ገልፀዋል።

የነዳጅ ዋጋ መጨመር የሸቀጦች ዋጋ ጭማሪ ጋር መያያዝ የለበትም የሚሉት አቶ ታደሰ፤ እያንዳንዱ ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ የሚሸጥበት ሥርዓት ተዘርግቶ ነዳጅ በተገቢው ዋጋ እንዲሸጥ መደረግ እንዳለበት አስገንዝበዋል።

አቅርቦቱን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄም፤ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የቤንዚንም ሆነ ናፍታ የአቅርቦት እጥረት የለም። በየማደያዎቹ ቤንዚንም ሆነ ናፍታ የለም የሚል ተለጥፎ ቢታይም በዚህ ምክንያት የቆመ መኪና ግን አይታይም ሲሉ አብራርተዋል።

ከባለ ሦስት እግር መኪኖች ጀምሮ ትላልቅ ተሽከርካሪዎች ጭምር ነዳጅ ሞልተው ሲንቀሳቀሱ ይታያሉ። ከዚህ ማረጋገጥ የሚቻለው ሕገ ወጥ ንግድ እንዳለ እንጂ የነዳጅ እጥረት እንዳለ አይደለም ብለዋል።

በሌላ በኩል ችግሩን ለመቅረፍ ሕገ ወጥ ነጋዴዎች ላይ ጠንከር ያለ እርምጃ መወሰድ እንዳለበት አመልክተው፤በሌሎች አገራት ከነዳጅ ማደያዎች ውጭ ነዳጅ ሲሸጥ የተገኘ አካል ጠንከር ያለ ቅጣትና ረጅም የእሥር ጊዜ ይጠብቀዋል።በአገራችን ደረጃ ግን በዚህ መልኩ እየተሠራ እንዳልሆነ ተናግረዋል።

ነዳጅን ከማደያ ውጪ መሸጥ የሕገ ወጥ ንግድ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የደህንነት ጉዳይም ጭምር ነው። አሁን እየተነሱ ያሉ የእሳት አደጋዎችንም ከሚባባሱበት ምክንያት አንዱ ይሄው ነው። በተጨማሪም ከነዳጅ ማደያዎች ውጪ የሚሸጥ ነዳጅ የጥራት ጉድለት ስለሚኖረው ተሽከርካሪዎች እንዲጎዱ ያደርጋል ብለዋል።

በአሁኑ ጊዜ ነዳጅ እጥረት ሊፈጥር የሚችል ዓለም አቀፋዊ ሁነት መኖሩንም አቶ ታደሰ አንስተዋል።

በዩክሬን እና ራሽያ ጦርነት ምክንያት የነዳጅ ዋጋ ንረትና የአቅርቦት እጥረት እንዳይፈጠር በሌሎች አገራት በኩል የነዳጅ ቁጠባ ቴክኒኮች መቀመጣቸውን፤ የመኪኖች እንቅስቃሴ እንዲገታና ነዳጅ በኮታ እንዲከፋፈል እየተደረገ መሆኑን ገልፀው በኢትዮጵያ ደረጃ እነዚህ መሰል እንቅስቃሴዎች መጀመር እንዳለባቸው ገልፀዋል።

# ምክር ቤቱ አገራዊ ምክክሩ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የምክክሩ ዋና ትኩረት የአገሪቱን ሰላምና አንድነት ማረጋገጥ ነው ያሉት ሰብሳቢዋ፤ ምክክሩ በአገሪቱ ላይ የተከሰተው ጦርነት አብቅቶ ወደ ሰላም የምንመለስበት፣ የትርክትና የዓርማ ልዩነታችንን የምንፈታበትና የጋራ ታሪክ እንዲኖረንና የጋራ ማንነታችንን በፍቃድና በሰላማዊ አግባብ ተነጋግረን ወደ መፍትሔ እንድንመጣ በሂደቱ ላይ የሚኖረው ግልጽነት ትልቅ ሚና ይጫወታል ብለዋል።

የአገራዊ ምክክሩ ሂደት አካታችና ግልጽ መሆን በሕዝቡና በሌሎችም ባለድርሻ አካላት ዘንድ ቅቡልነትና አመኔታ እንዲያገኝ ትልቅ ሚና ስለሚጫወት በትኩረት ሊሠራበት እንደሚገባ ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት እንደ ምክር ቤትም ሆነ ፖለቲካ ፓርቲዎች ለምክክሩ መሳካት የየበኩላቸውን ድርሻ ይወጣሉ ያሉት ሰብሳቢዋ፤ አገራዊ ምክክሩ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ጉዳይ በመሆኑ ግጭቶችን፣ ጦርነትንና እርስ በርስ አለመግባባትን ሁሉ እንድንፈታበት መሠረታዊ ሆኑ መርሆዎች ሊከበሩ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

የፖለቲካ ፓርቲዎች ምክር ቤት ንቁ ተሳትፎ እያደረገ በሂደቱ ላይ የሚስተዋሉ ሳንካዎችን ለማሳየትና መፍትሔ እንዲያገኙ ለማድረግ እየሠራ መሆኑን ገልጸው፤ በሂደቱ ላይ የሚስተዋሉ ጉድለቶች እየተስተካከሉና ሳንካዎች እየተቀረፉ ወደ ትክክለኛው ሥርዓት ይመጣል የሚል እምነት እንዳላቸው አስረድተዋል።

አገራዊ ምክክሩ የሁላችንም ስለሆነ የማይመለከተው አካል የለም ያሉት ሰብሳቢዋ፤ እንደ አራተኛ መንግሥት የሚታዩት ሚዲያዎችም የሚያስተላልፏቸው ዘገባዎች እውነት የሆኑና ለሕዝብ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ መሥራት አለባቸው። ለሕዝብ የሚያደርሱት ዘገባም ለአገር ግንባታ የሚበጅና ትክክኛ መረጃ መሆኑን መመርመር አለባቸው ብለዋል።

በቀጣይነት በሚሠሩ ሥራዎች ላይ ግልጽነት መፍጠር ሲቻል አመኔታን ስለሚያመጣ በትኩረት ሊታይ ይገባዋል።

# የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

እየተሠሩ እንደሚገኙ ገልጸዋል።

በክልሉ የበጋ መስኖ በተሠሩ ሥራዎች በጣም ጥሩ የሚባል የስንዴ ምርት ይገኛል ተብሎ ስለሚጠበቅ ይህን ተሞክሮውን ለማስፋት እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ ለመጪው የመኸር ምርት ዘመንም ማዳበሪያ ወደ አርሶ አደሩ በወቅቱ እንዲደርስ በማድረግና ሊታረስ የሚችል ማንኛውም መሬት ጾም እንዳያድር እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑን አብራርተዋል።

በፌዴራል እና በክልሉ የሚከናወኑ ሰፋፊ የመሠረተ ልማት ፕሮጀክት ሥራዎች አብዛኞዎቹ በተያዘው ጊዜና የጥራት ደረጃ ያለመፈጸማቸው የማኅበረሰብ እሮሮ ምንጭ እየሆነ የመጣ እንደሆነ ከክልሉ ሕዝብ ጋር በተደረገው ውይይት በስፋት መነሳቱን ያወሱት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ የተጀመሩ የመንገድ፣ ድልድይ፣ ትምህርትና ጤና ተቋማት ግንባታዎች በበጀት እጥረት ቆመው መቅረታቸውን አስታውሰዋል። እነዚህ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች ችግር እየሆኑ ስለመጡ በአስቸኳይ መፈታት አለባቸው በሚል ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው እንደሚሰሩም ተናግረዋል።

ዶክተር ኢንጂነር ነጋሽ ዋጌሾ እንደሚሉት፤ ክልሉ አዲስ እንደመሆኑ የበጀት እጥረት ችግር አለበት። በክልሉ ሕዝብ የተነሱ ጥያቄዎች አንዳንዶቹ በጀት የሚፈልጉ ቢሆንም በውይይት ወቅት የተነሱትን የሰላም፣ የወጣቶች የሥራ እድል ፈጠራ፣ እና የመሠረተ ልማት ጥያቄዎችን ደረጃ በደረጃ አቅም በፈቀደው መጠን ለመፍታት እንቅስቃሴ ተጀምሯል።ከመሠረተ ልማት ጋር ተያይዞ የተጠየቁ ጉዳዮችን የተወሰኑትን በክልሉ አቅም በተያዘው በጀት ዓመት መሠራት የሚችሉትን ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮች በመለየት ወደ ሥራ መገባቱን ተናግረዋል።

ክልሉ አሁን ባለው ሁኔታ ሰላማዊ መሆኑን የተናገሩት መስተዳድሩ ፤ ከአንዳንድ ባህላዊ ጎጂ ልማዶች እና ከግጦሽ መሬቶች ጋር ተያይዘው የሚነሱ ውስን ችግሮች ክልሉ ከሚዋሰነው ደቡብ ሱዳን ድንበር አካባቢ መኖራቸውን ጠቁመዋል ። በክልሉ ከዚህ በፊት ይንቀሳቀሱ የነበሩ አንዳንድ የታጠቁ ኃይሎች ጭምር መሳሪያቸውን በማስረከብ ከሕዝብ ጋር መቀላቀላቸውን ገልጸዋል።

በሸካ ዞን ቴፒ አካባቢ ከሁለት እና ሶስት ዓመት በፊት ችግር እንደነበረ አስታውሰው፣ አሁን ችግሩ ተፈትቶ ፍጹም ሰላማዊ መሆኑን ተናግረዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ቋሚ ኮሚቴ ግምገማ አስፈጻሚውን የሚያነቃ ነው!

ስድስተኛው ዙር የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተለያዩ ቋሚ ኮሚቴዎች ሰሞኑን የተቋማትን የዘጠኝ ወራት የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት እያዳመጡ ናቸው፤ ጉብኝቶችን እያደረጉም ተቋማትና ፕሮጀክቶች ያሉበትን ሁኔታ እየተመለከቱ ይገኛሉ።ይህን ተከትሎም ምክረ ሀሳቦችን፣ አስተያየቶችንና ማሳሰቢያዎችን እየሰጡ ናቸው።ይህ ክትትልና ቁጥጥር የመደበኛ ሥራቸው አካልና ወቅታዊ ተገቢም የተለመደም ነው።

በዚህ ረገድ የ2013ቱ ምርጫ የአንድ ፓርቲ አባላት ብቻ ይሰየሙበት የነበረውን ምክር ቤት ገጽ የቀየረ፤ የተለያዩ ፓርቲዎችና በግል የተወዳደሩም አሸንፈው የምክር ቤት ወንበር አግኝተው የገቡበት ሁኔታ እንዲፈጠር አስችሏል።በዚህም የቀደሙትን ምክር ቤቶች መልክና ይዘት መቀየር ተችሏል።ምክር ቤቱን የሀሳብ ብዝሃነት የሚታይበት በሚያደርግ መልኩ የተሰየመ ከመሆኑ አኳያ ደግሞ በምርጫው ምክር ቤቱ የዜጎች ድምጽ ሁሉ የሚደመጥበት እንዲሆን ይጠበቃል።

ይህ በመሆኑም ምክር ቤቱ እያከናወናቸው ያሉ ተግባራትም ይህንን የሚጠቁሙ ናቸው።የተለያዩ ሀሳቦች የሚንሸራሸሩበት ሞቅ ያለ ክርክር የሚደረግበት ለመሆን በቅቷል።ለበርካታ አመታት ጥርስ አልባ ሲባል ከኖረበት ሁኔታ እየወጣም ነው ማለት ይቻላል።በምክር ቤቱ የሀሳብ ብዝሃነት እየተንጸባረቀ ነው።ይህ ትልቅ ስኬት ነው።ምክንያቱም ሪፖርት አዳምጦ ወይም ጉብኝት አድርጎ አበረታች ሲል የኖረን ምክር ቤት መለወጥ ተችሏል።

ሰሞኑን ፓርላማው የተቋማትን ሪፖርት እያዳመጠ፣ ጉብኝቶችን እያደረገ እየሰጣቸው ያሉ ግብረ መልሶች፣ ምክረ ሀሳቦችና ማሳሰቢያዎች የሚያመለክቱትም ምክር ቤቱ ኃላፊነቱን በሚገባ እየተወጣ መሆኑን ነው።በዚህ ረገድ ያለፉት ምክር ቤቶች ጠያቂ አልነበሩም፤ ጠያቂ ከነበሩም ለመጠየቅ ያህል ነበር።በመሆኑም ምክር ቤቱ የሀሳብ ብዝሃነት የጠማው፣ የእከከኝ ልከክልህ ቤት ነበር ማለት ይቻላል።ያሳለፍነው ዘመን የሀሰት መረጃዎች፣ ሀሰተኛ ሪፖርቶች ይፈበረኩ የነበረውም ለዚህ ነው።አገራችን በሀሰተኛ መረጃ ሳቢያ ለገባችበት ጣጣ አንዱ ምክንያትም ይኸው የተቆጣጣሪና ክትትል አድራጊ ነው ማለት ይቻላል።

አሁን ያ ሁኔታ ሊቀየር እንደሚችል ፍንጭ የሚሰጡ የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎች እየታዩ መጥተዋል።የምክር ቤቱ አባላት በሚቀርቡላቸው ሪፖርቶች እንዲሁም በሚያደርጓቸው ጉብኝቶች ወቅት የሚሰጧቸው አስተያየቶችና ማሳሰቢያዎች ሲታዩ ምክር ቤቱ ኃላፊነቱን እየተወጣ፣ ተቋማትም ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ለማድረግ እየሠራ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ይህ ለውጥ እንዲመጣ ይጠበቅ ነበርናም አጀማመሩን ማድነቅ ይገባል።

ይህ መልካም ጅምር እንደተጠበቀ ሆኖ ግን ምክር ቤቱ ሊያጠናቸው የሚገቡ ጉዳዮች አሉ።አንዳንድ ባለስልጣናት አሁንም የአፈጻጸም ሪፖርቱን ገልብጠው ማቅረባቸውን ቀጥለዋል የሚሉ መረጃዎች ይሰማሉ።በቀጣይም እያንዳንዱን ሪፖርት በተለያዩ መንገዶች እየመረመረ ችግሩ በየትኛውም ተቋም እንዳይደግም የሚያደርግ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል።

ከመጣንበት መንገድ አኳያ ሲታይ የሀሰት ሪፖርት የሚያቀርቡ፣ የቀድሞ ሪፖርት ገልብጠው የተከበረው ምክር ቤት የሚሉት ምክር ቤት ፊት የሚያቀርቡ “ባለቤቷን የተማመነች በግ ላቷን ደጅ ታሳድራለች» እንዲሉ ደፋሮች የነበሩባት አገር ነች።አሁንም ይህ አይፈጸምም ተብሎ አይታሰብም።በኖሩበት በመጡበት መንገድ መሄድ የሚፈልጉ ደፋር ባለስልጣናት አይጠፉም።ሪፖርት ከማዳመጥ በተጨማሪ ድንገተኛ ጉብኝት ማድረግን የመሳሰሉ የተለያዩ የመከታተያ መንገዶችን መጠቀምም ያስፈልጋል።

ኃላፊነታቸውን መወጣት ያልቻሉ የተቋም ኃላፊዎች ሲያጠፉ ተው ማለት፤ እንደ ጥፋታቸው ልክ ተግሳጽ ከመስጠት አንስቶ እስከማንሳት የዘለቀ እርምጃ መውሰድም ያስፈልጋል። ይህ እርምጃ አስተማሪ ሊሆን በሚችል መልኩ መፈጸም ይኖርበታል።እርምጃውም ሕዝብ እንዲያውቀው በመገናኛ ብዙኃን ጭምር መገለጽ ይኖርበታል።

ይህ ሲሆን የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓቱን መልካም አድርጎ የጀመረው ምክር ቤቱ ቀጣይ የሚጠብቁትን ከፍ ያሉ ሥራዎች የሚወጣበትን አቅምም፣ ልምድም ይፈጥሩለታል።በዚህች አገር የመንግሥት ተቋማት ብዙ ውጥንቅጦች በወጉ ለመገንዘብና ለመፍትሄያቸው አጋዥ ለመሆን እድል ይሰጠዋል።ለዚህ ደግሞ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየወጡ ያሉ ሀሰተኛ ሰነድን የተመለከቱ መረጃዎች የምክር ቤቱን ሥራዎች ጠንካራ እንደሚያደርጉት ይጠበቃል።

የምክር ቤቱ የተለያዩ ቋሚ ኮሚቴዎች የተቋማት የእቅድ አፈጻጸም ግምገማ ውጤት ለሕዝብ እንዲደርስ መደረግ ይኖርበታል።ምክር ቤቱ የሚያደርጋቸው ዝግ ስብሰባዎችን ሳይጨምር በሩብ አመት፣ በመንፈቅ፣ በዘጠኝ ወር እና በአመቱ የአፈጻጸም ሪፖርት ግምገማ ወቅት መገናኛ ብዙኃን እንዲገኙ ማድረግ ይገባል።በግምገማው ብዙ ሊወጡ የሚችሉ ችግሮች፣ የመፍትሄ ሀሳቦች እንደሚኖሩ ታውቆ የግምገማው ሂደት ለሁሉም የመገናኛ ብዙኃን ክፍት መደረግ ይኖርበታል።በዚህም የምክር ቤቱን መለወጥ የሚያሳዩ ብዙ መረጃዎችን ለሕዝብ ማድረስ ይቻላል።

ተቋማትም ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ያደርጋቸዋል።ሀሰተኛ መረጃ ይዘው የተከበረው ምክር ቤት ፊት ቀርበው ከመዋረድ ይድናሉ።ምክር ቤት ሲቀርቡም ስለሚሄዱበት ጉዳይ በሚገባ አውቀውና ተረድተው መሆኑን እንዲረዱ ያስችላል።ቀጣዩ ሥራቸውን በሚገባ እንዲያከናወኑ የሚያስችሉ ምክረ ሀሳቦችን፣ አስተያየቶችንና ማሳሰቢያዎችን ሊያገኙ ይችላሉ።

ገና አሁን ጥርስ ያወጣው ይህ ምክር ቤት በዚህ ደረጃ እያሳየ ያለው ክትትልና ቁጥጥር ይበልጥ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ለማድረግ ራሱንም እየፈተሸና እያበቃ መሄድ ይኖርበታል።የራሱንም የተቋማትንም ገመና እየፈተሸ እቅዶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት እንዲፈጸሙ ሪፖርቶች በወቅቱ እንዲደርሱና እንዲታዩ ተቋማትን የሚገነቡ ግብረ መልሶችም እንዲሰጡ አበክሮ መስራት ይኖርበታል።በአጠቃላይ ምክር ቤቱ ሁሉንምም አበረታች ከማለት ወጥቶ ደከም ያሉትን ወደ መሸንቆጥ መግባቱ ይበል የሚያሰኝ ነው!


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## ከለውጥ ማግስት ከሚፈጠሩ ችግሮች ተምረን አገራችንን ከጥፋት እንታደግ

**ሙሉቀን ታደገ**

ከለውጥ ማግስት በተለያዩ ኃይሎች መካከል መከፋፈል እና ግጭት እንደሚኖር የተለያዩ አገራት ተሞክሮዎች ያመላክታሉ። የዓለም አገራት ተሞክሮ እንደሚያሳየው የለውጥ ኃይሎች የሕዝብን ድጋፍ እስካገኙ ድረስ ለውጥን ለማምጣት ብዙም ሲከብዳቸው አይታይም። ችግሩ ከለውጡ ማግስት ያለውን የለውጥ ሂደት ለውጡ ከተያዘለት ግብ እና አላማ አኳያ በትክክለኛው ጎዳና እንዴት ማስቀጠል ይቻላል? የሚለው ላይ ነው። ይህን ሃሳብ ለማጠናከር ከበርካታ አገራት የለውጥ ታሪኮች መካከል የራሽያ እና አሜሪካን ታሪክ በወፍ በረር ማየቱ ተገቢ ነው።

አሜሪካውያን ነፃነታቸውን ለማግኘት ተዋድቀው ነፃነታቸውን ከተቀናጁ በኋላ ለአሜሪካ ነፃነት ከፍተኛ ዋጋ የከፈሉ ኃይሎች ከነፃነት እና ከለውጥ በኋላ አገሪቱ ያገኘችውን ነፃነት፤ እንዲሁም የፖለቲካል ኢኮኖሚ አካሄድ ለውጥ ማስቀጠል ተስኗቸው ከፍተኛ ውድመትን ያስከተለ ጦርነት ማካሄዳቸውን የታሪክ ድርሳናት ያመላክታሉ።

አሜሪካውያን የብሪታኒያን የቅኝ ግዛት ሴራ በመበጣጠስ ከብዙ መስዋዕትነት በኋላ ነፃነታቸውን ማግኘት የቻሉ ቢሆንም፤ ከነፃታቸው ማግስት ግን የቅኝ ገዥዎችን ሴራ መበጣጠስ የቻሉት ኃይላት ሰሜን ምዕራብ እና ደቡብ ተብለው ለሁለት ተከፍሉ። የመከፋፈላቸውም መነሻ ምክንያቶች በርካታ ቢሆኑም ዋና ዋነዎቹ ግን ሁለት ናቸው። አንደኛው ኢኮኖሚ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ፖለቲካ ነበር።

ኢኮኖሚያዊ ምክንያቱ፣ የደቡቡ የአሜሪካ ክፍል ባርነት በአገረ አሜሪካ እንዲቀጥል ይፈልጉ ነበር። ደቡብ አሜሪካዎች ይህን እንዲሉ ያስቻለው ዋና ምክንያት የደቡብ አሜሪካ ኢኮኖሚ በግብርና ላይ የተንጠለጠለ እና ኢኮኖሚያቸው በግብርና ላይ መመስረቱ ከፍተኛ የባሪያ ጉልበት እንዲፈልጉ አድርጓቸው ነበር። በመሆኑም ባርነት በአገረ አሜሪካ መቀጠል አለበት ሲሉ ተደመጡ። በአሜሪካ የሰሜኑ ክፍል ደግሞ ኢንዱስትሪዎች ተስፋፍተው ስለነበር የሰው ኃይልን በማሽን መተካት ችለው ነበር። በመሆኑም ሰሜኖቹ ባርነት በአገረ አሜሪካ መኖር የለበትም ሲሉ የደቡቡን የአሜሪካ ኃይሎች መሞገታቸው ነው።

ሌላው ልዩነታቸው ፖለቲካ ነበር። ከዚህ አንጻር የደቡቡ የአሜሪካ ክፍል አሜሪካ በተሻለ መንገድ ለማስቀጠል ኮንፌደራላዊ የመንግሥት አወቃቀር ይሻላታል የሚል ሲሆን፤ የሰሜኑ አሜሪካ ክፍል ደግሞ አሜሪካን ማሻገር የሚችለው ሁሉንም የአሜሪካ ግዛቶች ማዋሃድ ሲቻል እንጂ በኮንፌደራላዊ የመንግሥት አወቃቀር አይደለም ሲሉ በጽኑ ሞገቱ። ይህም ልዩነታቸው አሜሪካኖችን እጅግ ለከፋ እና አውዳሚ ጦርነት ዳረጋቸው። በጦርነቱም በንግግር መፍታት ያልቻሏቸውን የለውጥ ጋሬጣዎች መንጥረው እና አስተካክለው አዲስ እና ኃያል የሆነችን ዩናይትድ ስቴስ ኦፍ አሜሪካ የተባለችን አገር መሠረቱ። አገራቸውንም አሁን ላለችበት የዓለም ቁጥር አንድ ልዕለ ኃያልነት ደረጃ አበቁ።

ሌላው ከለውጥ ማግስት ግጭቶች እንደሚከሰቱ ሁነኛ የዓለም ተሞክሮ የታየው በራሽያ ነው። በራሽያ የሮማኖቭ ሥርወ-መንግሥትን በመገርሰስ ራሽያን ለለውጥ ካበቁ ቡድኖች መካከል የራሽያ ሶሻል ዴሞክራሲቲክ ሌቨር ፓርቲ አንዱ ነበር። ይህ ፓርቲ ከለውጡ በኋላ ለውጡን በተፈለገው ልክ ማስቀጠል ተስኖት ቦልሼቪክ እና ሜንሼቪክ ተብሎ ለሁለት ተሰንጥቆ አረፈው። በዚህ ወቅት ቦልሼቪኮች ለለውጡ ምክንያት የሆኑ መነሻዎችን ዘንግተዋል፤ ለላባደሩ እና ለአርሶ አደሩ መወገን ሲገባቸው ለቡርዣው በመወገን ለውጡን ሊያደናቅፉት ነው ሲሉ ሜንሼቪኮችን ይከሱ ነበር። ሜንሼቪኮችም አርሶ አደሩን እና ወዛደሩን እንደ ለውጥ መዘወሪያ ኃይል መጠቀም ከአብዮቱ በፊት አንግበን የተነሳንለትን አላማ ለማሳካት የሚያስችል አይደለም በማለት ቦልሼቪኮችን ይከሱ ነበር። የኋላ ኋላ ቦልሼቪኮች ሜንሼቪኮችን የለውጡ ደንቃራ አድርገው ለሕዝብ አሳዩ። ሜንሼቪኮችም በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት አጡ። ቦልሼቪኮችም መሄድ ባለባቸው ቦታዎች ሁሉ ተጉዘው ራሽያን ለዚህ ክብር አበቁ።

እዚህ ላይ የምንረዳው ነገር የተለያዩ አገራት ከለውጥ ማግስት ለውጥ ያመጡ ኃይሎቻቸው የእርስ በርስ ግጭት ውስጥ እንደሚገቡ ነው። ከለውጥ በኋላ ለሚከሰቱ የግጭት መንስኤዎች በአብዛኛው ጊዜ በሁለት ናቸው።አንደኛው፣ ትክክለኛውን የለውጡን አላማ ለማስቀጠል ከሚመጣ ፍላጎት ሲሆን፤ ሁለተኛው፣ ደግሞ የለውጡ አካላት የሆኑ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ከለውጡ በኋላ እናገኘዋለን ብለው ያቀዱት ሁለንተናዊ ጥቅም በሆነ ምክንያት የሚያጡት መስሎ ሲሰማቸው የሚፈጠር ነው። ከላይ ከተጠቀሱ አገራት ተሞክሮ እንደተረዳነው ከለውጥ ማግስት በለውጥ አምጪዎች መካከል የሚፈጠረው አለመግባባት ከሁለቱ ምክንያቶች የመነጨ ነው።

በእኛም አገር በ1966 ዓ.ም፣ በ1983 ዓ.ም እና በ2010 ዓ.ም ለሦስት ጊዜያት አስተዳደራዊ ለውጥ ቢደረጉም ከላይ እንደተጠቀሱት አገራት ከለውጥ ማግስት የሚነሱ ጥያቄዎች መፍታት አቅቶን እስካሁን ድረስ እየተነታረክን እንገኛለን። ሆኖም የእኛ ችግር ከላይ በማሳያነት ካቀረብናቸው አገራት በእጅጉ ይለያል። ምክንያቱም ከላይ የተጠቀሱት አገራት ከለውጥ ማግስት ለጸብ ያመሯቸውን አጀንዳዎቻ የፈጠሯቸው ራሳቸው ሲሆኑ፤ በእኛ አገር ግን ከለውጥ ማግስት ለሚፈጠሩ የጸብ መነሻ የሆኑ አጀንዳዎችን የምንቀበለው ኢትዮጵያን ጠል ከሆኑ አገራት እና ቡድኖች በመሆኑ ነው።

ይህን ስል በአመክንዮ እንጂ እንዲሁ በግብዝነት ላለመሆኑ በርካታ አመክንዮችን ማቅረብ ቢቻልም ለዛሬው ግን ሁለት ማሳያዎችን እነሆ ብያለሁ።

አንደኛ፣ በ1966 ዓ.ም የመጣው አብዮታዊ ለውጥ የእውነተኛ ለውጥ እና ኢትዮጵያን ሊቀይር የሚችል የነበረ ቢሆንም አወቅን እና ተማርን የሚሉ ኃይሎች ኢትዮጵያን ለማጥፋት ሌት ከቀን ከሚታትሩ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ተልዕኮ በመቀበል የኢትዮጵያን ጦር በግንባር እስከመፋለም የደረሱ እና የኢትዮጵያ እንደ አገር የመቀጠል ህልውናዋን አደጋ ውስጥ የጨመሩበት ነበር። ሕወሓት እና መሰሎቹ ለዚህ ሁነኛ ማሳያ ናቸው።

እነኝህ ኃይሎች ከለውጡ መንግሥት ጋር ያደረጉት ግብግብ የኢትዮጵያን የባህር በር ያሳጣ እና አገረ መንግሥቱንም አደጋ ውስጥ የጨመሩ ነበሩ። እዚህ ጋ የብርጋዴል ጄኔራል ተሾመ ተሰማን ሃሳብ ልዋስ፤ እንደሚታወቀው አንድ ቤት ሲሠራ በርም መስኮትም ይሠራለታል። ለመቃብር ቤት ግን በርም መስኮትም አያስፈልገውም። ባህር በር የሌለው አገርም መስኮት እና በር የሌለው ቤት ነው። ይህ ማለት መቃብር ውስጥ ያለች አገር ናት።

ኢትዮጵያን ያለ ባህር በር ያስቀሯት የለውጥ ደንቃራዎች ወይም ጋሬጣዎች የውጭ ተላላኪዎች ሕወሓት እና መሰሎቹ ነበሩ። እነኝህ አካላት ለውጡን ሲያደናቅፉ እና የኢትዮጵያን አገረ መንግሥትነት ጥያቄ ውስጥ ሲጨምሩ አገር የማተራመስ አጀንዳውን የፈጠሩት በራሳቸው ሳይሆን ኢትዮጵያን ከሚጠሉ ምዕራባውያን አገራት ነበር። በዚህም በ1966 ዓ.ም የተፈጠረው አብዮት ወይም ለውጥ አብዮትነቱ ሳይታወቅ እስከ 2010 ዓ.ም አደረሰን።

ሁለተኛ፣ በ2010 ዓ.ም የመጣውን ለውጥ ተከትሎ፣ ቀድሞ የተሠራበት እና በዚህ ወቅት ጎልተው እንዲወጡ የተደረገባቸው በተለያዩ ቦታዎች ማንነትን መሠረት ያደረጉ ግጭቶች በመስፋፋታቸው ኢትዮጵያ ለአራት ዓመታት በአስቸጋሪ የለውጥ ጉዞ ውስጥ እንድትጓዝ ተፈረደባት። ለዚህም ዋናው ምክንያት በተፎካካሪ ፓርቲዎችም ሆነ በገዥው መንግሥት ውስጥ የሚገኙ አካላት ኢትዮጵያን ከሚጠሉ አካላት አጀንዳ ወስደው ስለሚንቀሳቀሱ ነው። በዚህም በመዋቅሩ ውስጥም ሆነ ከመዋቅሩ ውጪ ባሉ ኃይሎች በመታገዝ ጭምር አገር የመገንጠል አጀንዳ፣ የሽግግር መንግሥት የመመስረት አጀንዳ፣ ከመስከረም 30 ቀን 2011 ዓ.ም በኋላ መንግሥት የለም የሚል አጀንዳ፣ ወዘተ. ከውጭ ኃይሎች እየተቀበሉ አገርን ለትርምስና ጦርነት በመዳረግ እረፍት የመንሳት፣ የማዋከብና ሕዝቡ ተረጋግቶ ሳያስብ ለውጡ ወዳልተፈለገ አቅጣጫ እንዲያመራ ለማድረግ ሲሠሩ ቆይተዋል፤ እየሠሩም ናቸው።

ይህ ሁሉ የሚሆነው ደግሞ የኢትዮጵያን እድገት እንደ ስጋት የሚመለከቱ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች አማካኝነት ነው። እነሱ ውጭ ሆነው እኛ የእነሱን ጦርነት ተረክበን ስንዋጋ፤ ከጉዞችን ስንስተጓጎል፤ እነሱ ይሳለቁብናል። ስለሆነም የተጀመረውን ለውጥ ለማስቀጠል ከተፈለገ ሳይቃጠል በቅጠል ነውና ገዥው መንግሥት በሥሩ ያሉ ባንዳ ተላላኪዎችን ከመዋቅሩ ያስወጣ፣ በተፎካካሪ ፓርቲ ስም የጠላትን አጀንዳ አዝለው አገር ለማተራመስ የሚንቀሳቀሱ ኃይሎችም አደብ ይያዙ፤ ሕዝብም እንደ ሕዝብ ሰከን ብሎ የሚሆነውን በማስተዋል ማጤን ይኖርበታል። ሰው ከራሱም ከጎረቤቱም ይማራልና፤ ሌላ ለውጥ ሳንጠብቅ በዚህኛው ልንጠቀም፣ ከለውጥ ማግስት ከሚፈጠሩ ችግሮችም አገራችንን ልንታደግ ይገባል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## እየጦፈ የመጣው ዓለም አቀፍ የእጅ ቦርሳ ገበያ

**አቤል ገ/ኪዳን**

የእጅ ቦርሳ ሴት ልጅ ሊኖራት ይገባል ተብለው ከሚታሰቡ ቁሳቁስ መካከል አንዱ እና ዋነኛው ነው። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ሴት ልጅ በምትንቀሳቀስበት ጊዜ ከእጇ ሊታጣቸው የማይገቡ አንዳንድ መሠረታዊ ግብአቶች በመኖራቸው እና እነዚያን ነገሮች በአንድ ላይ ለመያዝ ቦርሳው አስፈላጊ ስለሆነ ነው።

ከዚህም ያለፈ ፋይዳ አለው። የእጅ ቦርሳ ለሴት ልጅ ውበት መጉላት አስተዋጽኦ ከሚያደርጉ የፋሽን ቁሳቁስ መካከልም አንዱ ነው። ለዚህም ይመስላል አንዳንድ ሴቶች ቦርሳ ለመያዝ የሚያበቃ ምክንያት ባይኖራቸውም እንኳ እንዲሁ ባዶ ቦርሳውን አንጠልጥለው ይወጣሉ የሚባሉት። የሆነ ሆኖ የእጅ ቦርሳ ለሴት ልጅ አስፈላጊ ነው።

ይህን ሀቅ ከያዝን በኋላ በአሁኑ ወቅት በዓለም ደረጃ ያለው የእጅ ቦርሳ ገበያ ምን ላይ ነው እኛስ እንደ አገር ምን ልንጠቀም እንችላለን የሚለውን መቃኘት የዛሬው ርእሳችን ይሆናል።

መረጃዎች እንደሚያመላክቱት፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ የእጅ ቦርሳ ገበያ በቢሊየኖች ዶላር የሚቆጠር ገንዘብ በአመት የሚንቀሳቀስበት ገበያ ነው። ፎርቹን ቢዝነስ ኢንሳይድ የተባለ ድረ ገጽ በዚህ ጉዳይ ላይ ባሰፈረው መረጃ መሠረት የእጅ ቦርሳ ገበያ በፈረንጆቹ 2020 ብቻ 47 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር ገቢ የተገኘበት ገበያ ነው። ይህ ገቢ ከኮሮና ወረርሽኝ መከሰት ጋር በተያያዘ ከፍተኛ መቀነስ አጋጥሞት የነበረ ሲሆን፣ ይህን የገበያ መቀነስ በቁጥር ሲያስቀምጡትም የእጅ ቦርሳ ገበያ በዓለም ደረጃ እስከ 25 በመቶ ማሽቆልቆል አጋጥሞት እንደነበር ይገልጻሉ። ብዙዎች ከቤት እንዳይወጡ መከልከላቸው ነው ለገበያ ማሽቆልቆሉ መንስኤው።

ከወረርሽኙ መቀነስ በኋላ ግን አሁን ላይ የቦርሳ ገበያው መልሶ መነቃቃት ማሳየት ብቻ ሳይሆን፣ እድገትም እየተመዘገበበት ነው። ድረ ገጽ ትንበያዎችን አመሳክሮ እንደገለጸው ከሆነ ከ2021 እስከ 2028 ባሉት 7 አመታት የእጅ ቦርሳ ገበያ በአመት 6 ነጥብ 7 በመቶ ገደማ እድገት በማስመዝገብ በ2028 እ.ኤ.አ በአመት 78 ነጥብ 4



**የእጅ ቦርሳ ገበያ በፈረንጆቹ 2020 ብቻ 47 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር ገቢ የተገኘበት ገበያ ነው**

ቢሊዮን ዶላር ገቢ የሚያስገኝ ዘርፍ ይሆናል። ይህም በ2019 እ.ኤ.አ ብቻ በዓለም ደረጃ 1 ነጥብ 3 ትሪሊዮን ከሚያስገባው እና ከ300 ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ሰዎች የሥራ ዕድል ከፈጠረው እና አሁንም ከፍተኛ እድገት እያስመዘገበ ያለው የፋሽን ዘርፍ አካል ነው።

ለመሆኑ የእጅ ቦርሳ ገበያ እንዲህ እንዲጦፍ ያደረገው ምክንያት ምንድን ነው የተባለ እንደሆነ ዋነኛው ምክንያት ሴቶች ከቤት እመቤትነት ወደ ቢሮ ሠራተኝነት እየተቀየሩ መምጣታቸው ነው። መረጃዎቹ እንደሚሉት፤ በአህጉር ከአገር አገር ቁጥሩ ቢለያይም የሴቶች የትምህርት ተደራሽነት በዓለም አቀፍ ደረጃ ከ80 በመቶ ልቋል። የዓለም ሥራ ድርጅት እንደሚለው ከሆነ ደግሞ በ2018 እ.ኤ.አ ብቻ ከጠቅላላው ሴቶች 48 በመቶው ከቤት እመቤትነት ወጥተው ሠራተኛ ሆነዋል። የዓለም ሴቶች በ2019 እ.ኤ.አ ብቻ አመታዊ ወጪያቸው ወደ 31 ትሪሊዮን ዶላር ገደማ ደርሷል።

እነዚህ ቁጥሮች በሙሉ የሚያመለክቱት ነገር ቢኖር የእጅ ቦርሳ ገበያ ገና እየጦፈ እንደሚሄድ ነው። ይህንን የተረዱ አገራትም ከዚህ ገበያ የድርሻቸውን ለመውሰድ ከፍተኛ ርብርብ እያካሄዱ እና አዳዲስ ፈጠራዎችን እየጨመሩ ነው። ከፈጠራዎቹ መካከል ቦርሳዎቹ የስልክ ቻርጀር እንዲኖራቸው ማድረግ፤ ውሀን መቋቋም እንዲችሉ ማድረግ እና መሰል ፈጠራዎች እየተጨመሩ ሄደዋል። በእጅ ቦርሳ ገበያው ላይ በተለይ ዋነኞቹ የቦርሳ ዓይነቶች ካርመን ቶቴ፤ ክላች እና ሳቸል የሚባሉ ሲሆን የመጀመሪዎቹ ሁለቱ በተለይ በሴቶች እጅጉን የሚዘወተሩ ናቸው።

ወደ እኛ አገር ስንመጣ የእጅ ቦርሳም እንደሌሎች ግብአቶች በአብዛኛው ከውጭ በሸመታ የሚመጣ ሲሆን፣ ይህም የአገሪቱን የውጭ ምንዛሬ ከሚፈታተኑ በርካታ የቅንጦት ግብይቶች መካከል ዋነኛው እንዲሆን ያደርገዋል። ነገር ግን ኢትዮጵያ ከፍተኛ የቆዳ ምርት ጸጋ ያላት አገር ከመሆኗ አንጻር በዚህ ዘርፍ ብትሠራ ብዙ ልታተርፍ የምትችል አገር ነበረች። ለዚህም ማሳያ የሚሆኑ ምልክቶች አሉ።

ኢቢሲ በአንድ ወቅት ይዞት የወጣ መረጃ እንደሚያመልከተው፣ ከሁለት አመት በፊት ውቅሮ የሚገኘው ሼባ ሌዘር ኢንዱስትሪ የሴቶች የእጅ ቦርሳን አምርቶ ወደ አሜሪካ ገበያ መላክ ጀምሮ ነበር። በዚህም በአመት 3 ሚሊዮን ዶላር በመጀመሪያው አመት ለማግኘት ችሎ ነበር። እንደ አገር ያኔ በነበረው የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ በአምስት አመት ውስጥ ከቆዳ እና ሌጦ ዘርፉ ከ700 ሚሊዮን እስከ 1 ቢሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ የነበረ ሲሆን፣ ከቦርሳ እና መሰል ንግድ ማግኘት የተቻለው ግን ከ2 ሚሊዮን ዶላር በታች ብቻ ነበር።

አንድ ፋብሪካ ግን ለብቻው በቀን 300 መቶ በአመት ደግሞ ወደ መቶ ሺ ገደማ በማምረት 3 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት ዝግጅቱን ጨርሶ ነበር። ይህን ገቢም በ5ኛው አመት ወደ 1 ሚሊዮን ቦርሳ ምርት አሳድጎ 25 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት ነበር የታለመው።

ይህ የሚያመለክተው ዘርፉ ከተሠራበት በዓለም ደረጃ የገበያ እጥረት እንደሌለ እና አማራጭ የውጭ ምንዛሬ ማግኛ ስልት እንደሚሆን ነው። አሁን ያለነው ገና እአአ 2022 ላይ ነው። በዚህ ወቅት የእጅ ቦርሳ ገበያው በዓለም ደረጃ አመታዊ ገቢው ወደ 50 ቢሊዮን ዶላር የተጠጋ ነው። ይህ አሀዝ በቀጣይ የት እንደሚደርስ ቀደም ብለን በጠቀስናቸው የቁጥር ማስረጃዎች ላይ ተመልክተናል። ስለዚህም ገበያው ከፊታችን ነው። ጥሬ ዕቃውም በእጃችን ነው። ከእኛ የሚጠበቀው ዓለምአቀፉን የጥራት ደረጃ በሚመጥን መልኩ made in Ethiopia የሆኑ ቦርሳዎችን አምርቶ መግባት ብቻ ነው። ያን ለማድረግ ማን ይከለክለናል?

ለማንኛውም የዛሬውን ጽሑፋችንን ዝነኛው ተዋናይ ቢሊ ኮነሊ ስለ ሴቶች እና ቦርሳዎች በሰጠው አስተያየት እናጠቃልላለን፡-«የሴት ልጅ አእምሮ እንደ እጅ ቦርሳዋ ውስብስብ ነው። የቦርሳዋ የመጨረሻ ወለል ላይ ደርሰህ እንኳ አንድ የሆነ የሚያስገርም ነገር ማግኘትህ አይቀርም» ከዚህም ቦርሳ ለሴቶች የግድ መሆኑን ያስረዳል።

# ማረፊያ/ትዝብት

## የሀሰተኞች አገር እንዳንሆን

**አቤል ገ/ኪዳን**

ከቀናት በፊት ነው፤ ቤት ቁጭ ብዬ ስልኬን እየጎረጎርኩ ነበር። ቤተሰቦቼ ደግሞ ቴሌቪዥን ከፍተው ፊልም እያዩ። ተከታታይ ድራማዎችን የሚያሳየው ቃና ቴሌቪዥን በሚያሳያቸው ፊልሞች መሀል አጭር ዜና ያቀርባል። ዜናው መነበብ ጀመረ።

ዜናው የትምህርት ሚኒስቴር የዘጠኝ ወራት የአፈጻጸም ሪፖርትን የተመለከተ ነው። በዘገባው መሠረት ባለፉት 9 ወራት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከ80 በላይ በሚሆኑ ተቋማት የቀረበለትን የትምህርት ማስረጃ አጣሩልን ጥያቄ ተቀብሎ ባደረገው ማጣራት ከ7ሺ459 የይጣራልን ጥያቄዎች 504ቱ ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ መሆናቸውን እንደደረሰበት ይገልጻል፤ አስደንጋጭ ነው።

የበለጠው አስደንጋጭ ነገር ግን ሚኒስትሮቹ ቀጥለው የተናገሩት ነው። በመቶ ሺዎች የሚቆጠር መሰብሰብ ያለበት የትምህርት ማስረጃ አለ፤ ከክልል ካቢኔ አንስቶ እስከ ወረዳ ካቢኔ አባላት መሰል ሀሰተኛ ማስረጃ ይጠቀማሉ፤ ነገር ግን ይህን ለማጣራት መሞከር ከባድ ነው፤ ምክንያቱም ፖሊስ እና ዳኞችን ጨምሮ በዚህ ውንብድና ውስጥ እየተሳተፉ ስለሆነ ነው አሉ።

ይህ አስደንጋጭም አሳሳቢም ነው። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ በዚያኑ ሰሞን የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ሀሰተኛ ማስረጃዎች መብዛታቸው ሥራዬን ከባድ አድርጎታል የሚል አቤቱታ ለጉብኝት ለመጡት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕግ፣ ፍትህና ዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት አስገንዝበዋል። ባለፉት ስድስት ወራት ብቻ 231 ሀሰተኛ የሰነድ ማስረጃዎችን መያዛቸውን ገልጸው፣ 152ቱ ሀሰተኛ መታወቂያ፣ 26 ከመቶ የሚሆነው ደግሞ ያላገባ ማስረጃ መሆኑን አብራርተዋል፤ ሀሰተኛ የቦታ ካርታም እንዲሁ እየተበራከተ መሆኑን ገልጸዋል።

> **ምጸታዊ የሚሆነው ነገር ግን ይሄ ብቻ አይደለም። በሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ቁጭ ብሎ የሚፈርደው ሰው ሌላ ቦታ ሲሄድ ልክ እንደሱ በሀሰተኛ ሰነድ ስልጣን ላይ ቁጭ ባለ ሌላ ወንጀለኛ ሲወሰንበት ማየቱ ነው**

ሀሰተኛ ዲግሪ፣ ሀሰተኛ ማስተርስ፣ ሀሰተኛ የጋብቻ ወረቀት፣ ሀሰተኛ የቤት ካርታ፣ ሀሰተኛ መታወቂያ፣ ሀሰተኛ መንጃ ፈቃድ፣ ሀሰተኛ ሀሰተኛ.... ። ይህ በአንድ ጎን አገሪቱ ባለፉት ጥቂት አስርት አመታት ያፈራችው ትውልድ የገጠመውን የሞራል ቀውስ የሚያመለክት ነው። በሌላ ጎን በዚህ የሞራል ቀውስ ውስጥ የተዘፈቁ ሰዎች ዛሬ ወንበር መያዛቸውንም ያመለክታል።

የትምህርት ሚኒስቴር ሹማምንት እንደ ነገሩን ከሆነ ባለ ሀሰተኛ ሰነዶቹ ሰዎች በተለያየ የመንግሥት እርከን ላይ ስልጣን ይዘው ተቀምጠዋል። ውሳኔም እያሳለፉ ነው። 10ኛ ክፍል ላይ የፎረሸ ሰው በሀሰተኛ ዲግሪ እውነተኛ ዲግሪ ያላቸውን ሰዎች ሲመራ እና በሕዝብ ላይ በጨበጣ ውሳኔ ሲያሳልፍ ማሰብ በእጅጉ ያማል።

ምጸታዊ የሚሆነው ነገር ግን ይሄ ብቻ አይደለም። በሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ቁጭ ብሎ የሚፈርደው ሰው ሌላ ቦታ ሲሄድ ልክ እንደሱ በሀሰተኛ ሰነድ ስልጣን ላይ ቁጭ ባለ ሌላ ወንጀለኛ ሲወሰንበት ማየቱ ነው። አስቡት ደግሞ ሀሰተኛ መታወቂያ ወይም የጋብቻ የምስክር ወረቀት የያዘ ሰው ከእነዚሁ ወሮበሎች ጋር መጥቶ ሲስተናገድ። ከዚያም እነዚህ ሦስት አካላት ሀሰተኛ መንጃ ፈቃድ ባለው ሹፌር ታክሲ ውስጥ ተሳፍረው ሲሄዱ አሰላስሉት። አስፈሪ ነው። አሳዛኙ ነገር በዚህ ሁሉ መሀል ከአንዱ ባለ ሀሰተኛ ዲግሪ ባለስልጣን ወደ ሌላው አጭበርባሪ ለውሳኔ ሲንከራተት የሚኖረው ሰላማዊ ሕዝብ ነው። ለዚህ ሕዝብ ይህ አይገባውም።

እንደ አገር መበልጸግ አላማችን ነው ተብሎ መንገድ ተይዟል። ሀሳቡ መልካም ነው። ነገር ግን ሀሰተኛ ሰነዶች በየቀኑ በገፍ በሚመረትባት አገር ብልጽግና በየት በኩል ይመጣል? ስልጣኔ እና ብልጽግና በፈጠራ አቅም ላይ የተመሠረተ ነው። የአሜሪካ እና የሌሎች ታላላቅ አገራት ስልጣኔ በዚህ መንገድ የተሠራ ነው።

በተለይ ከዘመነ አብርሆት በኋላ ምዕራባውያኑ ዓለምን የተቆጣጠሩት በቴክኖሎጂያዊ ፈጠራዎቻቸው ነው። የመፍጠር አቅም ከሌለህ ግን ቢያንስ ሌሎች የፈጠሩትን በአግባቡ ለራስህ እንዲስማማ አድርገህ መጠቀም አለብህ። የቻይና ያለፉት አራት አስርት አመታት ተአምራዊ እድገት ምስጢሩ ደግሞ ይሄ ነው። አሜሪካ የተፈጠረን አንድ ቴክኖሎጂ ቻይና በርካሽ ዋጋ በከፍተኛ ብዛት እና በአንጻራዊ ጥራት በማምረት የዓለምን ገበያ እየተቆጣጠረች እዚህ ደርሳለች።

የእኛ ስልጣኔ ከዚህ ከሁለቱም የራቀ ሆነ። እንደ ምዕራባውያኑ መፍጠር አልቻልንም። እንደ ቻይናም የተፈጠረ ቴክኖሎጂን አላምደን እና አስርጸን አልተጠቀምንም። በተቃራኒው በምዕራባውያኑ ቴክኖሎጂ ተጠቅመን በምሥራቃውያኑ መንገድ ተጉዘን ፎርጅድ ሰነድ ማምረት እየለመድን ነው። አሁን በያዝነው ጎዳና ከቀጠልን ቻይና የኢትዮጵያን ገበያ በርካሽ ምርቶች የተቆጣጠረችውን ያህል ባለ ሀሰተኛ ሰነድ ግለሰቦች ባንኩንም ታንኩንም ሊቆጣጠሩ ይችላሉ።

የትምህርት ሚኒስቴር የ9 ወራት ቆጠራ እንደሚያመለከተው ከሆነ ምርመራ ከተካሄደባቸው ሰነዶች መካከል 6 ነጥብ 7 በመቶ ገደማው ሀሰተኛ ናቸው። ይህ ማለት ከ100 ዲግሪዎች 6 ወይም 7ቱ ሀሰተኛ ናቸው ማለት ነው። በጣም ከፍተኛ ቁጥር ነው። ይህ ቁጥር ብዙ በሽታዎች ወረርሽኝ ለመባል ከሚያስፈልጋቸው ቁጥር በላይ ነው። ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ከመቶ አንድ እንኳ ቢሆን ወረርሽኝ ነው ተብሎ መጠራት ያለበት። ከመቶ 7 ከደረሰ ግን ከወረርሽኝም በላይ ነው። ይህ የአገር ብሔራዊ ደህንነት አደጋ ውስጥ መግባቱን አመላካች ነው።

ይህን የብሔራዊ ደህንነት ስጋት ለመቀልበስ አንድ መፍትሄ አለ። እሱም ሕግ ማስከበር ነው። ነገር ግን ሕግ ለማስከበርም በመጀመሪያ ሕግ አስከባሪው ራሱ ከእንዲህ ዓይነት ተግባር የጸዳ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ስለዚህም የማጽዳት ሥራው መጀመር ያለበት ከሕግ አስከባሪው ነው። ከዚያም በየደረጃው በአስፈጻሚው አካል ውስጥ ያለው ኃይል በሙሉ ሰነዱ መመርመር አለበት። ያኔ የሚመጣው ውጤት ምናልባት ብዙዎቻችንን ወደ ድንጋጤ ሊከተን የሚችል ይሆናል።

ዛሬ ላይ ጨክነን እና ራሳችንን ለአሳዛኙ እውነታ አዘጋጅተን ይህን ችግር ካልቀረፍን ግን እንደ አገር ነገ ላይ በብዙ ሀሰተኛ ነገሮች የተሞላች አገር ለቀጣይ ትውልድ ልናስረክብ እንችላለን። ያኔ አገሪቱ በሀሰተኞች እና ወንጀለኞች እጅ ወድቃ፤ በእነሱም ቅኝት ተቃኝታ ፤ የእነሱን የጥፋት እሴት ወርሳ እውነትን የምትጠየፍ እና ሀቀኞችን የምታሳድድ አገር ትሆናለች። ሀቀኞችን የምታሳድድ አገር ደግሞ እንደ አገር አትከርምም።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

## ሕዝባችን ከክፉው ቀን እንዲወጣ መልካሙን እናዋጣ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

አገር የግለሰቦች አስተሳሰብ ናት። አገር የምትቆመው በእኔና በእናንተ በጎ ሀሳብ ነው። ዜግነት ከዚህ ውጪ ትርጉም የለውም። አሁን ላይ እኔና እናንተ የምንሆነው ነገር ነው የአገራችንን የወደፊት ዕጣ የሚወስነው። አገራችን ለእኛ ምቹና አስፈላጊ እንድትሆን ከሁሉ በፊት እኛ ለአገራችን ምቹና አስፈላጊዎች መሆን ይጠበቅብናል። ለአገራችን መልካሙን ሳናዋጣ፣ ለሕዝባችን በጎውን ሳናደርግ አገርና መንግሥትን ብንወቅስ ዋጋ የለውም። ብዙዎቻችን ማድረግ ያሉብንን ሳናደርግ ለወቀሳ የምንቸኩል ነን። ከእኛ የሚጠበቅብንን ሳናደርግ ለትችት የምንሮጥ ነን። ይሄን ሀሳብ እንዳነሳ ያደረገኝ ወቅታዊውና ብዙዎቻችንን ያማረረውን የኑሮ ውድነት ነው። በአገራችን ሁሉም ቦታ የኑሮ ውድነት ተከስቷል። ይሄ የኑሮ ውድነት እንዴት መጣ ብለን ስንጠይቅ መጀመሪያ የምናገኘው መልስ በስግብግብ ነጋዴዎች አማካኝነት የመጣ እንደሆነ ነው። እርግጥ ለዚህ የኑሮ ውድነት የሰሜኑን ጦርነት፣ የኮሮና ወረርሽኝን፣ የፖለቲካ ሽኩቻውን እንዲሁም የገንዘብ የመግዛት አቅም መውረድና ሌሎች ምክንያቶችን መጥቀስ እንችላለን።

እነዚህ ሁሉ ችግሮች እንዳሉ ሆነው ግን የአንበሳውን ድርሻ የሚወስዱት እኚህ «የቀን ጅቦች» ያልኳቸው በአቋራጭ መበልጸግ የሚፈልጉ ስግብግብ ነጋዴዎች ናቸው። በየትኛውም መመዘኛ ብንመዝነው በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያ ውስጥ ያን ያክል የምርትና የአቅርቦት ችግር አለ ተብሎ አይታሰብም። ነገር ግን አንዳንድ ነጋዴዎች የአገራችንን ወቅታዊ ሁኔታ እንደ ጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም ምርት በመደበቅና ዋጋ በማናር ለአገራችን ተጨማሪ ስቃይን ፈጥረዋል። እኚህ ነጋዴዎች በወንጀል ሥራ ረጅም ሰንሰለት ያላቸው ናቸው። የመንግሥትን የሥራ ኃላፊዎች እጅ መጠምዘዝ የሚችሉ፣ ትንሽ ሰጥተው ብዙ ለመቀበል የተሰናዳ ስነ ልቦናን ያነገቡ ናቸው። ወቅት እየጠበቁ፣ የአገራችንን ሁኔታ እየተከታተሉ ዋጋ መጨመር ያደጉበት ነው። ከማኅበረሰቡ በቅለው ማኅበረሰቡን እንዴት ማገልገል እንዳለባቸው አያውቁም። ከዛሬ ሌላ ነገ የሌላቸው በወገናቸው ስቃይ የሚስቁ አዳፋ ነፍሶች ናቸው። እኚህ አዳፋ ነፍሶች ራሮቶችን ቢያውቁ ኖሮ፣ እኚህ ገፍ ነፍሶች ጽድቅናን ቢማሩ ኖሮ የሕዝባችን የመኖር ጥያቄ በዚህ ልክ ባልሆነ ነበር።

ከትናንት እስከዛሬ ራሳችንን ብቻ ስንጠቅም የኖርን ነን። አብሮ የመብላትና፣ ተካፍሎ የመጋራት ኢትዮጵያዊ ባህላችን በጥቂት ራስ ወዳድ ግለሰቦች እየተሸረሸረ ነው። በሁሉም ነገር ላይ ኢትዮጵያዊነትን ለመግለጥ ምቹ ጊዜ ላይ ነበርን። ግን ራስ ወዳድነታችን ከኢትዮጵያዊነታችን በላይ ገዝፎ በመከራ ለተያዘ ሕዝብ ሌላ መከራ ሆነነዋል። እንዲህ ዓይነቱ ጊዜ አንድነታችንን ለመመለስ፣ የመረዳዳትና የመተጋገዝ ባህላችንን ከፍ ለማድረግ ጥሩ ጊዜ ነበር። ግን አልተጠቀምንበትም። ይሄ የኑሮ ውድነት ያልነካው የማኅበረሰብ ክፍል የለም። ከግለሰብ ባለፈ በፖለቲካውና በኢኮኖሚው እንዲሁም በማህበራዊ ሕይወታችን ላይ የከፋ ችግር እየፈጠረ ነው። በተለይም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያለውን የማኅበረሰብ ክፍል በእጅጉ እየጎዳው ይገኛል። የሚሰጡ እጆቻችን፣ የሚያዝኑ ልቦቻችን ወዴት ገቡ? እነዛ የሚራሩ ነፍሶቻችን፣ ድሀ ሲያዩ የሚያነቡ አይኖቻችን ወዴት ተሰወሩ? ፈሪሀ እግዚአብሔርን የተማረው በኢትዮጵያዊነት ተለቁጦ የተሠራው ግብረ ገብ ሰውነታችን ወዴት አለ?

መንግሥት የገበያውን ሁኔታ ለማረጋጋት እያደረገ ያለው ጥረት የሚደነቅ ቢሆንም፤ ከዚህም በላይ የቤት ሥራ እንዳለው ብዙ አመላካች ሁኔታዎች እየታዩ ነው። የፍላጎት መጠን መጨመር፣ የሕዝብ ቁጥር ከአመት አመት መጨመር፣ ከገጠር ወደ ከተማ የሚፈልሰው የማኅበረሰብ ክፍል ማደግ እና በመሳሰሉ ምክንያቶች አቅርቦቱን ከፍላጎት ጋር የማጣጣም ሥራው ተጠናክሮ መቀጠል አለበት። አጋጣሚዎችን በመጠበቅ ዋጋ በሚያንሩና ምርት በሚደብቁ የማኅበረሰብ ክፍሎች ላይ መንግሥት የማያዳግም እርምጃ መውሰድ ይጠበቅበታል። ሕይወትን ከድጡ ወደ ማጡ የወሰዱ ወጪት ሰባሪ የቀን ጅቦች እያደረሱ ላሉት የሰብዓዊ እንግልት ፈር እስኪይዙ ድረስ ተገቢውን ቅጣት ሊያገኙ ግድ ነው። ይሄ ባልሆነበት ሁኔታ ላይ የምናስተካክለው ነገር አይኖርም። ጮኸታችን ዋጋ የሚያወጣው ችግር ፈጣሪ ግለሰቦች ለሕግ ሲቀርቡ ነው። አሁን ላይ በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች በተደረገ ፍተሻ በርካታ የተደበቁ ምርቶች እየተገኙ ነው። ማስጠንቀቂያ ተሰቷቸው ማስጠንቀቂያውን ቸል ብለው በተገኙ ድርጅቶች ላይ ደግሞ እስከ መታሸግ የሚደርስ ቅጣት እየተላለፈ ነው። ይሄ ይበል የሚያሰኝ ነው። ግን ደግሞ በእጅ መንሻ የመንግሥት አካላትን እያታለሉ አሁንም ድረስ ከጥፋታቸው ያልታረሙ በርካታ ስግብግብ ነጋዴዎች አሉና እነሱም ሀይ ሊባሉ ይገባል።

ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነት አገራዊ ችግሮች ሲፈጠሩ አብዛኞቻችን ወደ መንግሥት ጣታችንን የምንቀስር ነን። አገራዊ ችግሮች በመንግሥት ብቻ አይፈቱም የኔም የእናንተም አብሮነት ግድ ይላል። ከመንግሥት ይልቅ እኔና እናንተ ለማኅበረሰቡ ቅርብ ነን። በአካባቢያችን የሚሆነውን እያንዳንዱን ኩነት የመታዘብ ዕድሉ አለን። ችግሮች ሲፈጠሩ፣ በአካባቢያችን ሕገ ወጥ ነጋዴዎችን ስናይ የመጠየቅ መብት አለን። ከፍ ሲልም ለሚመለከተው አካል በማጋለጥና ጥቆማ በመስጠት ኃላፊነታችንን መወጣት እንችላለን። ሌቦቻችንን አቅፈን እየተኛን፣ ችግር ፈጣሪዎችን ደብቀን እያሳለፍን የምንከላከለው ሕገ ወጥ ወንጀል አይኖርም። ይሄን የኑሮ ወድነት የፈጠረው እኮ ማንም አይደለም አብረውን የሚኖሩ የአካባቢያችን ነዋሪዎች ከፍ ሲልም ነጋዴ ቤተሰቦቻችን ናቸው። እነሱን በማጋለጥና ለሕግ በማቅረብ ለድሀ ሕዝባችን አለኝታ መሆን እንችላለን። ይሄ ሕዝብ በድህነት፣ በጦርነት፣ በኋላ ቀርነት ለዘመናት ሲጎዳ የኖረ ሕዝብ ነው። ይሄ ሕዝብ በድርቅ፣ በፖለቲካ ሽኩቻ የሚገባውን አጥቶ የኖረ ሕዝብ ነው። እንደ አገር ብዙ ነገር አጥተናል። በታሪካችን ላይ ማስታወስ የማንፈልጋቸውን ነውረኛ ትናንቶች ጽፈናል። አሁን ላይ እንደ መንግሥትም ሆነ ኃላፊነት እንደሚሰማው ዜጋ ለዚህ ሕዝብ ማንኛውንም በጎ መስዋዕት ልንከፍል ይገባል። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ፣ በቆረቆር ላይ ቁምጥና ሆነን ለችግሩ ሌላ ችግር ከመሆን ይልቅ ለመፍትሄና ለለውጥ ብንበረታ አሁን ላይ የምናያቸው ችግሮቻችንን ማስወገድ እንችላለን። ምክንያት እየፈለግን ከመገፋፋት ይልቅ ምክንያት እየፈለግን ብንተቃቀፍ ያዋጣናል። አንዳንድ ቀኖች አሉ፤ ልክ እንደ አሁኑ በጋራ ኖረን እንድንሻገራቸው የተፈጠሩ። አንዳንድ ጊዜዎች አሉ፣ ልክ እንደአሁኑ የእኛን አብሮነት የሚፈልጉ። አንዳንድ ቀኖች አሉ፣ ለብቻ ኖረን፣ ለብቻ ሮጠን የማናልፋቸው። እነዚህ ቀኖች የሚታለፉት በአንድነትና በመተሳሰብ ነው። ስለዚህ ሀብታም ከሆነን ለድሀው ወገናችን፣ ነጋዴ ከሆንን አቅም ለሌለው ሸማች ልንራራ ይገባል።

> **እስኪ አንድ ጊዜ ወደ ዓለም እንመልከት፤ የዓለም ኃያላን አገራት ስንዴ ረድተውን ያውቃሉ፣ ገንዘብ አበድረውንና ረድተውን ያውቃሉ። በፖለቲካው በኢኮኖሚው፣ በማህበራዊ ሕይወታችን የረዱን ብዙ ነገር አለ። እኛ ግን ራሳችንን ረድተን አናውቅም**

የኢትዮጵያ ሕዝብ ድሀ ሕዝብ ነው። ማጣት ያስጎነበሰው ሕዝብ ነው። በራስ ወዳድነት ይሄን ሕዝብ ድጋሚ አንገት እንዲደፋ መፍቀድ የለብንም። ከሌለው ላይ ቆርሶ ቀን ያወጣን ሕዝብ ነው፤ ውለታውን ለመመለስ ዛሬ ላይ በጎ ሆነን ከጎኑ ልንቆም ይገባል። በራስ ወዳድነት በዚህ ሕዝብ ላይ የምናደርገው ማንኛውም ነገር ነገ ላይ የማንችለውን ዋጋ ነው የሚያስከፍለን። ዛሬ ላይ ምርት ጨምረንም ሆነ ዋጋ አንረን የምናሰቃየው ሕዝብ ትናንት ላይ ከሌለው ላይ የሰጠን ነበር። ዛሬ ላይ በፖለቲካና በኢኮኖሚ ጫና የምናሳድርበት ማኅበረሰብ ትናንት ላይ ዛሬን እንድናይ መንገድ የጠረገልን ነበር። ዛሬ ላይ በጎነታችንን የነፈግነው ሕዝብ ትናንት ላይ ከፍ እንድንል ምክንያት የሆነን ሕዝብ ነው። ይሄን ሕዝብ ማገልገል በምን ይለካል? ለዚህ ሕዝብ መገዛት ዋጋው ምን ያህል ነው? ውለታ በል መሆን የለብንም። ዛሬ ላይ ያሉን ነገሮች ሁሉ ማኅበረሰባችን የሰጠን ነው። ይሄን ሕዝብ በታማኝነት በማገልገል ውለታውን መመለስ ይኖርብናል። እንደ ነጋዴ በእውነትና በታማኝነት ልናገለግለው ይገባናል። እንደ መንግሥትም የማኅበረሰቡን ችግሮች በመፍታትና አፋጣኝ መፍትሄዎችን በመፈለግ ከጎኑ ልንቆም ይገባል።

ወቅቱ በመተሳሰብና በመተጋገዝ የምንኖርበት እንጂ በራስ ወዳድነት የምንበለጽግበት አይደለም። አይደለም በዚህ አስከፊ ጊዜ ቀርቶ በደህናው ጊዜም ቢሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ምንም የሌለው ነው። እያንዳንዷን ክፍተት እንደ ምክንያት በመቁጠር ስቃይ መፍጠር የለብንም። ዜግነት ትርጉም የሚኖረው በእንደዚህ ዓይነቱ ጊዜ ላይ አገርና ሕዝብን በታማኝነት ስናገለግል ነው። ለአገራችን ዋጋ መስጠት አለብን፣ ለሕዝባችን ዋስትና ልንሆነው ይገባል። በመረዳዳትና በመተጋገዝ የትናንቱን የአብሮነት መንፈስ መድገም እንጂ ስር በሰደደ የእኔነት ስሜት በጭፍን መጋለብ አይኖርብንም። ልብ ቢኖረን ኖሮ ይህ ጊዜ የአገራችንን ውለታ የምንመልስበት ነበር። ብናስተውል ኖሮ ደግነታችንን በማሳየት ድሃውን ሕዝባችንን የምንክስበት ነበር።

እስኪ አንድ ጊዜ ወደ ዓለም እንመልከት፤ የዓለም ኃያላን አገራት ስንዴ ረድተውን ያውቃሉ፣ ገንዘብ አበድረውንና ረድተውን ያውቃሉ። በፖለቲካው በኢኮኖሚው፣ በማህበራዊ ሕይወታችን የረዱን ብዙ ነገር አለ። እኛ ግን ራሳችንን ረድተን አናውቅም። እኛ ለእኛ ንፉጎች ነን። ኢትዮጵያዊነት እኮ የራስ መልክ ነው። በዙሪያችን ያለው ሕዝብ የእኔና የእናንተ መልክ ነው። ይሄን ሕዝብ መርዳት ሲገባን ምርት እየደበቅንና ዋጋ እያናርን እናሰቃየዋለን። ለምን? በዚህ ለምን ውስጥ ራሳችሁን ፈልጉት። ድሀ ገድሎ የሚከብር ሀብታም የለም። ድሀ አስጨንቆ ቀን የሚወጣ ባለጸጋ የለም። በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ ለአገራቸው ቸር የማያስቡ፤ በዚህ ሰዓት አጋጣሚ እየጠበቁ በአገርና ሕዝብ ላይ ስቃይ የሚፈጥሩ፤ በዚህ አገር በጭንቅ ባለችበት ሰዓት አጋጣሚውን በመጠቀም ለአገርና ለሕዝብ የማይራሩ ሁሉ «የቀን ጅቦች» ናቸው። ስልጣናቸውን ተገን አድርገው ከድሀ አገርና ሕዝብ ላይ የሚሰርቁም እነሱ «የቀን ጅቦች» ናቸው።

በምንም ነገር ላይ ራሳችንን መፈተሽ ይኖርብናል። ምን እያደረግን ነው ያለነው? ችግር ፈጣሪዎች ነን ወይስ ችግር ፈቺዎች? የሕዝባችን ችግር ያመናል ወይስ ችግሩን እንደ መወጣጫ ተጠቅመን ከፍ ለማለት እየሞከርን ነው? ዜግነታችን በዚህ ጥያቄ ውስጥ ነው ያለው። የአገር ፍቅር ስሜታችሁ እነዚህን ጥያቄዎች ስትጠይቁ የሚጸና ነው። ራሳችሁን ጠይቁ። አገር መውደድ፣ ለአገሬ ምን እያደረኩ ነው ከሚል ከመልካም ሀሳብና ተግባር የሚጀምር ነው። የአገር ፍቅር ከመስጠትና ከበጎነት የሚጀምር ነው። ሰውነት በዙሪያችን ያሉትን ማቀፍና ማፍቀር ነው። ወደ መጥፎ የምንራመዳት አንድ ርምጃ ነገ ላይ ለእኛ መውደቂያ ጉድጓድ የምትሆን ናት።

በደህናው ጊዜ በቀን ሦስት ጊዜ የማይበላ ማኅበረሰብ በዚህ የኑሮ ውድነት ዛሬ ላይ ምን እንደሚሆን መገመት አይከብደንም። የምናገኘው ወርሀዊ ደመወዝ አይደለም የወር አስቤዛ ሊገዛ ቀርቶ አምስት ሌትር ዘይት ለመግዛት አቅም እያጣ ነው። በዚህ ሕዝብ ላይ ክፉ መሆን እውነት ስርየት የሌለው ሀጢዐት እንደሆነ ነው ማስበው። በማንኛውም መስክ ላይ የተሰማሩ የአገርና የሕዝብ ጠላት የሆኑ ውለታ በል የቀን ጅቦች መጋለጥ አለባቸው። ሕዝብ እያስጨነቁና ድሀ እየበዘበዙ ያሉ ነውረኛ ግለሰቦችና ድርጅቶች በሕግ መጠየቅ ይኖርባቸዋል። ጅብነታቸውን እስኪተዉ ድረስ በሥራቸው መጠየቅ ይኖርባቸዋል። ነገ ላይ ጅብ እንዳይወልዱ የአገር ፍቅር ስሜትን ሊማሩ ይገባል። ይህ እንዲሆን ግን ዛሬ ላይ ያለን ሁላችን እኛ ኃላፊነታችንን ልንወጣ ይገባል።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# ከቤተሰብ ፍጆታ ያለፈ የከተማ ግብርና

**ስምስም መንግሥቱ**

ለአካባቢው ማህበረሰብ ስለ ግብርና ሥራ ማውራት «ለቀባሪው አረዱት» እንደሚባለው አባባል ነው፡፡ ከግብርና ሥራ ጋር እንደሚተዋወቁ የሻከረው እጃቸው ምስክር ነው። በአካባቢያቸው ያለሙት አትክልት ጉልህ ማስረጃ ነው፡፡ በአካባቢው ለማልማት አቅም የሌለው እንኳን ቢኖር ያለውን ቦታ አቅሙና ጉልበቱ ያላቸው እንዲያለሙበት ይፈቅዳል። ይህን አስደናቂ የከተማ ግብርና ሥራ የተመለከትነው በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ አራት ውስጥ ነው፡፡

ወላጆች ለልጆች ያቆዩት መልካም ተሞክሮ ዛሬ በልጆቻቸው እግር ተተክቶ መሬቱ ለልማት በመዋል ለምግብ የሚውሉ አትክልቶች በስፋት ከመመረታቸው በተጨማሪ የመተዳደሪያ ገቢያቸውም ሆኗል፡፡ ለአካባቢ ውበትም ሆኗል። ማህበረሰቡ እያከናወነ ያለው የአትክልት ልማት በአገር ደረጃ ለተያዘው የከተማ ግብርናን የማበረታታት መርሃግብር ትልቅ እገዛ አድርጓል፡፡ በልደታ ክፍለ ከተማ ውስጥ በንቅናቄ እየተከናወነ ላለው የከተማ ግብርናም አካባቢው ሞዴል መሆኑም የበለጠ ትኩረት ስቧል፡፡ እኛም በስፋት አትክልት በሚለማበትና የዶሮ እርባታም በሚከናወንበት በዚህ ሥፍራ ተገኝተናል፡፡ ባየነው ልማትም የግብርና ሥራን ማነው ለአርሶ አደሩ ብቻ የሰጠው አስብሎናል፡፡ መሬቱና የመስራት ፍላጎቱ ካለ በከተማም የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ እንደሚቻል በተጨባጭ አይተናል፡፡ ማህበረሰቡ የግብርና ሥራን የተገነዘበ መሆኑ ደግሞ ለልማቱ ውጤታማነት የበለጠ ዕድል ሰጥቷል፡፡

ከተማ ውስጥ ተወልዶና ተምሮ የግብርና ሥራ የሚመኝ ወጣት እምብዛም አያጋጥምም፡፡ ነገር ግን በተለያየ የሥራ መስክ ለመሰማራት ፍላጎት የሚያሳዩ የከተማ ልጆችን በግብርና ሥራ ላይ ማግኘት ዘመን መቀየሩን ነው የሚያሳየው።

ገቢ ካስገኘ ማንኛውም ሥራ በየትኛውም ቦታ የሚከበር መሆኑን በግብርና ሥራው ላይ ያገኘኋቸው ወጣቶች ማሳያ ናቸው፡፡ ወጣት ዘካሪያስ ቢረዳ ትዳር መስርቶ የልጆች አባት ቢሆንም በዕድሜው ወጣት ነው፡፡ በአካባቢው የሚያለማው አትክልት ዋና የገቢ ምንጩ ነው፡፡ ዛሬ አቅማቸው ደክሞ ከቤት የዋሉት ወላጆቹ ባላቸው ቦታ ላይ አትክልት አልምተው ተጠቃሚ ሲሆኑ እያየ ብቻ ሳይሆን እየሠራም በማደጉ በእነርሱ እግር ተተክቶ በግብርና ሥራው ሲሰማራ አልተቸገረም፡፡ የሥራን ባህል ያወረሱትን ወላጆቹንም ያመሰግናቸዋል፡፡

ወጣት ዘካሪያስ አትክልት የሚያለማው በመስመር ነው፡፡ አንድ አልሚ እስከ ስድስት መስመር ይኖረዋል፡፡ መሬቱ በካሬ እስከ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ይሆናል፡፡ በዚህ የሚያለማው የአትክልት ዓይነቶች የተለያየ ዝርያ ያላቸው ቆስጣ፣ ጎመን፣ አበባ ጎመን፣ ሰላጣ፣ የሾርባ ቅጠል፣ ካሮት፣ ቃሪያ፣ ባሮ ሽንኩርት ነው፡፡ ልማቱ የሚከናወነው በባህላዊ መሣሪያዎች በጉልበት ነው፡፡ ለመስኖ የሚጠቀሙት ውሃም በአቅራቢያቸው ከሚገኝ ወራጅ ውሃ ነው፡፡

የአትክልት ልማቱ ምርታማ እንዲሆን ማዳበሪያና ምርጥዘር መጠቀም ያስፈልጋል። ወጣት ዘካሪያስም የመሬት ማዳበሪያ የሚጠቀመው ከከብት እዳሪ የተፈጥሮ ማዳበሪያ (ኮምፖስት) በማዘጋጀት መሆኑን ይናገራል። የተፈጥሮ ማዳበሪያውን የሚያዘጋጁት በአካባቢው ከብት ካላቸው ሰዎች በግዥና አልፎ አልፎም ከአካባቢው በመሰብሰብ ነው፡፡ በዚህ መልኩ መቀጠሉ አዋጭ ሆኖ አላገኙትም፡፡ ከአትክልት ልማቱ በተጨማሪ ከብትና ዶሮን በመጨመር ጥምር ግብርና ማከናወን ቢችሉ ለማዳበሪያ ግብአት የሚውለውን የከብት እዳሪ በቀላሉ ማግኘት ይችላሉ፡፡ ተመጋጋቢ የሆነ ሥራ በመስራት የበለጠ ውጤታማ እንደሚያደርጋቸው በመተማመን ዕቅድ ነድፈው ለአራዳ ክፍለ ከተማ የግብርናውን ዘርፍ ለሚመራው ክፍል አሳውቀው ምላሽ እየጠበቁ ነው፡፡ እቅዳቸው ተቀባይነት ኖሮት የመስሪያ ቦታ ቢመቻችላቸውና ለእርባታ የሚሆን የእንስሳት ዝርያ በተመጣጣኝ ዋጋ ማግኘት ቢችሉ ከራሳቸው ባለፈ የከተማ ግብርናን ዓላማ ሊያሳኩ እንደሚችሉ ያምናሉ። የክፍለ ከተማው ድጋፍና ክትትል እንዳልተለያቸውም ወጣቱ ነግሮናል፡፡


የከተማ ግብርና ዘርፈ ብዙ ዓላማዎች አሉት፡፡ አሁን ላይ ለምግብ አገልግሎት የሚውሉ አቅርቦቶች ላይ እየተስተዋለ ያለውን የዋጋ ንረት በማርገብ የኑሮ ውድነትን ለማሻሻል አንዱ አማራጭ የከተማ ግብርናን በስፋት በማከናወን የሸማቹን የመግዛት አቅም ያማከለ ለማድረግ፣ እያንዳንዱ የከተማ ነዋሪም የዕለት ፍጆታውን በራሱ ለመሸፈን እንዲችል ለማበረታታት፣ ሥራ የሌላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎችም በዘርፉ ላይ በመሰማራት ገቢ በማመንጨት የኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ጥቂቶቹ ናቸው። «በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ» በሚባለው ብሂል ወጣት ዘካሪያስ እየተጠቀመ መሆኑን ነግሮናል፡፡ እርሱ እንዳለው በየቀኑ ምርቱን ለገበያ ያቀርባል፡፡ ይህም ምርት ከበቂ በላይ



ወጣት ዘካሪያስ በአትክልት ልማቱ ላይ፣



የአቶ ኃይለገብርኤል ነሪ የዶሮ እርባታ፣



ፎቶ፡- ስምስም መንግሥቱ

አቶ ሰለሞን ገብሬ ስለ ግብርና ሥራው ገለጻ ሲያደርጉ፣

መኖሩን ያረጋግጣል፡፡ ግብይቱም የሚከናወነው ነጋዴዎች ከማሳው ላይ ምርቱን ለቅመው በማንሳት ሲሆን፣ ሽያጩም በግምት ነው የሚከናወነው፡፡ ከአንድ ማሳ በአንዴ ለቀማ ከ1500 እስከ 2500 ብር ነው የሚሸጠው፡፡ ግለሰቦች እንደአቅማቸው መግዛት ከፈለጉም ይስተናገዳሉ፡፡ የመሸጫ ቦታ ተመቻችቶላቸው አልሚውና ሸማቹ በቀጥታ ተገናኝቶ ቢገበያይ ግን ተጠቃሚነታቸው የበለጠ ሊሆን እንደሚችል ነው ወጣቱ የገለጸልን፡፡

የጋራዥና የተለያየ ስድስት ዓይነት የሙያ ባለቤት መሆኑንና ከነበረው ሙያ ሁሉ ግብርና እንደሳበው የገለጸልን አቶ ሰለሞን ገብሬ ይባላል፡፡ ከግብርና ሥራው የኢኮኖሚ ተጠቃሚ ብቻ ሳይሆን አካላዊና አዕምሮአዊ ጤናም ማግኘቱን ይናገራል፡፡ ያለማውን አትክልት በማየት ይደሰታል። ሲቆፍርና ሲኮተኩት አካላዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ጤናውን ይጠብቃል፡፡ በመሆኑም ሙሉ ጤናማ እንደሆነ ይሰማዋል። በግብርናው የሚያገኘው ገቢ ወይንም የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ባሉት የተለያየ የሙያ ዘርፍ ከሚያገኘው የተሻለ ሆኖ ነው ያገኘው፡፡ አሁን በአንድ ሄክታር መሬት ላይ ነው ልማቱን እያከናወነ የሚገኘው፡፡

አቶ ሰለሞን በግብርናው ሥራ በቆየባቸው 17 ዓመታት የታዘበውን ከጥቂቶች በስተቀር የብዙዎች የሥራ ባህል ደካማ መሆኑን ነው፡፡ ጉልበት የሚጠይቅና የሚያቆሽሽ ሥራ የሚፈልግ ሰው አለመኖሩን የተረዳው አጋዥ ሠራተኞች ሲፈልግ ከሚያገኘው መልስ ነው፡፡ የግንዛቤ ችግር እንጂ የግብርና ሥራ እንደሚባለው አያቆሽሽም፡፡ ቁፋሮውም ሆነ ኩትኮታው፣ ችግኝ ተከላውም በውስን ወቅቶች ነው የሚከናወነው፡፡ እራስን ጠብቆ ለመሥራት አያግድም፡፡ ከጉዳቱ ጥቅሙ ከፍ ያለ ነው፡፡ በሰው ኃይል እጥረት በዘር ያልተሸፈነ መሬት እንዳለውም ተናግሯል፡፡ በከተማ ግብርና ሥራ ላይ ረጅም አመት የቆየው አቶ ሰለሞን፣ የተለየ ለውጥ አላመጣም የሚል አስተያየት በአካባቢው አንዳንድ ነዋሪ ቢቀርብበትም አስተያየቱ ከግብርና ሥራው አላራቀውም፡፡ ለውጥ ላለማምጣቱ ምክንያቶቹ ያመረተውን ምርት በቀጥታ ለተጠቃሚው ማቅረብ ባለመቻሉና በመካከል በሚገቡ ደላሎች እንደሆነ ይናገራል፡፡

«መሬት ቆፍሬ፣ ዘር ገዝቼ፣ ውሃ አጠጥቼና ኮትኩቼ ሦስት ወር ሙሉ ለፍቼ ያለማሁትን አትክልት በዋጋ ከነጋዴ እኩል ነው የምካፈለው» ሲል ያማርራል፡፡ በከፍተኛ ሁኔታ ትርፍ ለማግኘት የሚሞክረውን ነጋዴና ደላላ ማስወጣት የሚቻለው አልሚውና ሸማቹ በቀጥታ የሚገናኙበት መንገድ ሲመቻች መሆኑን ይናገራል፡፡ ክፍለከተማው ችግሩን ግንዛቤ ውስጥ በመክተት ለሁለት ሳምንት በፑሽኪን አደባባይ ባመቻቸው የመገበያያ ቦታ ለውጡን ማየት መቻሉንም ገልጿል፡፡ የተመቻቸው ቦታ በተለያየ ምክንያት በመከልከሉ ግብይቱ ሊቀጥል አልቻለም፡፡ ሌሎች የተሰጡት ቦታዎች ከሸማቹ ጋር ለመገናኘት ምቹ አይደሉም፡፡ እርሱ እንዳለው የቀጥታ ግንኙነቱ ምቹ በሆነ ቦታ ላይ ቢመቻች ግን ነጋዴ በ40 ብር የሚያቀርበውን አንድ እስር ጎመን በግማሽ በማቅረብ ሸማቹን ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል፡፡ በተናጠል ያነጋገርናቸው አልሚዎች የየራሳቸውን የልማት ሥራ የሚያከናውኑ ቢሆንም መሬቱ በአንድ አካባቢ በመሆኑ ብዙ ነገሮችን ተጋርተው ነው የሚሠሩት፡፡

የአትክልት ልማቱ ከሚከናወንበት ሥፍራ ሳንወጣ ተመጋጋቢ በሆነው በዶሮ እርባታ ሥራ ላይ የተሰማራውን የአቶ ኃይለገብርኤል ነሪ ሥራ ቃኝተናል፡፡ አምስት አመት ከሠራበት የአሽከርካሪነት ሥራ ወጥቶ ነው ፊቱን ወደ ዶሮ እርባታ ያዞረው፡፡ ለገበያ የሚበቃ ባይሆንም ለቤተሰብ የምግብ ፍጆታ የሚውል አትክልትም ባለው አነስተኛ ቦታ ላይ ያለማል፡፡ የዶሮ እርባታ ሥራ ክትትል የሚጠይቅ ነው፡፡ በመሆኑም ጊዜውን በአግባቡ ሥራ ላይ ያውላል፡፡ ፊቱን ወደ ግብርና ሥራ ማዞሩ አሽከርካሪ ሆኖ በሌሎች ላይ ይታዘባቸው ከነበሩ ወጣ ካሉ የሥነምግባር ችግሮችና እርሱም የመጥፎ ሥነምግባር ሰለባ ሳይሆን ቶሎ ለመመለስ ስላስቻለው የዶሮ እርባታውን ባለውለታው አድርጎ ይወስደዋል፡፡ በዶሮ እርባታው ላይ ተሰማርተው ውጤታማ የሆኑ ጓደኞቹን በማየትና በልጅነቱም ቤተሰቡም ሆነ የአካባቢው ማህበረሰብ ዶሮ ሲያረባ እያየ በማደጉ የሥራ ዘርፉን ለመምረጥ አንዱ ምክንያት ሆኖታል። ይሄ አዋጭ የሥራ ዘርፍ እንደሆነውም አረጋግጧል፡፡ ጉልበቱንና ጊዜውን ለሥራ በማዋል ሀብት የሚያፈራበትንም ዕድሜ ለመጠቀም ጊዜው አሁን እንደሆነም ያምናል፡፡

የዶሮ እርባታውን ከቤተሰቡ ጋር በመሆን በአምስት መቶ ዶሮዎች ነው ሥራውን ዘንድሮ የጀመረው፡፡ በክፍለ ከተማው አማካኝነትም ሥልጠናዎችን ቀድሞ በማግኘቱ አልተቸገረም፡፡ በተለያየ ጊዜ ከአምስት መቶ እስከ ስምንት መቶ ዶሮዎችን በማስገባት ነው የእርባታ ሥራውን የሚሠራው፡፡ ግብይቱ የሚከናወነው ዶሮዎቹ እንቁላል መጣል እስከሚያቆሙ ድረስ እንቁላል ይሸጣል፡፡ ጎን ለጎን ደግሞ እንቁላል መጣል ያቆሙ ዶሮዎችን ይሸጣሉ። ወደ ሥራው ለመግባት የሥራ ፈቃድ ማግኘት የነበረው ውጣ ውረድና ለዶሮ ቤት ለመሥራት የነበረው ወጪ ቶሎ ለውጤት የሚያበቃ ካለመሆኑ በስተቀር መስመር ከያዘ በኋላ ያለው ሂደት ተስፋ ሰጪ ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ለዶሮዎች የሚውለው የአንድ ኩንታል ዋጋ እስከ ሦስት ሺህ ብር የሚገዛ በመሆኑ ውድነቱ ተግዳሮት እንደሆነበት ይናገራል፡፡ አቶ ኃይለማርያም ሥራውን ለመጀመር ወደ አራት መቶ ሺህ ብር ወጪ አውጥቷል፡፡ ወደፊት የሚያስገኝለትን ውጤት ተስፋ በማድረግ ወጪው አላሳሰበውም፡፡ ክፍለ ከተማው የብድር አገልግሎት የሚያገኝበትን ቅድመ ሁኔታ በማመቻቸት ያለማስያዥያ 75ሺ ብር ብድር ማግኘቱ ለሥራው ትልቅ ድጋፍ ሆኖለታል፡፡ ወደፊት የከብት እርባታንም ጨምሮ በመሥራት የግብርና ሥራውን የማስፋት ፍላጎት እንዳለው ገልጾልናል፡፡

የከተማ ግብርና ሥራ በከተማው የሚስተዋለውን የዋጋ መናር ማርገቡን የነገሩን ደግሞ የልደታ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ አሰግደው ኃይለጊዮርጊስ ናቸው። የኑሮ ውድነቱን ከሚያርገበው አንዱ የከተማ ግብርና መሆኑ ስለታመነበት በንቅናቄ በስፋት በማጠናከር እየተሠራ ይገኛል። ሥራውም ሁለት ጉዳዮችን ታሳቢ ያደረገ ነው። አንዱ በከተማ ግብርና ሥራ ላይ የቆዩ ወይንም ነባር ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾችን፣ ግለሰቦችን፣ በአጠቃላይ በጋራና በተናጠል የሚሠሩትን የማጠናከርና የመደገፍ ሲሆን፣ ድጋፉም ምርትና ምርታማነታቸውን ለማሳደግ የሚያስችላቸውን ቴክኖሎጂዎችን ጨምሮ የተለያዩ የግብርና ግብአቶች በማሟላት ይገለጻል፡፡ አልሚዎቹ ከግብርና ባለሙያዎችና ከአመራሩ ጋር በቅርበት እንዲሠሩም እየተደረገ ይገኛል፡፡ በልማቱ ላይ የሚገኙት አብዛኞቹ ከቤተሰብ ፍጆታ ባለፈ ለገበያ አቅርበው እየተጠቀሙ ናቸው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ግን በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ በተከናወኑ አዳዲስ የግብርና ሥራ እንቅስቃሴዎች በክፍለ ከተማው ወደ 25ሺ የሚሆነው ነዋሪ የቤተሰብ ፍጆታውን ማሟላት ባይችል እንኳን ቢያንስ 50 በመቶ እራሱን መደጎም እንዲችል በንቅናቄ እየተሠራ መሆኑን የተናገሩት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፣ ከታች እስከ ላይ ባለው እርከን የሚገኘው አመራር ቁልፍ አጀንዳው አድርጎ በመያዝ ኮሚቴ አዋቅሮ በእቅድ እየተመራ እየገመገመ ሥራው እንዲከናወን ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ እስካሁን በተከናወነው ሥራም ከ12ሺ በላይ የሚሆኑ ነዋሪዎች ለቤተሰብ ፍጆታ የሚውሉ ልማቶች ላይ እየተሳተፉ ነው፡፡ ትምህርት ቤቶች፣ የኃይማኖት ተቋማት፣ የጤና እና ሌሎችም ተቋማት ላይ የከተማ ግብርና ልማት እንዲሠራባቸው ጎን ለጎን ጥረት እየተደረገ መሆኑንና ሌሎች አማራጮችን በመፈተሽም ሥራውን ለማስፋት እየተሞከረ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በልማቱ ሥራ አመራሩም አርአያ መሆን ስላለበት ሰፊ ግቢ ያላቸው በማልማት እንዲያሳዩም አቅጣጫ ተቀምጧል። ከአንድ ወር በኋላም ልማቱ ደርሶ ለአካባቢ ማህበረሰብ ጭምር ይሆናል የሚል እምነት የጣለበት ነው፡፡ በዶሮ እርባታ፣ በከብት ማድለብና ማርባት በተመሳሳይ ለማጠናከር ጥረቶች ይቀጥላሉ ብለዋል፡፡ ዋና ሥራ አስፈጻሚው በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ አራት ውስጥ ያለውን ልማት በማድነቅ፣ በአካባቢው ወደ ዘጠኝ ሄክታር ላይ ከሚለማው የተለያየ አትክልት ኅብረተሰቡ እየጠቀመ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ማህበራዊ

# አስኳላ

# ኢንስፔክሽን - የትምህርቱ ዘርፍ ችግር ፈቺ መሣሪያ

ግርማ መንግሥቴ



እዚህ "ኢንስፔክሽን" የሚለውን ፅንሰ ሀሳብ እንደ ወረደ ነው ሥራ ላይ ውሎ የምናገኘው። ባለሙያዎች ቀጥተኛውን አግኝተው እስኪነግሩን ድረስም እኛ "ከስጋት ነፃ" በሆነ መልኩ ይህንኑ እንጠቀማለን ("ኢንስፔክሽን"ን "ቁጥጥር"፣ "ኢንስፔክተር"ን "ተቆጣጣሪ"፣ "ኦዲተር" የሚሉት/የማይሉት እንዳሉ ሆነው) ማለት ነውና እንቀጥል።

ኢንስፔክሽን በማንኛውም ዘርፍ እስኪባል ድረስ ተፈላጊና አስፈላጊ ፅንሰ ሀሳብ ነው። "የማይገባበት የለም" እስኪባልም ድረስ ጨው ነው። የራሱ የሆኑ "ስታንዳርዶችን እና ማዕቀፎች" አሉት። "የትምህርት ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት" የሚባል ዘርፍና የዘርፉ ሹም ሁሉ አለው። አንዳንዶች ጋ ሀይራርኪው እስከ "ኢንስፔክሽን መምሪያ" ድረስ ይዘልቃል። "የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን የሥራ ሂደት ኃላፊዎች"ም አሉት። የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆችም ይሁን ዩኒቨርሲቲዎች ለ"ኢንስፔክሽን" ያላቸው ቦታ በ"ከ - እስከ" የሚወሰን አይደለም። "ሱፐርቪዥን"ም እንደዛው። ችግሩ በአገራችን የእነዚህ ፅንሰ ሀሳቦች ዘለግ የለ እድሜና እየተስተዋለ ያለው የትምህርት ጥራት ማሽቆልቆል አለመጣጣሙ ነው።

ከጥቂት አመታት በፊት "በአገር አቀፍ ደረጃ ሊያሠራ የሚችል፣ ወጥነት ያለውና ለትምህርት ጥራት መሻሻል አስተዋፅኦ ሊያበረክት የሚችል የኢንስፔክሽን ስታንዳርድ ባለመኖሩ በአገሪቱ የሚገኙ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የተለያዩ መለኪያዎችን ሲጠቀሙ መቆየታቸው" ችግር እየፈጠረ እንደነበር፤ ይህንንም ለመቅረፍ " የኢንስፔክሽን ማዕቀፍ" ማዘጋጀት እንደሚያስፈልግ የጉዳዩ ባለቤት የሆነው የትምህርት ሚኒስቴር (የኢንስፔክሽን ማዕቀፍና ቼክሊስት ለማዘጋጀት ደብረ ዘይት በከተመበት ጊዜ) ገልፆ እንደነበር አይዘነጋም። ይህ የሚነግረን ያለው ቃሉ እንጂ "የኢንስፔክሽን ሥርዓት ለመዘርጋት" የሚያስችለው፤ መተግበሪያው አይደለም ማለት ነው። ጉዳዩን አጥብበን ወደ አዲስ አበባችንም ስናመጣው ያው ነው። ለዚህ ደግሞ ከሚከተለው አንቀፅ በላይ ማሳያ የለም።

"በበጀት አመቱ በስታንዳርድ ኢንስፔክሽን ሞዳሊቲ ለመጀመሪያ ጊዜ በከተማ አስተዳደሩ ስር በሚገኙ 87 የግል እና የመያድ ኮሌጅ ላይ ስታንዳርድ ኢንስፔክሽን የተሠራ ሲሆን ኮሌጆቹ ከግብአት፣ ከሂደትና ከውጤት አንፃር ያገኙትን ውጤት በዝርዝር በመተንተን ለባለድርሻ አካላትና ለኮሌጆቹ ያሉበትን ደረጃ በሚያሳይ መልኩ በማዘጋጀት በኢንስፔክሽኑ የተገኙትን ጥንካሬዎችና ክፍተቶች እንዲሁም ለክፍተቶቹ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን በተገቢው በመለየት የተግባሩን አፈፃፀም ሊያሳይ በሚያስችል መልኩ [...]" ማዘጋጀቱን ይነግረናልና "ለመጀመሪያ ጊዜ ..."ን ታዝበን፤ የኢንስፔክሽንን ፋይዳ ተገንዝበን ልናልፈው እንገደዳለን። እናታችንን ሲያዞር የኖረውን የትምህርት ጥራት ችግርም ችግሩ ከስረ መሠረቱ ምን እንደሆነ (ቢያንስ በከፊል) እንረዳለንና ለጠቅላላ እውቀትም ቢሆን የዚህ ጽሑፍ አንባቢያንን "በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ስልጠና ጥራት፣ የሙያ ብቃትና ምዘና ማረጋገጫ ባለስልጣን የ2013 በጀት አመት የግልና የመያድ ኮሌጆች የውጭ ኢንስፔክሽን ትንተና ማጠቃለያ ሪፖርት" በሚል ርእስ በባለስልጣኑ የትምህርትና ሥልጠና ጥራት ማረጋገጥ ዳሬክቶሬት የተዘጋጀውን ሰነድ እንዲመለከቱ እንጋብዛለን። (በነገራችን ላይ፣ በአሁኑ ሰዓት በተለያዩ ተቋማት አማካኝነት ለውይይት የሚቀርቡ ሰነዶች ብዙዎቹን አሠራሮች "ለመጀመሪያ ጊዜ ..." ሲሉ ነው የሚነበቡት። እውነት ከሆነ መሀል ላይ ኢትዮጵያ አርጋ፤ ወይም ሱባኤ ገብታ ነበር ማለት ነው።)

እዚህ ላይ ግን፣ ከዚሁ ሰነድ ርቀን ሳንሄድ ሰነዱ ስለ "ኢንስፔክሽን" አላማ፣ ወሰንና ፋይዳ በ"ፓወርፖይንት" ያስቀመጠውን እንመልከት።

የኢንስፔክሽን ግኝት ትንተና አላማ "ኮሌጆች የሚጠበቅባቸውን ተፈላጊ የት/ስልጠና የጥራት የአፈጻጸም ደረጃ ማሟላታቸውን ለማረጋገጥና ኮሌጆቹና ባለድርሻ አካላቶች በግኝቶቹ ላይ የበኩላቸውን አወንታዊ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ለማስቻል እና በየደረጃው የተጠያቂነት ሥርዓትን ለማስፈን"፤ የትንተናው ወሰን "ይህ የስታንዳርድ ኢንስፔክሽን ትንተና ሰነድ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚገኙ ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 4 የሚያሰለጥኑ የግልና መንግሥታዊ ያልሆኑ (መያድ) ኮሌጆች ላይ ያተኮረ ይሆናል፡፡" እንዲሁም ኢንስፔክሽኑ ለቴ/ሙያ ት/ስልጠና ጥራት ያለው ፋይዳን "በከተማ አስተዳደሩ ስር በሚገኙ የቴ/ሙያ ት/ስልጠና ኮሌጆችን በ2013 ዓ.ም ከስታንዳርድ ኢንስፔክሽን አገልግሎት አንፃር ያሉበትን ደረጃ ለማሳወቅ" በማለት ያሰፍረዋል። የኢንስፔክሽን አላማ፣ ወሰንና ፋይዳ እነዚህ ሲሆኑ፤ "ኢንስፔክሽን" የትኩረት መስኮችም አሉት፤ መለኪያዎችም እንደዛው።

ከላይ የጠቀስነው ሰነድ "የኢንስፔክሽን የትኩረት መስኮች" መለኪያዎችንም ግብአት፣ ሂደትና ውጤት መሆናቸውን ከገለፀ በኋላ እያንዳንዳቸው የየራሳቸው የትኩረት መስኮች እንዳሏቸውም አስቀምጧል። (1 እና 2 በግብዓት /Input/ አቅጣጫ፤ 3 እና 4 በሂደት /Process/ አቅጣጫ፤ እንዲሁም 5 በውጤት /Outcome/ ትይዩ መቀመጣቸውን ከወዲሁ ማስታወስ ያስፈልጋል።)

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የተቋሙና የኮሌጁ ሕንፃዎች (Training Facilities)፣ የሰው ኃይልና የፋይናንስ አቅም (የትኩረት መስክ 1)፤ የጥራት ማሻሻያ ለውጥ ትግበራ እና ምቹ የስልጠና አካባቢ (የትኩረት መስክ 2)፤ የውጤት ተኮር አሰለጣጠን ሂደት (የትኩረት መስክ 3)፤ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ማሰልጠኛ ተቋሙ/ኮሌጁ ከባለድርሻ አካላትና ከማህበረሰብ አገልግሎት ጋር ያለው ግንኙነት (የትኩረት መስክ 4)፤ ብቁ፣ ተወዳዳሪና ሥራ ፈጣሪ ባለሙያ ማፍራት የሚችል ጥራቱ የተረጋገጠ ተቋም/ ኮሌጅ መፍጠር (የትኩረት መስክ 5)።

በማጠቃለያው ቀዳሚ መስመር ላይ "ኢንስፔክሽን የተቋማትን/የኮሌጆችን ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመለየት ጠንካራ ጎኖችን በበለጠ ለማጠናከር፣ ክፍተቶችን ለማረም ወይም ለማስተካከል ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡" የሚለው ይህ ሰነድ ከላይ ያልነውን ብቻ አይደለም የሚለው፤ የኢንስፔክሽንን ወሳኝ ሚናንና የሕግ ማእቀፍ የተበጀለት መሆኑንም "በኢንስፔክሽን መመሪያ ቁጥር 03/2012 ዓ.ም ገፅ 18 ተራ ቁጥር 16 ንዑስ ቁጥር 3 ላይ በተቀመጠው መሠረት አንድ ኮሌጅ ደረጃ 1 ሆኖ ከ40% በታች ውጤት ካገኘ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንደሚዘጋ በማስቀመጡ ዳሎል ቢዝነስና ቴክኖሎጂ ኮሌጅ እና ባዮስ ቢዝነስ ኮሌጅ ደረጃቸው ከ40% በታች በመሆኑ በቀጥታ እንዲዘጉና ተጠያቂ እንዲሆኑ መደረግ ይኖርበታል።" ሲል ከነ ውጤቱ ያስቀምጣል። ከዚህ የምንረዳው ለተቋማት ዋናው ህልውናቸው የኢንስፔክሽንን ፈተና ማለፍ ወይም አለማለፍ መሆኑን ሲሆን፤ ጥያቄው በየ ጥጋ ጥጉ፣ ጋራ ሸንተረሩ፣ ወንዝና ተራራው ... ያሉት እነ እንቶኔ ከዚሁ ከኢንስፔክሽን አኳያ ፈተናውን አልፈው ነው ወይስ ታልፈው ህልውናቸው እዚህ ድረስ ሊዘልቅ የቻለው የሚለው ሲሆን፤ መልሱን ሳይሆን አስተያየቱን ለባለሙያ ትተነው እናልፋለን። ("እውነት እዚህ አገር ኢንስፔክሽን ቢኖር ኖሮ ተቋማት በአደባባይ የዲግሪ መቸብቸቢያ ገበያቸው እንዲህ ይደራ ነበርን?" በማለት የሚጠይቁ አስተያየት ሰጪዎችን አስተያየት እዚህ አላካተትንም እንጂ፤ ብናካትትማ ...)

ይህንን ሀሳብ እዚህ ልናነሳ የቻልነው በዚሁ ሰነድ (ፓወርፖይንት 18) ላይ "[...] 3 ኮሌጆች ከ80% በላይ ውጤት በማግኘት የጥራት ስታንዳርዱን ያሟሉ በመሆናቸው ተሞክሮዎቻቸውን የሚያስፉበትንና በላቀ ደረጃ ስታንዳርዱን እንዲያሟሉ የሚደገፉበትን አቅጣጫ ልንከተል ይገባል፡፡" የሚል በመኖሩ ሲሆን፤ "3 ኮሌጆች" ብቻ ለሚለው አፅንኦት በመስጠት ነው። "የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል" ይባላል። የትምህርት ነገርስ? ያወያያል፤ ያነጋግራል፤ ያመራምራል።

ትምህርትን ከማስፋፋት ጎን ለጎን ጥራቱን ለማረጋገጥ የሚረዳ ስሌቶችን በመንደፍ በትምህርት ቤቶች ለመማር ማስተማሩ አጋዥ የሆኑትን የትምህርት ግብዓት፣ ሂደትና ውጤት በማሻሻል የተማሪዎችን እውቀት፣ ክሂሎትና አመለካከት ለማጎልበት በ1999 ዓ.ም የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ ተቀርፆ በሁሉም የአገራችን ክልሎች በመተግበር ላይ ነው፡፡ ፓኬጁ የመምህራን ልማት፤ የሥርዓተ ትምህርት፣ መጻሕፍትና ምዘና፤ የትምህርት ቤት መሻሻል፣ የትምህርት አመራርና አስተዳደር፤ የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ እንዲሁም የሥነ ዜጋና ሥነ ምግባር መርሀ ግብሮችን አካቷል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በሁሉም የአገሪቱ ክልሎች በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የመርሀ ግብሮቹን አፈጻጸም ለመገምገም የሚያስችል የኢንስፔክሽን ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኗል፡፡

ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች እንደሚያሳዩት በትምህርት ቤቶች የሚካሄድ ተከታታይ ኢንስፔክሽን የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻልና የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ የኢንስፔክሽን የግምገማ ውጤት የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ በተለይም ደግሞ የትምህርት ቤት ማሻሻያ መርሀ ግብር አተገባበርን በተመለከተ መረጃ የሚሰጥ ሲሆን በዚህም ትምህርት ቤቶች ቀዳሚ የትኩረት አቅጣጫ መሆን ያለባቸውን ለመለየት እንዲረዳቸው የሚያካሂዱት ግለ-ግምገማ ተገቢውን ሂደት የተከተለ መሆኑን ለመፈተሽና የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመጠቆም የበኩሉን ድርሻ ያበረክታል፡፡

የኢትዮጵያን ትምህርት፣ ትምህርት ፖሊሲና አጠቃላይ ሥርዓተ ትምህርቱን በተመለከተ በየጊዜው የተለያዩ መረጃዎችን የምናገኝ ሲሆን፤ አንዱም በ2016 የወጣውና "ዓለም ባንክ በዲሴበር 7/2012 በ221 ገጽ በዘጠኝ ምዕራፍ በሰጡት መግለጫ አንኳር ነገሮችን አንስተዋል። እነዚህም አንኳር ጉዳዮችን በሰፊው በማተት የችግሩን አሳሳቢነት በማጉላት መንግሥት በአስቸኳይ እርምት መውሰድ እንዳለበት በአንክሮ ያስጠነቀቀ ሲሆን ችግሩንም በአፋጣኝ መግታት ካልተቻለ በአገርና በሕዝብ ላይ ሊያመጣ የሚችለውን ችግር በግምገማው አስቀምጧል።" የሚለው ነው። ከላይ እንደተመለከትነው ከሆነ ይህንን የሚያክል ችግር ከመፍታት አኳያ፣ ምንም እንኳን ብቸኛው ባይሆንም፣ ኢንስፔክሽን የመሪነት ሚናውን ይጫወታል ማለት ነው።

ሁላችንም እንደምናውቀው፣ በአገራችን ትምህርትን የተመለከቱ አደረጃጀቶች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም። "አዳዲስ የትምህርት አደረጃጀቶች" በሚል ሁሌም ሲጣልና ሲነሳ፤ የዛሬው ለነገ ሳይሆን ሲቀርና ለሌላ አዲስ ቦታውን ሲለቅ ነው ስናይና ስንሰማ የኖርነው። ኮማንድ ፖስት፤ አንድ ለአምስት፤ BPR (መሠረታዊ የሥራ ሂደት)፤ የመምህራን ውጤት ተኮር፤ የልማት ሰራዊት፤ ተሀድሶ፤ የለውጥ ሰራዊት፤ ተማሪን ያማከለ የመማሪ-ማስተማር ሂደት፤ ሪፎርሜሽን (Reformation) ... እና የመሳሰሉ አደረጃጀቶች አየሩን ቢናኙበትም የሚፈለገው ጋ ደርሰው ውጤትን ሊያስገኙ ግን አልተቻላቸውም። ለምን? ከተባሉት፣ ከተነገሩትና ከተደረጉ ጥናቶች የምንረዳው አቢይ ጉዳይ ቢኖር እነዚህ ሁሉ አደረጃጀቶች በበቂ የኢንስፔክሽን ተግባርና ባለሙያው ካልተደገፉ ምንም ዓይነት ውጤት ሊያመጡ አለመቻላቸውን ነው።

ጉዳዩ ምን ላይ እንዳለ፣ የት እንደ ደረሰ ባይታወቅም "የትምህርት ጥራት ችግርን ለመፍታት "የከፍተኛ ትምህርት ጥራት ምክር ቤት" ማቋቋም አስገዳጅ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። ምክር ቤቱ በአገሪቱ የሚገኙ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የትምህርት ጥራትን ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲያረጋግጡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና ምሩቃንን ለማፍራት ፋይዳ የሚኖረው ገለልተኛ ምክር ቤት መሆኑ ተነግሯል። በሣይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር በአዲስ አበባ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ግቢ ውስጥ በተዘጋጀው የከፍተኛ ትምህርት ጥራት ምክር ቤት ምስረታ ላይ . . ." የሚል ዜና ይኸው ጋዜጣ በአንድ ወቅት ማስነበቡ ይታወሳል። ጥራት ጉዳይ እዚህ ድረስ አሳሳቢ ሆኗል ለማለት ነው።

በአጠቃላይ፣ በሌላ ዝግጅት በዚሁ በኢንስፔክሽን ጉዳይ ላይ ከባለሙያ ጋር ቆይታ የምናደርግ መሆናችን እንዳለ ሆኖ፤ ከላይ ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው ለአንድ ተቋም ውጤታማነት የኢንስፔክሽን (በተለይ የውጪ) ሥራ ድርሻው በቀላሉ የሚታይ አይደለም። በመሆኑ ከተነሳንበት አኳያ ጉዳዩን ከትምህርት አንፃር ተመለከትነው እንጂ በሁሉም ተቋም ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባው መሆኑን መረዳት ይቻላል። በተለይ፣ በተለይም በትምህርቱ ዘርፍና ትውልድ ላይ እየደረሰ ካለው አደጋ (ብዙዎች "የትምህርት ጥራት ኪሳራ" ይሉታል) አኳያ ኢንስፔክሽንን ጨምሮ በርካታ ሥራዎች ሊሠሩ ይገባል እንላለን። "አዲስ አበባን በትምህርት ጥራት አርአያ የማድረግ እንቅስቃሴ" በሚልና ሌሎች ጽሑፎቻችን ለመግለፅ እንደ ሞከርነው ሁሉ በያዝነው አመት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ስልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ እየሠራ ያለው ተግባር የሚበረታታ ሲሆን፤ ሌሎችም የእሱን አርአያነት በመከተል የትምህርቱን ዘርፍ በፍጥነት ሊታደጉት ይገባል። ለዚህ ደግሞ ዓይነተኛው መሣሪያ ኢንስፔክሽን ነውና "ቺርስ ኢንስፔክሽን!!!" እንላለን።

# ‹‹መንግሥት ድጎማን በሚመለከት በሚወስደው ርምጃ ጥናት ላይ ተመስርቶ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል››

*- ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ*
*የምጣኔ ሀብት ባለሙያ*

**ምሕረት ሞገስ**

ድጎማ የሚል ቃል ሲነሳ ተደጋግሞ የሚነገረው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በድጎማ ላይ የተንጠለጠለ ስለመሆኑ ነው። በእርግጥም ድጎማ እንደኪሣራ መታሰብ ባይኖርበትም መንግሥት በሁሉም ነገሮች ላይ ድጎማ ማድረጉ ተገቢ ስላለመሆኑ ይገለፃል። ምክንያቱም በመንግሥት ላይ ጫና በርትቶ ሲያንገዳግደው ኢኮኖሚው አደጋ ላይ ስለሚወድቅ አደጋው የከፋ እና የሰፋ ስለሚሆን። ይህንን መነሻ በማድረግ መንግሥት ከድጎማ ወጥቶ ኢኮኖሚውን ለገበያ ክፍት ለማድረግ ጥናት ከማካሔድ ጀምሮ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ መግባት አለበት የሚለውን ሃሳብ መሠረት በማድረግ መንግሥት ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እየገባ ስለመሆኑ እየተገለፀ ይገኛል።

መንግሥት ጫናው ሲበዛበት እያቃተው ማራገፍ ሲጀምር በጥንቃቄ ካደረገው ጉዳቱ አነስተኛ ጥቅሙ ደግሞ ከፍተኛ ይሆናል። በትክክል መደጎም ያለበት ኅብረተሰብ ጉልህ ጫና እንደማይደርስበት ተደርጎ እንዴት እንደተደጎመ ለማሳየት ያህል የኤሌክትሪክ አገልግሎት ድጎማ መቀነስን ተከትሎ ከ12 ዓመታት ቆይታ በኋላ የአገልግሎት ዋጋ ማሻሻያ በመጥቀስ ድጎማ በዝርዝር ታይቶ በጥንቃቄ ከተነሳ የከፋ ጉዳት አያስከትልም የሚሉ ወገኖችም አሉ። የመንግሥት የኤሌክትሪክ አገልግሎት ድጎማ መሳሳት ለጊዜውም ቢሆን ብዙ የኅብረተሰብ ክፍልን ያነጋገረ እና በወቅቱ ፈጥሮት የነበረው ጫጫታ የሚዘነጋ ባይሆንም በዓመታት ተከፋፍሎ ከታኅሣሥ 2011 ዓ.ም ጀምሮ ማሻሻያው ሲተገበር ዝቅተኛ ገቢ ያለውን ተገልጋይ ጉልህ ጉዳት እንዳይደርስበት ጥንቃቄ በመደረጉ መደጎም ያለበት ኅብረተሰብ ተደጉሞ የመንግሥት ጫናም ቀንሶለታል።

መንግሥት ብዙኃኑን ሕዝብ ለመጥቀምና ኢኮኖሚውን ለማረጋጋት በሚል ከልክ ያለፈና በበቂ ጥናት ላይ ያልተመሠረተ ድጎማ ማቅረብ ምንም እንኳ በኢኮኖሚው ውስጥ ያለውን ከፍተኛ የኑሮ ውድነት ጉዳት ለመቀነስ የሚያግዝ ቢሆንም መንግሥት የሚያጣው እና መደጎም ያለበት ኅብረተሰብ የሚያገኘው ጥቅም ሲነፃፀር ውጤቱ ሰፊ ልዩነት እንዳለው በመጥቀስ በኤሌክትሪክ ብቻ ሳይሆን የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ሌሎች ድጎማዎችንም መቀነስ እና ማንሳት እንደሚኖርበት የምጣኔ ሀብት ባለሞያዎች ይናገራሉ። በምሳሌነት ዘይት፣ ስኳር፣ ሩዝ፣ የሕፃናት ምግብን በመደጎም እና ከቀረጥ ነፃ በማስገባት ተጠቃሚው በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኝ መንግሥት ድጋፍ ቢያደርግም ኅብረተሰቡ ግን መንግሥት ከሚያጣው ጋር የተመጣጠነ ጥቅም እያገኘ አይደለም። እነዚህ ምርቶች ከቀረጥ ነፃ በማስገባት መንግሥት ብዙ መሠረተ ልማቶችን የሚሠራበትን በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ እያጣ ይገኛል።

በዋናነት ሰሞኑን መነጋገሪያ የሆነው ነዳጅም ቢሆን ነዳጅ አምራች አገራት ሳይቀሩ በዓለም የነዳጅ ዋጋ ሲመሩ ኢትዮጵያ ግን የሕዝቡ የገቢ አቅም አነስተኛ ነው በማለት ከፍተኛ ድጎማ በማድረግ በነዳጅ ብቻ 100 ቢሊዮን ብር ጉድለት በመንግሥት እየተሸፈነ መቆየቱ በአጠቃላይ የአገሪቷ ወገብ እንዲጎብጥ በማድረጉ ከጥቅል ድጎማ ይልቅ ወደ ዝርዝር ድጎማ መግባት አስፈላጊ መሆኑ ተገልፆ ሥራዎች መሠራት ጀምረዋል። በተቃራኒው ነዳጅ ከአጠቃላይ ሊባል ከሚችል ምርት ጋር የተገናኘ በመሆኑ ድጎማ መቀነስም ሆነ ማንሳት አደጋው የከፋ ሊሆን እንደሚችል በመጠቆም ጥንቃቄ ማድረግ ያሻል የሚል የምጣኔ ሀብት ባለሞያዎች አስተያየትም እየተስተጋባ ነው። ይህን እያሉ ካሉ የምጣኔ ሀብት ባለሞያዎች መካከል ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ አንዱ ናቸው። ከድጎማ ጋር ተያይዞ እርሳቸውን ጠይቀን የመለሱልንን እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

> **ድጎማ ሰላም እና ደህንነት ላይ የራሱ ሚና ይኖረዋል። ድጎማ ሲቀር ሰላም ይጠፋል። ይሔ ደግሞ ለመንግሥትም አደጋ ይሆናል**



ፎቶ፡ በኢዩብ ተፈሪ

**አዲስ ዘመን፡- ድጎማ ምንድን ነው ከሚለው እንጀምር?**

**ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፡-** ድጎማ ሕዝብን ለመደጎም የሚሰጥ ነው። ድጎማ አንዳንድ ችግሮች ሲመጡ ሰዎች እንዳይቸገሩ ታስቦ የሚሰጥ ድጋፍ ነው። አሁን በቅርቡ ለምሳሌ የኮቪድ -19 መከሰቱን ተከትሎ ዩናይትድ ስቴትስም ሆነች የአውሮፓ ሁሉም አገራት ዜጎቻቸው ሥራ ስላልሠሩ በማለት በየሂሳብ ቁጥራቸው በርከት ያለ ገንዘብ ልከዋል። በትሪሊየን የሚቆጠር ገንዘብ አውጥተዋል። ይህ በአውሮፓም ሆነ በሰሜን አሜሪካ የተፈፀመ ነው። ሌሎችም የአፍሪካ አገሮች በተለያየ መልኩ ሕዝባቸው እንዳይጎዳ በማሰብ ይደጉማሉ። ለምሳሌ መንግሥታት ከውጭ የሚመጣ ነዳጅን ይደጉማሉ። ምክንያቱም ነዳጅ የልማት ሞተር ነው።


ነዳጅ ሲጨምር ትራንስፖርት ስለሚጨምር የሁሉም የሸቀጦች ዋጋ ይጨምራል። ሕዝብ የሚንቀሳቀስበት ዋጋ ይጨምራል። ስለዚህ እኛም አገር ለረዥም ጊዜ ነዳጅ በድጎማ ላይ ነበር። በተጨማሪ አስፈላጊ የሚባሉ ሰዎች በየቀኑ የሚጠቀሟቸው ምግቦች ይደጎማሉ። ለምሳሌ ግብፅ፣ ሱዳን እና ሌሎችም የአፍሪካ አገሮች ምግቦች እንዳይወደዱ እና ሕዝቡ እንዳይቸገር ይደጉማሉ። በግብፅ ለ50 ዓመታት የዳቦ ዋጋ አልተቀየረም። ሱዳን ለረዥም ጊዜ የዳቦም ሆነ የሌሎች ምግቦች ድጎማ ነበር። ልክ ድጎማው ሲነሳ አልበሽርን ሕዝቡ ‹‹ሆ›› ብሎ አባርሮታል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለዚህ ድጎማ ለሕዝብ ብቻ ሳይሆን ለመንግሥትም ሲባል የሚካሔድ ነው ማለት ይቻላል?**

**ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፡-** በትክክል ድጎማ ለሕዝብ ብቻ አይደለም፤ ለመንግሥትም የሚጠቅም ነው። ምክንያቱም ድጎማ ሰላም እና ደህንነት ላይ የራሱ ሚና ይኖረዋል። ድጎማ ሲቀር ሰላም ይጠፋል። ይሔ ደግሞ ለመንግሥትም አደጋ ይሆናል። ምክንያቱም ሕዝብ ተጎዳሁ ብሎ ሲያምን ወደ ሌላ ነገር ይገባል። በአብዛኛው በተለይ የኑሮ ውድነት ሲያጋጥም ድጎማ ከሌለ ችግር ይፈጠራል። የዓለም የገንዘብ ድርጅት እና የዓለም ባንክ በ1980ዎቹ መዋቅራዊ የኢኮኖሚ ለውጥ ብለው በሚያስተገብሩበት ጊዜ ወደ 40 አገሮች የመንግሥት ግልበጣ ተደርጓል። ይህ የሆነበት ምክንያት ዓለም አቀፍ ድርጅቶቹ የሚሉት መንግሥታት ድጎማ እንዲያነሱ ሲገፋፉ፤ ሕዝቡ ሠርቶ መክፈል ካልቻለ የመንግሥት የገንዘብ ቋት ባዶ ይሆናል በማለት ነበር። በተጨማሪ ልማት አይኖርም፤ ስለዚህ ሰፊ ልማት እንዲኖር እና ሕዝቡ እንዲንቀሳቀስ ድጎማ አንሱ ይሉ ነበር። ነገር ግን መንግሥታቱ ድጎማ ሲያነሱ እነርሱ እንዳሉት አልሆነም። እንዲያውም ሕዝቡ ተነሳ።

ድጎማ የተነሳበት ሕዝብ ወደ ልማት ከመግባት ይልቅ ወደ አመፅ ሔደ። የሚያሳዝነው ሕዝቡ ሲነሳ ደግሞ ምንም እንኳ ወጣቱ እና ሌላ ሌላውም በሙሉ በአንድነት ‹‹ሆ›› ብሎ ቢወጣም ተደራጅቶ ያለው ወታደር ብቻ

# ወቅታዊ



## ድጎማ ሲነሳ የመንግሥት ጫና ይነሳል። ነገር ግን መንግሥት ድጎማውን በሚያነሳበት ጊዜ ሌሎቹ የኢኮኖሚ አውታሮች እየሠሩ ነው ወይ ሕዝቡ በዚህ ሊንቀሳቀስ ይችላል ወይ የሚለው በደንብ መታየት አለበት

በመሆኑ ወታደሩ ስልጣኑን ይረከባል። ለዚህ በምሳሌነት ማሊ፣ ጊኒ እና ሌሎችንም አገሮች መጥቀስ ይቻላል። በእነዚህ አገራት ያ ሁሉ ችግር የተከሰተው ከድጎማ ጋር ተያይዞ ነው። ድጎማዎች በአጠቃላይ በበጀት ተይዘው ለሕዝብ የሚሰጥ ሲሆን በተለይም ምግብ ነክ ነገሮች ተራው ኅብረተሰብ መጠቀም እንዲችል ማድረግ ትክክል ነው። በተቃራኒው ከሆነ ችግሩ ቀላል አይሆንም።

**አዲስ ዘመን፡- ድጎማ መሰጠት ያለበት በትክክል ለማን ነው?**

**ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፡-** አንዳንድ በኅብረተሰቡ ውስጥ በደል የደረሰባቸው ናቸው የሚባሉ ቡድኖች እንዲደገፉ መደረግ ይኖርበታል። ለምሳሌ የሴቶች ፖሊሲ ሲወጣ ፣ የሕፃናት ፖሊሲ ሲወጣ፣ የአቅመ ደካሞች ፖሊሲ ሲወጣ እንዲሁም አካል ጉዳተኞች በሙሉ የሚጠቀሙባቸው ነገሮች ድጎማ የሚደረግበት ሁኔታ ይኖራል። ሌላው ደግሞ በጤናው ረገድ የሆስፒታል የአገልግሎት ዋጋ ከፍተኛ ሆኖ ዜጎችን እንዳይጎዳ፣ የመድኃኒት ዋጋ እንዳይንር በብዙ አገሮች ድጎማ ይደረጋል። ለምሳሌ አውሮፓ ለዜጎቻቸው በነፃ ሕክምና ይሠጣሉ። መድኃኒት በሙሉ ነፃ ነው። በሌላ በኩል የርዕዮተ ዓለም ጉዳይም አለ። ሶሻሊስት ዘመም የሆኑ ክርስቲያን ዴሞክራቶች፣ ሶሻሊስት ዘመሞች ዋናው ትኩረታቸው የሕዝባቸው ደህንነት ነው። ስለዚህ ድጎማን ያበረታታሉ።

በሌላ በኩል ሕዝባዊ ነን ባይ መንግሥታት እየተነሱ ድጎማዎችን እያነሱ ሕዝቡ በውድድር መኖር አለበት በማለት አቋም ይይዛሉ። እነኚህኞቹ ስልጣን ላይ ለመውጣት የሚሉት ከአፍሪካ የመጡ ስደተኞች ሥራችንን ወሰዱ፤ ለምሳሌ ከሶሪያ በስደት የሔዱትን በመጥቀስ ሙስሊሞች አገራችን ውስጥ ገቡብን ይላሉ። ስልጣን ላይ ከወጡ በኋላ ግን ኢኮኖሚውን ያደቃሉ። ለምሳሌ ከዩክሬን ጋር ተያይዞ ፑቲን ከምዕራቡ ዓለም ጋር የገቡበት ጭቅጭቅ ሕዝባዊ ናቸው የሚባሉትን ሊያጠፋቸው ይችላል። ምክንያቱም አሁን ቀኝ ዘመም የመንግሥት አስተዳደር ሳይሆን የድሮዎቹ አገር በመጠበቅ የሕዝብን ደህንነት በማረጋገጥ የነበሩ ፖለቲካ ፓርቲዎች ስልጣን ላይ ሊወጡ ይችላሉ የሚል ግምት አለ።

**አዲስ ዘመን፡- የሱዳንን የአልበሽርን ተሞክሮ በማየት ድጎማ ድሃውን ማኅበረሰብ ብቻ ሳይሆን መንግሥትንም ይጠቅማል ብለዋል። እስኪ በደንብ አብራርተው ድጎማ በትክክል ማንን ይጠቅማል?**

**ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፡-** ድጎማ ተብሎ ሲነሳ ዋነኛው ትኩረቱ የሰዎች ደህንነት ነው። እዚህ ላይ የመንግሥት ደህንነት እና የአገር ደህንነት ሁሉ የሚካተቱበት ነው። የሰዎች ደህንነት ሲባል የእያንዳንዱ ግለሰብ ደህንነት ነው። ግለሰቦች ደህና ካልሆኑ በተለይ እንደአፍሪካ ባለች ከፍተኛ ቁጥር ባለባት አህጉር ውስጥ ያሉ አገራት የወጣቶች ደህንነት ትልቅ ጉዳይ ነው። ወጣት ተምሮ ሥራ የሚያገኝበት ዕድል ከሌለ የራሳቸውን ሥራ የሚፈጥሩበት ሁኔታ ላይ ፖሊሲዎች እና የመንግሥት የአስተዳደር ሥርዓት ሲታይ አስቸጋሪ ካልሆነ ድጎማ ሲነሳ ተያይዞ አመፅ ይቀሰቀሳል። በዚህ ጊዜ ወጣቱ ወደ መበጥበጥ ይገባል። ነገር ግን ወጣቱ ሥልጣን አይይዝም። ስልጣን የሚይዘው ወታደር ይሆናል። ወታደሩ ደግሞ ካለፈውም መንግሥት የባሰ ይሆናል። ለዚህ ማሳያው የደርግ ዘመንን እንደምሳሌ ማቅረብ ይቻላል።

በወታደር አገዛዝ ሕዝብን መግደል እና መጨረስ ታይቷል። በሌላ በኩል ከወታደሩ ውጪ ደግሞ የሽምቅ ተዋጊዎች ወደ ስልጣን የሚወጡበት ሁኔታ ይፈጠራል። ለምሳሌ ኢህአዴግን መጥቀስ ይቻላል። በሌሎች አገሮችም እንደታየው የሽምቅ ተዋጊዎችም ሆኑ ወታደሮቹ የሚታያቸው ጠላትን ማጥፋት ብቻ ነው። ምክንያቱም የሚሠለጥኑት ጠላት ሲታይ መግደል ላይ ብቻ በመሆኑ ጠላትን በማነጋገር የሚያምኑ አይደሉም። ስለዚህ መንግሥታት ለራሳቸው ሲሉ ድጎማ ማድረግ አለባቸው። ዋናው ነገር ግን የኢኮኖሚ ፖሊሲው መልክ መያዝ አለበት። አሁን ዚምባቡዌ ገንዘቡ ዋጋ አጥቶ የገንዘብ ግሽበቱ ሰማይ ወጥቶ መጨረሻ ላይ ብዙ ዓመት የቆዩ ሰውዬን ፕሬዚዳንት ሙጋቤን ከስልጣናቸው ያወረዳቸው የራሳቸው ፓርቲ ነው። በሽርም የራሳቸው ወታደሮች ናቸው ያወረዷቸው። ስለዚህ ይህ ሲታይ ድጎማ ለመሪዎችም ሆነ ለአጠቃላይ የአገሪቱ ባለስልጣናት የሚጠቅም ነው።

ድጎማ ሲነሳ ሁሉንም የሚጎዳ ይሆናል። ለምሳሌ ላይቤሪያ ላይ ፕሬዚዳንቱንም ሚኒስትሮቹንም ገድለው አስከሬናቸውን ሕዝብ እንዲያየው ብለው በአደባባይ ፀሐይ ላይ ያዋሉት በዚሁ ምክንያት ነው። አብዛኛውን ጊዜ አፍሪካ ውስጥ የመንግሥት ግልበጣ የሚካሔደው በዚሁ ምክንያት ነው። እኛም አገር በአጼ ኃይለሥላሴ ጊዜ ነዳጅ በሳንቲም ቤት ትንሽ ጨመረ ተብሎ ነገር ተንቀሳቀሰ። ታክሲ በጠበጠ ተማሪም ሲናገር ኖሯል። መሬት ላራሹ እና የብሔር ብሔረሰብ መብት ተባለ፤ የደርግ ወታደራዊ አስተዳደር ተቋቋመ። ደርግ ወደ ስልጣን ሲመጣ መጀመሪያ 60ዎቹን አረደ። ይህን ተከትሎ በነጭ ሽብር እና በቀይ ሽብር እንዲሁም በረሃብ ወደ ሁለት ሚሊዮን ሕዝብ አለቀ። 28 ነፃ አውጪ ግንባሮች ተቋቁመው ደግሞ ደርግ ሲወድቅ የሽግግር መንግሥት ተቋቋመ። ስለዚህ መንግሥት ድጎማን በሚመለከት በሚወስደው ርምጃ ጥናት ላይ ተመስርቶ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል።

**አዲስ ዘመን፡- የድጎማ መነሳት የሚጠቅመው ማንን ነው?**

**ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፡-** የድጎማ መነሳት የሚጠቅመው መንግሥትን ብቻ ነው። መንግሥት ምናልባት በጀቱን ለማስተካከል ያግዘዋል። ነገር ግን ድጎማ የሚደረገው በሁለት መንገድ ነው። አንዱ ለምሳሌ ነዳጅን መጥቀስ ይቻላል። እኔ ወደ 26 አገራት ሠርቻለሁ። በአፍሪካ አገር በሙሉ ከአንድ ዶላር በታች ቤንዚል የለም። ይሔ ከዛሬ 25 ዓመት በፊት ነው። በአገራችን ግን ነዳጅ ለረዥም ጊዜ ሲደጎም የኖረ ነው፤ ምክንያት አለው። አንደኛው የኅብረተሰቡ ገቢ ዝቅተኛ መሆን ሲሆን፤ ሌላው በኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ደረጃ እየሔደ ያለ እንደኢትዮጵያ ዓይነት ኢኮኖሚ ነዳጅ መደጎሙ መጨረሻ ላይ ኅብረተሰቡ ሠርቶ አምጥቶ በሚከፍለው ታክስ አገሪቱ ላይ በሚያመጣው የኢኮኖሚው ጥቅም ይሸፈናል ተብሎ ታስቦ ነው።

ይሔ ድጎማ ሲነሳ የመንግሥት ጫና ይነሳል። ነገር ግን መንግሥት ድጎማውን በሚያነሳበት ጊዜ ሌሎቹ የኢኮኖሚ አውታሮች እየሠሩ ነው ወይ ሕዝቡ በዚህ ሊንቀሳቀስ ይችላል ወይ የሚለው በደንብ መታየት አለበት። ለምሳሌ መንግሥት የነዳጅ ድጎማን ቢያነሳ ሕዝቡ እንዴት ይንቀሳቀሳል የሚለው ሊጤን ይገባዋል። ድጎማ ከሰብአዊ ዕርዳታ ተለይቶ የሚታይ አይደለም። አገራችን ውስጥ ብዙ ግጭቶች አሉ። በሌላ በኩል በድርቁ ምክንያት ብዙ የሰብአዊ እርዳታ የሚፈልጉም አሉ። ምግብ፣ መጠለያ እና መድኃኒት ይፈልጋሉ፤ የሚሰጣቸው በነፃ ነው። ድጎማ ከዚያ ትንሽ ከፍ ያለ እንጂ ያነሰ አይደለም። ድጎማ በቋሚነት ማድረግ ሳይሆን ጥናት እየተጠና ዩኒቨርሲቲዎች በየክልሉ በየአካባቢው በሚያርጉት ጥናት ላይ በመመስረት በተለያየ መልኩ ድጎማ ማድረግ ይቻላል። በመጨረሻም ይሔ የአገሪቱን ደህንነት እና የውስጥ መረጋጋትን የሚያረጋግጥ ነው።

የኢኮኖሚ ችግር ሁልጊዜ ለሕዝቦች መነሳሳት ዋና ምክንያት ነው። ሕዝቦች በሚነሳሱበት ጊዜ ደግሞ መሪ የሌለው የሕዝብ መነሳሳት ጉዳዩን አስቸጋሪ ያደርገዋል። ምክንያቱም መሪ ቢኖራቸው ከመሪዎቹ ጋር ተነጋግሮ ችግሮችን መፍታት ይቻላል። መሪ ከሌለ ግን በየቦታው የሚነሳው የሕዝብ ብሶት ወደ ፅንፈኝነት አምርቶ እርሻ እና ፋብሪካ ወደ ማቃጠል ገብቶ አገር ያፈርሳል። አገራችንም ውስጥ ብዙ አይተናል። መኪና ማቃጠል፤ ምግብ ወደ ከተማ እንዳይገባ መከልከል እና ሌሎችም ጥፋቶች ነበሩ። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲፈጠር ማነጋገር የሚቻልበት ሁኔታም አይኖርም። የፀጥታ ኃይሎቹ ደግሞ በጉልበት ፀጥታ ለማስከበር ሲሞክሩ ሌላ ቀውስ ይፈጠራል። ስለዚህ ጥንቃቄ ያሻል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም እጅግ አመሰግናለሁ።**

**ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፡-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ።

# ዓለም አቀፍ

## በደቡብ አፍሪካ በተከሰተው ጎርፍ የጠፉ ሰዎችን የመፈለጉ ሥራ አሁንም እንደቀጠለ ነው



በደቡብ አፍሪካ ኩዋዙሉ ናታል ግዛት ለቀናት የጣለውን ከባድ ዝናብ ተከትሎ በተከሰተው ጎርፍ የጠፉ ሰዎችን የመፈለጉ ሥራ አሁንም እንደቀጠለ ነው።የአደጋ ጊዜ ሠራተኞች በሕይወት የተረፉ ሰዎችን ለመፈለግ በሚያደርጉት ጥረት በመንገዳቸው ላይ ዝናብ በመኖሩ ፍለጋቸውን አዳጋች አድርጎባቸዋል።

ሂሮ ካንጋታ የደርባን ነዋሪ ነው። በጎርፉ ምክንያት ለዘመናት የደከመበትን ቤቱን አጥቷል።"ቤቴ እዚህ ነበር። ወንዙ ከቤቴ ጀርባ ስድስት ወይም ሰባት ሜትር ርቀት ላይ ነበርና ቤቴ ምንም አይሆንም ብዬ አስቤ ነበር" ይላል ሂሮ ካንጋታ በደርባን የሚገኘውን ቤቱን ፍርስራሽ እያመላከተ።

"በጣም ተጨንቄያለሁ። ምን እንደማደርግ አላውቅም።የት እንደምሄድም አላውቅም። ወደፊት የሚሆነውን አላውቅም። በእውነቱ ወደፊት የሚታየኝ ምንም ነገር የለም" ይላል።ሂሮ በጎርፉ ሳቢያ ጉዳት ካጋጠማቸው 40 ሺህ የሚጠጉ ሰዎች አንዱ ነው።ባለሥልጣናት እንደሚሉት 13 ሺህ 500 ቤቶች ወድመዋል። በርካቶችም ቤት አልባ ሆነው ያለመጠለያ፣ ምግብ እና ውሃ ቀርተዋል።

ከሂሮ ቤት አቅራቢያው ያለች አንዲት ሴት በበኩሏ ቤቷ ከመፍረሱ በፊት መሸሽ እንዳለባት ተናግራለች።" አሁን የማርፍበት ቦታ እፈልጋለሁ። አሁን ለልጆቼ ደህንነት ስል እየወጣሁ ነው። በጣም ከባድ ነው ግን በሕይወት ስለተረፍን ደግሞ ፈጣሪያችንን እናመሰግናለን" ብላለች።

እስካሁን በአደጋው 400 ሰዎች ሕይወታቸው ያለፈ ሲሆን ይህ ቁጥር ሊጨምር እንደሚችል ስጋት አለ። የአደጋ ጊዜ ሠራተኞችም በሕይወት የተረፈ ሰው ለማግኘት ፍለጋቸውን ቀጥለዋል።አንዳንድ የቁፋሮ ማሽን አሽከርካሪዎች ለፋሲካ በዓል በመሄዳቸው በሕይወት የተረፉ ሰዎችን የማፈላለግ ሥራው አደጋ ላይ ነው።ጊፍት ኦፍ ዘ ጊቨርስ የተባለ አንድ የእርዳታ ድርጅት የቁፋሮ ማሽኖች ላይ መሥራት ለሚችሉ ሰዎች ጥያቄ አቅርቧል።

ምናልባት ይህ ሊደርስ የሚችለው ሕይወትን ከመታደግ በተቃራኒ አስከሬኖችን ለማውጣት ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ አሁንም ነዋሪዎች በእጃቸው ፍርስራሹን እየቆፈሩ ነው።ንጹህ የመጠጥ ውሃ ፍለጋም ሌላኛው ፈተና ሆኗል። ካለፈው ሳምንት ጀምሮ በግዛቱ የተከሰተው ጎርፍ ቤቶችን አውድሟል፣ የኃይል መስመሮችን፣ መንገዶችን እና ድልድዮችን አፈራርሷል።

በሰሜን ደርባን በአማኦቲ ነዋሪዎች ከአንድ ከፈነዳ የቧንቧ መስመር ውሃ ለማግኘት ተሰባስበዋል።የወረፋው ሰልፍ ረጅም በመሆኑ ነዋሪዎች ተስፋቸው ተሟጧል።" ቤታችን ውስጥ ውሃ የለም። ምንም መሥራትም ሆነ መመገብ አንችልም። መታጠብ አንችልም። መንግሥት እንዲረዳን እንፈልጋለን" ሲል አንድ ነዋሪ ለቢቢሲ ተናግሯል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ወደ 300 የሚጠጉ ትምህርት ቤቶች እና የተወሰኑ የጤና ተቋማት ከጥቅም ውጭ ሆነዋል።የተወሰኑ ማኅበረሰቦችም መንገዶች እና ድልድዮች በመፈራረሳቸው ከሌላው አካባቢ ጋር መገናኘት እንዳይችሉ ሆነዋል።ፕሬዚዳንት ሲሪል ራማፎሳ በዚህ ሳምንት መጀመሪያ ላይ ወደ ግዛቱ አምርተው የደረሰውን ጉዳት ተመልክተዋል።ፕሬዚዳንቱ በወቅቱ የጎርፍ አደጋው "በአስርተ ዓመታት ውስጥ አስከፊው ጉዳት" ሲሉ መግለጻቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

## የእንግሊዙ ሊቀ ጳጳስ ዩኬ ጥገኝነት ጠያቂዎችን ወደ ሩዋንዳ ለመላክ ማቀዷን ኮነኑ



መንግሥት ጥገኝነት ጠያቂዎችን ከዩናይትድ ኪንግደም ወደ ሩዋንዳ ለመላክ የያዘው እቅድ " ከአምላክ ሥራ ጋር የሚቃረን ነው፤ ፈሪሃ አምላክ አይደለም" ሲሉ የካንተርበሪው ሊቀ ጳጳስ ተናገሩ።

ሊቀ ጳጳስ ጀስቲን ዌልቢ የፋሲካ በዓልን ምክንያት በማድረግ ባደረጉት ስብከት የክርስቶስ ትንሳኤ ኃላፊነታችንን የምንቀንስበት አይደለም" ብለዋል።ከዚህ በተጨማሪ ሊቀ ጳጳሱ በዩክሬን በሚካሄደው ጦርነት የተኩስ አቁም እንዲደረግ ጥሪ ያቀረቡ ሲሆን በኑሮ ውድነት ላይ ያላቸውን ስጋት ገልጸዋል።

መንግሥት ጥገኝነት ጠያቂዎችን ወደ ሩዋንዳ ለመላክ ለማቀዱ "የሰዎችን ሕይወት ከሕገ ወጥ አዘዋዋሪዎች ለመጠበቅ ለውጥ ያስፈልጋል" ሲል በምክንያት ያስረዳል።ይሁን እንጂ በሕገ ወጥ መንገድ ወደ ዩኬ የሚገቡ ስደተኞች የጥገኝነት ጥያቄያቸውን ለማቅረብ እና ጉዳያቸውን ለማስፈፀም ወደ ምስራቅ አፍሪካዊቷ አገር መላክን የሚያካትተው የ120 ሚሊዮን ፓውንድ እቅድ ከፍተኛ ተቃውሞ ገጥሞታል።

ከ160 በላይ የሚሆኑ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች እና ዘመቻ የሚያካሂዱ ቡድኖች በዚህ ሳምንት ይፋ የተደረገውን እቅድ "ጭካኔ የተሞላበት ነው" ሲሉ ሚኒስትሮች ሃሳባቸውን እንዲሰርዙ አሳስበዋል።

በተቃዋሚ ፓርቲዎች እና በአንዳንድ ወግ አጥባቂዎችም በኩልም እቅዱ ትችት ቀርቦበታል።በካንተርበሪ ካቴድራል ሊቀ ጳጳስ ዌልቢ " ጥገኝነት ጠያቂዎችን ወደ ውጭ አገር ለመላክ መታሰቡ ላይ ከባድ የሥነ ምግባር ጥያቄዎች" እንዳሉ ይናገራሉ።"ዝርዝሩ ለፖለቲካ ነው፤ መርሁ ግን በአምላክ ፍርድ ላይ መመርኮዝ አለበት፤ እንደዚህ መሆን ግን አይችልም" ብለዋል።

" ኃላፊነታችንን መሸከም ስላልቻልን ክርስቲያናዊ እሴቶች ላይ የተመሠረተች አገር እንደ አገር ያለንን አገራዊ ኃላፊነት መወጣት አልቻልንም። ይህም ለውድቀታችንና ለኃጢያታችን ኃላፊነት ከወሰደው እግዚአብሔር ባህርይ ጋር ተቃራኒ ነው" ብለዋል ሊቀ ጳጳሱ።

የአገር ውስጥ መሥሪያ ቤቱ ሊቀ ጳጳሱ በእቅዱ ላይ ለሰነዘሩት ትችት ምላሽ ዩኬ የተቸገሩትን በመደገፍ ኩሩ ታሪክ እንዳላት በመግለጽ እና የጥገኝነት ጥያቄዎችን በመቶ ሺዎች ለሚቆጠሩ ሰዎች " ደህንነቱ በተጠበቀና ሕጋዊ በሆነ መንገድ" የተሻለ ሕይወት መስጠታቸውን አስታውሷል።

ነገር ግን "ዓለም ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በዓለም አቀፍ ደረጃ የስደት ችግር ገጥሟታል እና ሕገ ወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች የሰዎችን ሕይወት አደጋ ላይ እንዳይጥሉ ለመከላከል እና የተበላሸውን ዓለም አቀፍ የጥገኝነት ሥርዓት ለማስተካከል ለውጥ ያስፈልጋል" ብለዋል ቃል አቀባዩ።

የአገር ውስጥ መሥሪያ ቤቱ አክሎም ሩዋንዳ " ደህንነቱ የተጠበቀ" እንደሆነች እና የጥገኝነት ጥያቄዎችን ተቀብላ በዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ሕጎች መሠረት እንደምታስተናግድ ገልጿል።የተባበሩት መንግሥታት ከፍተኛ የስደተኞች ኮሚሽን (ዩኤንኤችሲአር) ጥገኝነት ጠያቂዎችን ከዩናይትድ ኪንግደም ወደ ሩዋንዳ መላክ ዓለም አቀፍ ሕግን እንደሚጻረር መግለጹ የቢቢሲ ዘገባ ያመለክታል።

**ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም**

## ብቃት ያለውና ተወዳዳሪ ዜጋን ለማፍራት ዓላማ ያደረገው የመውጫ ፈተና

**እየሩስ ተስፋዬ**

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመውጫ ፈተናው ብቁና ተወዳዳሪ ምሩቃንን በማውጣት ጥራት ያለውና በአግባቡ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለገበያው ለማቅረብ እንደሚያስችል ተስፋ ተጥሎበታል። የትምህርት ሚኒስቴር ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፕሬዚዳንቶች ጋር በመውጫ ፈተና አሰጣጥ ዙሪያ አውደ ጥናት ማካሄዱ ይታወቃል። የትምህርት ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ሳሙኤል ክፍሌም በዩኒቨርሲቲዎች የሚሰጡት የመውጫ ፈተናዎች ተገቢውን እውቀት፣ ክህሎትና ስብዕና ያሟላ ምሩቅ ለማፍራት እንደሚያስችል መግለጻቸው የሚታወስ ነው።

ሚኒስቴሩ ይፋ እንዳደረገው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ አቅማቸው እስኪጎለብትና አካዳሚክ እና ተቋማዊ ነፃነታቸው ሙሉ በሙሉ እስኪረጋገጥ ድረስ ፈተናው በጊዜያዊነት በትምህርት ሚኒስቴር በኩል ይሆናል። የመውጫ ፈተናው ከመጪው ዓመት ጀምሮ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ እንደሚሰጥ እና ለዚህም ተገቢው ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል።

በኢትዮጵያ ብሮድካስት ኮርፖሬሽን ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በሚያዘጋጀው «ከትምህርት ገጽ» በተሰኘው ዝግጅት በትምህርት ሚኒስቴር የሳይንስ ምርምር ጉዳዮች ዳይሬክተር ጄነራል ዶክተር ሰለሞን ቢኖር እና በሚኒስቴሩ የአካዳሚክስ ጉዳዮች ዳይሬክተር ጄኔራል የሆኑት ዶክተር ኤባ ሚጀና በ2015 ዓ.ም ሊሰጥ በታቀደው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመውጫ ፈተናን አስመልክቶ ቆይታ አድርገዋል።

ዶክተር ሰለሞን ቢኖር እንደተናገሩት፤ በአገራችን መውጫ ፈተና መስጠት አዲስ አይደለም። ይሁን እንጂ በሁሉም መስኮች አስፈላጊነቱ ታይቶ ለመግባት ሲባል ከዚህ በፊት የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር



ዶክተር ሰለሞን ቢኖር



ዶክተር ኤባ ሚጄና

ለኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ በዚህ ዙሪያ ጥናት እንዲያጠና ኃላፊነት ሰጥቶት ነበረ። አካዳሚውም በመውጫ ፈተናው ላይ ሠፋ ያለ ጥናቶችን አቅርቧል።

የመውጫ ፈተና ተግባራዊ እንዲሆን ከአራት ዓመት በፊት ሥራዎች የተጀመሩ ሲሆን፤ እንዴት ነው የሚተገበረው? የሚለውን እና እንዲህ ያሉ ክለሳዎች ሲደረጉ በጥናትና ምርምር መሆን ስላለባቸው በጉዳዩ ላይ ጥናትና ምርምር ያደረጉ ምሁራን ጥሪ በቀረበላቸው መሠረት ከ20 በላይ ወረቀቶች ቀርበዋል። ከመውጫ ፈተና ጋር በተያያዘ ቀጥታ ተያያዥነት ያላቸው ስድስቱ ተመርጠው ከዚህ ቀደም በተዘጋጀው አውደ ጥናት ላይ እንዲቀርብ መደረጉን ይገልጻሉ።

የመውጫ ፈተና ተማሪዎች የተሻለ እውቀት፣ አመለካከትና ክህሎት እንዲኖራቸው የሚያደርግ ሲሆን፤ ከትምህርት ጥራት ጋርም ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው በመሆኑ ለቀጣሪዎች፣ ለቤተሰብና ለአገር ብቁ ዜጋን ከመፍጠር ባሻገርም በዓለም አቀፍ ደረጃ ለመቀጠር እንደሚያስችልም ዶክተር ሰለሞን ያስረዳሉ።

ዶክተር ኤባ በበኩላቸው፤ የመውጫ ፈተናው በሌላ አገር እንዴት እንደሚሰጥ፣ ምን ዓይነት ስልቶችን እንደሚጠቀሙ፣ በትምህርት ጥራትና አግባብነት ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደነበረው የጥናት ወረቀቶቹ በግልጽ ያሳዩ መሆናቸውን በመጠቆም፤ ጥናቶቹ በአጠቃላይ ትኩረት ያደረጉት የመውጫ ፈተና አስፈላጊነት፣ የማስፈፀሚያ ስልት፣ ስትራቴጂዎችና መደረግ ያለባቸውን ቅድመ ዝግጅት ያካተቱ በመሆናቸው ትልቅ ግብአት መሆኑን ያስረዳሉ። በእኛ አገር ከዚህ ቀደም በሕግ ትምህርትና በጤና ሳይንስ ትምህርት ላይ የመውጫ ፈተና ይሰጥ የነበረ በመሆኑ በዛ ላይ እውቀት ለመጨመርም አግዞናልም ይላሉ።

የመውጫ ፈተናዎች ላይ ከዚህ በፊት የነበሩትን ተሞክሮዎች በተመለከተ ማብራሪያ የሰጡት ዶክተር ኤባ፤ በተማሪዎች ውጤት ላይ ከፍተኛ መሻሻል አሳይቷል። እንዲሁም ተማሪዎች ተመርቀው ሲወጡ በቀጣሪዎች ዘንድ ተአማኒነት እንዲኖራቸው ያደረገ በመሆኑ በኢንዱስትሪው ተፈላጊነት እንዲኖራቸው አድርጓል። ምንም እንኳን የትምህርት ጥራትን አስመልክቶ ቀጣሪዎች በአብዛኛው ጊዜ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚመረቁ የተማሪዎች ብቃት አጠራጣሪ ነው የሚል እምነት ያላቸው በመሆኑ፤ ለኢንተርንሺፕ (ለተግባራዊ ልምምድ) እንኳን ሲወጡ ለመቀበል ፈቃደኛ አይሁኑ እንጂ እንዲህ ያለው ችግር የመውጫ ፈተና በሚወስዱ ተማሪዎች ላይ እምብዛም ሲገጥማቸው አይስተዋልም።

ከሌላው ዓለም በተገኘው ልምድ እንዲሁም በአገራችን በሕግና በጤና ትምህርት የሚሰጠው የመውጫ ፈተና ውጤቶች እንዳመላከቱት ከሆነ ፈተናው በሌሎች የትምህርት ፕሮግራሞች ላይ ማስፋት አስፈላጊ መሆኑን ዶክተር ኤባ ይጠቅሳሉ። ይህም ተማሪዎች ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት እንዲያገኙ እንደሚረዳቸው ያነሳሉ። በመሆኑም ፈተናው ተማሪዎችን ከማነቃቃቱ በተጨማሪም መምህራንም ከዚህ በፊት ሲሰጡበት ከነበረው ትምህርት አሰጣጥ የበለጠ ትኩረት አድርገው እንዲያስተምሩ ያደርጋቸዋል። የከፍተኛ ተቋማትም ቢሆኑ በልዩ ሁኔታ የሚሠሩ በመሆናቸው ተማሪዎች ብቃት ያላቸው ሆነው እንዲወጡ ከማድረግ አንጻር መነቃቃትን ይፈጥርላቸዋል።

ዶክተር ኤባ እንደገለጹት፤ በ2015 ዓ.ም የሚመረቁ ሁሉም ተማሪዎች የመውጫ ፈተናውን የሚወስዱ ሲሆን፤ ትምህርት ሚኒስቴር የማስተባበር ሚናውን በከፍተኛ ሁኔታ ይጫወታል። ከሙያ ማህበራትና ተቋማት ጋር በመሆንም ሥራው የሚሠራ እና ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ መመሪያ እና የአሠራር ሥርዓት ክለሳ ተደርጎባቸዋል።


በጦርነት የተጎዱ ትምህርት ተቋማትን መልሶ በማቋቋም ተማሪዎችን በጋራ ወደ ትምህርት ገበታቸው ለመመለስ አቅምዎ የፈቀደውን የገንዘብ መጠንድጋፍ ማድረግ -


የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የባንክ ሒሳብ ቁጥር - 1000448700945

በአጭር የጽሑፍ መልዕክት አቅም የፈቀደውን የብር መጠን ጽፎ ወደ 9222 በመላክ፣

በቴሌብር ድጋፍ ለማድረግ የቴሌብር ቁጥር 9222ን መጠቀም

በቴሌብር ዓለም አቀፍ ሀዋላ ከውጭ ሀገራት ድጋፍ ለማድረግ በ0993161616

# ስፖርት



## ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በዛሬው የቦስተን ማራቶን እንደሚያሸንፉ ይጠበቃል

**ብርሃን ፈይሳ**



የፈረንጆቹ ሚያዝያ ወር በገባ ሦስተኛው ሰኞ በሚከበረው የአርበኞች ቀን የሚካሄድ ዓመታዊ ውድድር ነው፤ የቦስተን ማራቶን። ከዓለም አንጋፋ የአትሌቲክስ ውድድሮች መካከል የሚጠቀሰው የቦስተን ማራቶን እአአ 1896 በአቴንስ የመጀመሪያውን ኦሊምፒክ ተከትሎ በቀጣዩ ዓመት (1897) ተጀመረ። በዓለም አትሌቲክስ ቀዳሚ ደረጃ ከተሰጣቸው ስድስቱ ታላላቅ የጎዳና ላይ ሩጫዎች መካከልም አንዱ ነው። እአአ 2020 በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ስጋት ምክንያት ውድድሩ ከመሰረዙ ባለፈ ለ124 ዓመታት በተከታታይ ተካሂዷል።

በዓለም ላይ አሉ የተባሉ ዝነኛ አትሌቶች የሚሳተፉበት ውድድሩ ፈጣን ሰዓት ከሚመዘገብባቸውና በአትሌቶችም ዘንድ እጅግ ተመራጭ ከሆኑት የጎዳና ላይ ሩጫዎች መካከል ተጠቃሽ ነው። በኮቪድ ወረርሽኝ ምክንያት ለአንድ ዓመት መሰረዙን ተከትሎ ባለፈው ዓመት ደግሞ ከተለመደው ውጪ ወራትን በማራዘም ነበር የተደረገው።

በዚህ ዓመትም ወደመደበኛ መርሃ ግብሩ ተመልሶ ዛሬ የዓለም ምርጥ የማራቶን ሯጮችን ያፎካክራል። በዛሬው ውድድርም እንደተለመደው በጎዳና ላይ ሩጫ ልምድ ያላቸው ዝነኛ አትሌቶች ይሳተፋሉ፤ የምሥራቅ አፍሪካውያኑ አገራት ኢትዮጵያ እና ኬንያ አትሌቶች ፉክክር ደግሞ በጉጉት የሚጠበቅ ሆኗል።

በወንዶች ዘርፍ በውድድሩ እንደሚካፈሉ ካረጋገጡት አትሌቶች መካከል አምስት የሚሆኑት የግል ምርጥ ሰዓታቸው 2ሰዓት ከ3 ደቂቃ ሲሆን፤ የተቀሩት ደግሞ ከ2ሰዓት ከ10 ደቂቃ በታች በመግባት ፈጣን ሰዓት ያስመዘገቡ ናቸው።

ኢትዮጵያዊው አትሌት ብርሃኑ ለገሰ በዝርዝሩ ውስጥ ስማቸው ከተካተተው ፈጣን አትሌቶች ቀዳሚው ሲሆን፤ እአአ በ2019 የበርሊን ማራቶን የገባበት 2:02:48 የሆነ ሰዓት አለው። አትሌቱ በውድድሩ ብቻም ሳይሆን በማራቶን ከተመዘገቡ ፈጣን የዓለም ሰዓቶች መካከል ሦስተኛው ነው። ይኸውም አትሌቱን የውድድሩ አሸናፊ ሊያደርገው ይችላል የሚል ግምት አሰጥቶታል።

የቫሌንሺያ 2020 ማራቶንን 2:03:00 በሆነ ሰዓት በመግባት የራሱን ምርጥ ሰዓት ያስመዘገበው ኬንያዊው አትሌት ኢቫንስ ቺቤት ደግሞ ቀጣዩ ፈጣን አትሌት ነው። አትሌቱ በተያዘው ዓመት የለንደን ማራቶን የሮጠ ሲሆን፤ አራተኛ ደረጃን በመያዝ ነው ያጠናቀቀው፤ ይኸውም የውድድሩ ጠንካራ ተፎካካሪ እንደሚሆን ማሳያ ነው።

የ2019 የቦስተን ማራቶን አሸናፊው ላውረንስ ቼሮኖም በድጋሚ በውድድሩ እንደሚካፈል አረጋግጧል። አትሌቱ በ2020 የቫሌንሺያ ማራቶን የአገሩን ልጅ ተከትሎ ሁለተኛ የሆነበት 2:03:04 የሆነ ሰዓት የውድድሩ ሦስተኛው ፈጣን አትሌት አድርጎታል።

ያለፈው ዓመት የለንደን ማራቶን አሸናፊው ሲሳይ ለማ እና ክንዴ አጣናው በጥቂት ሰከንዶች የሚበላለጥ ፈጣን ሰዓት አላቸው፤ ለአሸናፊነት ከሚገመቱት አትሌቶች መካከል ናቸው። ሌላኞቹ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ለሚ ብርሃኑ እና ሌሊሳ ዴሲሳም ከፍተኛውን የአሸናፊነት ቅድመ ግምት ካገኙት መካከል ቀዳሚዎቹ ናቸው። አትሌቶቹ ያላቸው ፈጣን ሰዓት 2ሰዓት ከ4 ደቂቃ ቢሆንም፣ ከፍተኛ ልምድ አላቸው። ይኸውም ሌሊሳ ዴሲሳ እአአ 2013 እና 2015 እንዲሁም ለሚ ብርሃኑ የ2016 የቦስተን ማራቶን አሸናፊ በመሆናቸው ነው። በአምናው የቦስተን ማራቶን ሦስተኛ ደረጃን ይዞ ያጠናቀቀው ወጣቱ አትሌት ጀማል ይመርም ቀላል ግምት ከማይሰጣቸው አትሌቶች መካከል አንዱ ነው።

በሴቶች በኩልም በተመሳሳይ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች አሸናፊ እንደሚሆኑ በእጅጉ ይጠበቃል። በዚህ ውድድር አንጋፋዋ አትሌት ፋጡማ ሮባ እአአ ከ1997 ጀምሮ በተከታታይ ለሦስት ዓመታት አሸናፊ በመሆን አስደናቂ ታሪክ ማጻፍ ችላለች። እአአ 2014 በአትሌት ብዙነሽ ዳባ የተመዘገበው 2:19:59 የሆነ ሰዓትም እስካሁን ተቀናቃኝ ያላገኘ የውድድሩ ክብረወሰን ነው።

በዚህ ውድድር ከሚካፈሉት መካከል አትሌት ደጊቱ አዝመራው ከፍተኛውን የአሸናፊነት ግምት አግኝታለች። ያለፈው ዓመት የለንደን ማራቶንን ሁለተኛ በመሆን የገባችበት 02:17:58 የሆነ ሰዓትም የአትሌቷ ፈጣን ሰዓት ሲሆን፤ ይህ ሦስተኛ ተሳትፎዋ ይሆናል። የ23 ዓመቷ አትሌት በአምስተርዳም ማራቶን አሸናፊነት የጀመረችውን የጎዳና ውድድር በአዲስ ጉልበትና ብቃት ከክብር ወደ ክብር ትሸጋገርበታለች የሚል ተስፋ አስገኝቶላታል።

እታገኝ ወልዱ እና አባበል የሻነህም ባለፈው ዓመት በቫሌንሺያ እና አምስተርዳም ማራቶኖች ያሳዩትን ብቃት በማሳየት የውድድሩ ምርጥ ተፎካካሪዎች እንደሚሆኑ ይጠበቃሉ።


### አማራ ክልል

ንብረትነቱ ኤልያስ ገብሩ የሆነ ባጃጅ ተሽከርካሪ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 1-21259 አማ ሰሌዳ የጠፋ መሆኑን ባለንብረቱ በ16/06/2014 ዓ.ም በተፃፈ አመልክቷል፡፡ ሰሌዳውን ወድቆ ተሰርቆ ወይም በሌላ ግለሰብ እጅ ላይ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ሪፖርት እንዲያደርግ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑ እንገልፃለን፡፡

**በአ.ብ.ክ.መ ትራንስፖርት ሎጀስቲክስ ባለሥልጣን የደቡብ ወሎ ዞን ትራንስፖርት ተጠሪ ጽ/ቤት የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ቡድን**

### ኦሮሚያ ክልል

የባለንብረቱ ስም በአቶ ቡሌገልቹ አባበንዳ የሆነው የተሽከርካሪ የሠሌዳ ቁጥር 03-58264 ኦሮ የፊት ሠሌዳ የጠፋባቸው ለመሆኑ 29/07/2014 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡

ሠሌዳውን ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይገፑዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 (አስራ አምስት)ቀን ውስጥ ለጽ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርጉ እያስታወቅን ፤ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሠሌዳ የሚታተም መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**የምዕራብ ጉጂ ዞን ትራንስፖርት ባለስልጣን**

የባለንብረቱ ስም ፒስ ማይክሮ ፋይናንስ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-6669 ኦሮ የተሽከርካሪ ዓይነት ሞተር ሳይክል የሻንሲ ቁጥር DGO1X-012129የሞተር ቁጥር 3TS-093106 ሞዴል DT175 የሊብሬ ቁጥር 0239079 የሆነ ተሽከርካሪ ሰሌዳ የጠፋባቸው መሆኑን በመግለጽ በምትኩ ሰሌዳ እንዲሰጣቸው በ23/07/2014 ዓ.ም. ጠይቀውናል፡፡

ሰሌዳውን ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይገፑዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ለጽ/ቤት ሪፖርት እንዲያደርጉ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በኦሮ/ብ/ክ/መ/የሰገጣፎ ሰገዳዲ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ባለሥልጣን**

### አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሳሽ/አመልካች፡- ወ/ሮ ኑሪት ኡመር አህመድ በተከሳሽ/በተጠሪ፡- አቶ ቴዎድሮስ ተረፈ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ፡- አቶ ቴዎድሮስ ተረፈ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ ፍ/ቤቱ ያዘዘ ለ21/8 2014 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡05 ሰዓት ለሆነው ቀነ ቀጠሮ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መናገሻ ምድብ 1ኛ ችሎት ያዘዘ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

የባለንብረት ስም ቶማስ ታደሰ ውብሸት የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-07325 የተሽከርካሪው አይነት ድርብ አገልግሎት የሻንሲ ቁጥር DJNK320TP00397 ሞዴል K32TJUNSL የሞተር ቁጥር 4G63ST2813 የሊብሬ ቁጥር 127581/28717/2783249 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ24/7/2014 ዓ.ም. አመልክተዋል፡፡

ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአቃቂ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

ባለንብረት ስም መንግስቱ በላይ መኮነን የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-99412 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZ5BLSF3HN286203 ሞዴል ZZ1257S4341W የሞተር ቁጥር WD615.47*170917005077* የሊብሬ ቁጥር 0072731/0272032 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ14/7/2014 ዓ.ም. አመልክተዋል፡፡

ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የየካ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ኮሜት ት/አ/ማ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-38195 የተሽከርካሪው ዓይነት ሌላ የሻንሲ ቁጥር LZZ5SB77A303035 ሞዴል zz42 የሞተር ቁጥር 07120710701C የሊብሬ ቁጥር e0093905 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ28/7/2014 ዓ.ም. አመልክተዋል፡፡

ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአቃቂ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም አንዱአምላክ ወ/ማርያም ማሄዳ የሰሌዳ ቁጥር አአ03-01-57607 የተሽከርካሪው አይነት የመስክ ተሽከርካሪ የሻንሲ ቁጥር JT711PJA507001389 ሞዴል LADDCRUSER ሞተር ቁጥር 1HZ-0262111 የሊብሬ ቁጥር 177978/303130 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ3/8/2014 ዓ.ም. አመልክተዋል፡፡

ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የየካ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ጫላ ቀና ገለታ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-76977 የፊት ታርጋ የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZ5ELNC4FN081110 ሞዴል ZZ3257N3447A1 የሞተር ቁጥር WD615.69*150707012547* የሊብሬ ቁጥር 0127655 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ30/7/2014 ዓ.ም. አመልክተዋል፡፡

ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የንፋስ ስልክ ላፍቶ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ጣና ቁፋሮና ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-38705 የተሽከርካሪው አይነት ሌላ የሻንሲ ቁጥር MK26A00496 ሞዴል MK265 የሞተር ቁጥር MD92-300981 የሊብሬ ቁጥር 263668 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ4/8/2014 ዓ.ም. አመልክተዋል፡፡

ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የንፋስ ስልክ ላፍቶ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ጫላ ቀና ገለታ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-76978 የኋላ ታርጋ የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZ5ELNC8FN081112 ሞዴል ZZ3257N3447A1 የሞተር ቁጥር WD615.69*150707013787* የሊብሬ ቁጥር 0127651 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ30/7/2014 ዓ.ም. አመልክተዋል፡፡

ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የንፋስ ስልክ ላፍቶ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ብርቱካን ገበያው ሀይሌ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-90809 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር JT1EOEE9000223404 ሞዴል EE90L-AEMDEW የሞተር ቁጥር NOT*/ የሊብሬ ቁጥር 311602 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 3/8/2014 አመልክተዋል፡፡

ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ወስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የአዲስ አበባ አሽከርካሪ እና ተሽከርካሪ ፍቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን**